አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

# አዲስ ልሳን

ቅጽ 32 ቁጥር 3591 | ቅዳሜ መስከረም 9 ቀን 2019 ዓ.ም | ዋጋው 10.00 ብር







# የዲፕሎማሲው ከፍታ

- ኢትዮጵያ የብሪክስ አባል በመሆን እያከናወነች ያለችው ተግባር የላቀ የዲፕሎማሲ ድል መሆኑ ተጠቁሟል

**በመለሰ ተሰጋ**

ኢትዮጵያ ረዥም ዘመናትን ያስቆጠረ ደማቅ ታሪክ ያላት ሀገር ናት፡፡ በመሆኑም ከዓለም ሀገራት ጋር ያላት የውጭ ግንኙነት ዘለግ ያለ ዕድሜን አስቆጥሯል። በተለይ ሀገሪቱ ካለችበት ስትራቴጂካዊ መልክዓ ምድር አቀማመጥ አኳያ ለዲፕሎማሲ ግንኙነት የበለጠ ተመራጭ ሀገር ሆናለች፡፡

የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲያዊ ድል በዘመናት መካከል ከፍታውን እየጨመረ የመጣ ነው፡፡ ከኢትዮጵያም አልፎ ለአፍሪካውያን ነፃነት ፋና ወጊም ነው። ለዚህ ማስረጃ ይሆነን ዘንድ ከታሪክ ጎጆ ላይ አንድ ሰበዝ እንምዘዝ፤ ፓን-አፍሪካኒዝም፡፡ በዚህ ንቅናቄ “አፍሪካ ትዋሃድ፤ በራሷ ልጆችም ትመራ” በሚል ብርቱ ትግል ተካሂዷል፡፡

ታዲያ የቅኝ ግዛትን ቀምበር ከአፍሪካ ትከሻ አሽቀንጥሮ ለመጣልም በነፍጥ እና በዲፕሎማሲ የታገዘ መራራ ትግልም ተደርጓል፡፡ ይህንንም ተከትሎ 1960ዎቹ አብዛኞቹ የአፍሪካ ሀገራት ከቅኝ ግዛት ተላቅቀዋል፡፡ ለዚህ ነጻነታቸውና ጸረ-ቅኝ ግዛት ትግል ስኬት የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ክንድና ድጋፍ አይተኬ ሚና እንደነበረው ታሪክ ምስክር ነው፡፡

ወደ ገጽ 3 ዞሯል




ፎቶ- ከገፀ ድር

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በህንድ በተካሄደው 18ኛው የብሪክስ የመሪዎች ጉባኤ ላይ ተገኝተው መልዕክት አስተላልፈዋል

## የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ የ2019 ብስራት

4



ፎቶ- ከገፀ ድር

የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ እና ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ አመራሮች የስራ ስምምነት ሲያደርጉ

## የአዲስ አበባ የጤና ቱሪዝም ማዕከልነት ጉዞ

16



ፎቶ- ከገፀ ድር

ለጤና ቱሪዝም አቅም የሚፈጥረ ው የላፍቶ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ከፊል ገጽታ

## የመስከረም ስጦታዎች

20



ፎቶ- ከገፀ ድር

በመስከረም ወር ከተወለዱ ስፖርተኞች መካከል ጥቂቶቹ

# የበዓላቱ ድምቀቶች

- የአዲስ አበባ ልማት ህዝቡ ማህበራዊና ባህላዊ እሴቶቹን በነፃነትና በደስታ እንዲያንጸባርቅ አዲስ ምዕራፍ መክፈቱ ተጠቁሟል





ፎቶ - ከገፀ ድር

የመስቀል ደመራ እና ኢሬቻ በአዲስ አበባ ሲከበሩ

**በለይላ መሀመድ**

አቶ ከተማ ጥላሁን ይባላሉ። ተወልደው ያደጉት በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ ሁለት ልዩ ስሙ አባኮራን ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ነው። እንደ አንድ ነዋሪ የከተማዋን የቆየና የአሁኑን ገጽታ፣ “አብዛኞቹ ሰፈሮች የጽዳት ችግር የነበረባቸው፣ መንገደኞች የሚጸዳዱባቸውና ነዋሪዎች ቆሻሻ የሚጥሉባቸው በመሆናቸው ለማህበራዊ ዝግጅትም ሆነ ለበዓል አከባበር ምቹ አልነበሩም፤ በተለይ ለአደባባይ በዓላት” ሲሉ ለዝግጅት ክፍላችን ተናግረዋል፡፡

ወደ ገጽ 5 ዞሯል

# “እንጦጦ ፓርክ ለመስከረም ወር ጎብኚዎቹ የተለያዩ ዝግጅቶችን አድርጓል”

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የህዝብ መዝናኛ ቦታዎች እና ፓርኮች ኮርፖሬሽን አስተዳደር ምክትል ዋና ስራ አስፈጻሚ እና የእንጦጦ ፓርክ አስተዳደር ኃላፊ አቶ መዝገቡ ይስማው

**በፋንታነሽ ተፈራ**

ላለፉት በርካታ ዓመታት አዲስ አበባ እና ቱሪዝም ሆድና ጀርባ ሆነው ቆይተዋል ቢባል ማጋነን አይሆንም። ጸጋዎቹ ቢኖሩም በልኩ መጠቀም ላይ ቀላል የማይባል ውስንነት ነበር። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ይህን የሚቀይር ስራ እየተከናወነ መሆኑ መሬት ላይ ያለው ስራ የተግባር አስረጂ ነው። የዝግጅት ክፍላችን የዚህ አንድ ማሳያ የሆነው እንጦጦ ፓርክ በማቅናት በተለይ በወርሃ መስከረም ከሌሎች ጊዜያት በተለየ ሊጨምር የሚችለውን ቱሪስት ታሳቢ ያደረገ ምን ዝግጅት አድርጎል ስንል ቃኝተናል፡፡

አቶ አህመድ ባሙሻያህ ይባላሉ፡፡ ከሳዑዲ ዓረቢያ መዲና ከተማ ከታላቅ ወንድማቸው ጋር ኢትዮጵያን ሊጎበኙ መጥተው ነው ያገኘናቸው፡፡

ወደ ገጽ 7 ዞሯል







**አድራሻ** +251 111 112 218 +251 111 267 266 www.amn.gov.et 5 kilo infront of St. Mary Church Addis Ababa Ethiopia

# ርዕሰ አንቀፅ



## የአዲስ አበባ ልማት ለአደባባይ በዓላት የበለጠ ፍካትን የሚፈጥር ነው!

ከተሞች ሕዝብ ተሰባስቦ የሚኖርባቸው፣ የሚሠራባቸው፣ የሚዝናናባቸውና ባህሉን የሚያከብርባቸው ሕያው ስፍራ ናቸው። አዲስ አበባም ይህን ዘመናዊ የከተማ ምስል የምታንፀባርቅ መሆኗን በተጨባጭ የምናየው ነው። እንደ አዲስ አበባ ያለ ግዙፍ ከተማ ለነዋሪዎች ምቹና በተለይም ለአደባባይ በዓላትና የተለያዩ ኩነቶች በቂ የሆኑ ዘመናዊ ስፍራዎች እንዲኖራት ይጠበቃል፡፡

በዚህ ረገድ በቅርብ ዓመታት የተከናወኑ የኮሪደርና የወንዝ ዳርቻ ልማቶች ለከተማዋ አዲስ ገጽታ ከመስጠት ባለፈ የሕዝብ እንቅስቃሴንም የበለጠ ምቹ እያደረጉ ናቸው። ለአብነት ያህል የቦሌ መንገድ ኮሪደር ሲጠናቀቅ ሰፋፊ የመኪና መንገዶች፣ የእግረኛና የብስክሌት መስመሮች፣ የመኪና ማቆሚያዎች፣ የታክሲና የአውቶቡስ ተርሚናሎች፣ ፓርኮች፣ አረንጓዴ ስፍራዎች፣ ፏፏቴዎችና የሕዝብ መጸዳጃዎች ወደ አገልግሎት ገብተዋል። በፒያሳና ሌሎች የኮሪደር ልማቱ የተከናወነባቸው ስፍራዎችም ተመሳሳይ አገልግሎት የሚሰጡ የፕሮጀክቱ ገፀበረከቶች ወደ ህዝብ አገልግሎት ገብተዋል፡፡ ይህ ደግሞ በየአመቱ በበርካታ የአደባባይ በዓላት ለምትደምቀው አዲስ አበባ ልዩ ውበትን የሚፈጥር ነው፡፡

የወንዝ ዳርቻ ልማቱም የከተማዋን የሕዝብ መዝናኛና የበዓል ማክበሪያ ስፍራዎች ምቹነት የሚያሰፋ ሌላ ትልቅ እሴት ነው። ከእንጦጦ እስከ ቀጨኔ መድኃኔዓለም የተንጣለለው የወንዝ ዳርቻ ልማት አረንጓዴ ስፍራዎች፣ የእግረኛና የብስክሌት መንገዶችን አካቷል። ልማቱ 597 ሄክታር መሬት፣ 22 ኪሎ ሜትር የእግረኛ መንገድ፣ 8 ኪሎ ሜትር የብስክሌት መስመርና 4 ኪሎ ሜትር የእግር ጉዞ መንገድን ያካተተ ነው፡፡ እነዚህ ስፍራዎች የዕለት ተዕለት የከተማ ሕይወትን ለማሳመር የሚያገለግሉ የጋራ ሀብቶች ናቸው። አዲስ አበባ የአደባባይ በዓላት መድረክ መሆኗም የከተማዋን ልማት ፋይዳ የሚያጎላ ነው። መስቀል፣ ኢሬቻና ጥምቀት በየዓመቱ በከተማዋ ብዙ ሕዝብን የሚያሰባስቡ የአደባባይ በዓላት ናቸው። በየአመቱ በመስከረም ወር የሚከበረው የሆራ ፊንፊኔ በዓል በርካታ ህዝብ የሚሳተፍበት ነው፤ የመስቀል ደመራም በመስቀል አደባባይ ትልቅ ሕዝባዊ ተሳትፎን የሚያስተናግድ ነው። እንዲህ ያለ ብዙ ሕዝብ የሚሳተፍባቸው በዓላት ሲኖሩ ምቹ መንገድ፣ ንጹሕ አካባቢ፣ ፓርክ፣ የመኪና ማቆሚያና የሕዝብ መገልገያ ስፍራ መኖሩ በዓሉን የበለጠ ያሳምረዋል።

የበዓላት ድምቀት ግን ለነዋሪዎች የደስታ ምንጭ ብቻ አይደለም፤ ለከተማዋ የቱሪዝም እድልም ነው። የመስቀልና ኢሬቻ በዓላትን ለመታደም የመጡ የውጭ ጎብኚዎች ባህላዊ ድባቡን፣ የሕዝቡን አቀባበልና የበዓላቱን ልዩ ይዘት እንዲያደንቁ የበለጠ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራሉ። በዓላት ለሆቴል፣ ለትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎች፣ ለንግድና ለሌሎች የከተማ አገልግሎቶች ገቢ የሚፈጥሩ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች ናቸው። በተለይ አዲስ አበባ የአፍሪካ ሕብረትና በርካታ ዓለም አቀፍ ተቋማት መቀመጫ መሆኗ ከበዓላት ጋር የሚገናኙ ቱሪዝምና የከተማ ዲፕሎማሲ እድሎችን ያጠናክራል።

በመሆኑም የአዲስ አበባ ልማትን እንደ የዛሬ ሀብት ብቻ ሳይሆን ለነገ ትውልድ የሚተላለፍ የጋራ እሴት አድርጎ መመልከት ይገባል። የተገነቡ ኮሪደሮችን፣ ፓርኮችን፣ የወንዝ ዳርቻዎችን፣ የእግረኛና የብስክሌት መንገዶችን መጠበቅ የመንግሥት ብቻ ኃላፊነት ሳይሆን የነዋሪዎችም የጋራ ግዴታ ነው። በተመሳሳይ የልማት ሥራዎችን ወደ ከተማዋ ሁሉም ክፍሎች በማስፋፋት፣ አዲስ አበባ ለነዋሪዎቿ ምቹ የኑሮ ስፍራ፣ ለበዓላት የደመቀ መድረክ፣ ለጎብኚዎች ማራኪ መዳረሻና ለኢትዮጵያ የሚመጥን ዘመናዊ መዲና እንድትሆን የምንፈልገውን የጋራ ራዕይ ወደ ተጨባጭ ሁኔታ ማሸጋገር ይቻላል።

## የእኔ እይታ

**ይህ ገፅ ዜጎች በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ሃሳባቸውን በነፃነት የሚያንፀባርቁበት ሲሆን ይህም የጋዜጣዋን የዝግጅት ክፍል አቋም አይገልፅም።**

## ልብ ልንላቸው የሚገቡ የኢኮኖሚ ዕድሎች

**በኤግል ከ6 ኪሎ**

በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚከበሩ የአደባባይ በዓላት ከባህላዊ እና መንፈሳዊ እሴታቸው ባሻገር ለሀገራት ትልቅ የኢኮኖሚያዊ ዕድገት አቅም ናቸው። እነዚህ ኩነቶች በየዓመቱ በመቶ ቢሊዮን የሚቆጠር ዶላር የሚያንቀሳቅሱ ሲሆን፣ ለቱሪዝም፣ ለሆቴልና እንግዳ ተቀባይነት፣ ለትራንስፖርት፣ ለንግድ እንዲሁም ለፈጠራ ኢንዱስትሪዎች ሰፊ የገበያ ዕድል ይፈጥራሉ። የብራዚሏ ሪዮ ዲ ጄኔሮ ከተማ በየዓመቱ በሚካሄደው የካርኒቫል በዓል ብቻ ከ1 ቢሊዮን ዶላር በላይ ገቢ የምታገኝ ሲሆን፣ የሳውዲ አረቢያዋ መካ ደግሞ ከሐጅ እና ኡምራ ትልቅ የንግድ እንቅስቃሴ በመፍጠር በቢሊዮን የሚቆጠሩ ዶላሮችን ታስገባለች። እነዚህ ከተሞች በዓላቱን በስርዓት በመምራት ከፍተኛ የኢኮኖሚ ጥቅም ለማግኘት ችለዋል።

ኢትዮጵያ ደግሞ እንደ መስቀል፣ ጥምቀት፣ ኢሬቻ፣ ጊፋታ፣ ፊቼ ጨምበላላ፣ ጎቤና ሺኖዬ፣ ሶለል፣ ሻደይ፣ አሸንድዬ እና ሌሎች በርካታ ኃይማኖታዊና ህዝባዊ የአደባባይ በዓላት ባለቤት ነች። እነዚህ በዓላት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎችን በአንድ አደባባይ የሚያሰባስቡና ከፊሎቹም የዩኔስኮ የሰው ልጅ የማይጨበጥ የባህል ቅርሶች ሆነው የተመዘገቡ ቢሆኑም፣ ከእነሱ ማግኘት የሚገባንን ያህል ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ማግኘት ችለናል ብዬ አላምንም። በዓላቱ በሚከበሩባቸው ዕለታት ሰፊ የህዝብ እንቅስቃሴ ቢኖርም፣ ይህን አጋጣሚ ወደተደራጀ ቢዝነስና ዘላቂ የገቢ ምንጭነት የመቀየር ተግባር በአጥጋቢ ደረጃ አልተከወነም ባይ ነኝ፤ ይህን የማድረግ ልምዳችን አሁንም ገና በጅምር ደረጃ ላይ ይገኛል። አብዛኛው ንግድ በጊዜያዊና በባህላዊ የችርቻሮ ሽያጭ ላይ ብቻ የተገደበ ነው፡፡

ለዚህ ዋናው ምክንያት በዓላትን እና ቢዝነስን አያይዞ የመመልከት አመለካከታችን አሁንም ዝቅተኛ መሆኑ ይመስለኛል። የአደባባይ በዓላትን ከስነ-ስርዓቱ ባሻገር ለንግድ፣ ለምርት ማስተዋወቅ፣ ለቱሪዝም መሳቢያነት እና ለስራ ዕድል ፈጠራ መጠቀምን ልምድ እንዳላደረግን እሙን ነው፤ ታድያ የአደባባይ በዓላቱ ባህላዊና ኃይማኖታዊ እሴታቸውን ሳይለቁ፣ ጥንታዊ መልካቸውን መሠረት ያደረጉ ዘመናዊ አገልግሎቶችን፣ የንግድ ኤግዚቢሽኖችን፣ የኪነ-ጥበብ ዝግጅቶችን እና የቱሪስት ማረፊያዎችን በማዘጋጀት ከፍተኛ ሀብት መፍጠር ይቻላል እላለሁ።

ይህን ክፍተት ለመቅረፍ በዓላትን እና ቢዝነስን አያይዞ የመመልከት አመለካከታችን ሊጎለብት ይገባል። በዓላቱ ባህላዊና ኃይማኖታዊ ክብራቸውን ሳይለቁ፣ ዘመናዊ የቱሪዝም ፓኬጆችን፣ የኪነ-ጥበብና የንግድ ኤግዚቢሽኖችን በመቅረጽ የሀገሪቱን የባህል ሀብት ወደ ተጨባጭ ኢኮኖሚያዊ ጥንካሬ መቀየር ይኖርብናል።

ስለሆነም የኢትዮጵያ ባለሀብቶች፣ ጀማሪ ስራ ፈጣሪዎች እና የባህልና ሌሎች የሚመለከታው አካላት በዓላቱ ሲደርሱ ጊዜያዊ ምርቶችን ከመሸጥ ባለፈ፣ የቱሪዝም ፓኬጆችን በማዘጋጀት፣ የፈጠራ ስራዎችን በማቅረብ እና በዓላቱን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ማዕከል በማድረግ መስራት ይገባል። መንግስትም አስፈላጊውን የመሰረተ ልማት እና የደህንነት ማሻሻያ በማድረግ ለንግዱ ማህበረሰብ ምቹ ሁኔታን ማመቻቸት ይኖርበታል።

የአደባባይ በዓላትን መንፈሳዊና ባህላዊ ክብር እንደጠበቅን፣ ለወጣቶች የስራ ዕድል እና የውጭ ምንዛሬ ማግኛ መሳሪያ አድርጎ የመጠቀም አመለካከት ማደግ አለበት። ይሄን ማድረግ ስንችል ብቻ ነው የባህል ሀብታችንን ወደ ተጨባጭ ኢኮኖሚያዊ ጥንካሬ መቀየር የምንችለው ብዬ አምናለሁ።

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ**

**እየተዘጋጀች ዘወትር ቅዳሜ ወደ አንባቢያን የምትደርሰው ይህች ጋዜጣ ግንቦት 1985 ዓ.ም ተመሰረተች**

**አድራሻ**
አምስት ኪሎ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት በሚገኘው ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጎን
ስልክ ቁጥር 0111-574923
ፖ.ሣ.ቁ 27080 code 1000
ፋክስ - 559368
addislisan1985@gmail.com

**የገበያ አገልግሎት እና የማስታወቂያ ዝግጅት ዳይሬክቶሬት**
ስልክ 0111 - 112218

**አታሚ**
ሜጋ ማተሚያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር

**ግራፊክስ ዲዛይን**
እዮብ ተፈራ

**ሌይአውትና ዲዛይን**
ፍልሰታ አየለ
መና ዮሐንስ

**የእርምት ባለሙያ**
ቸርነት ዋለልኝ
ገነት መላኩ

**የዕለቱ አዘጋጆች**
ይግለጡ ዳዴ
ለይላ መሀመድ
ፋንታነሽ ተፈራ
ሸዋርካብሽ ቦጋለ
አብርሃም ገብሬ

**ዋና አዘጋጅ**
ተካልኝ አማረ
Tekalignteke123@gmail.com
አድራሻ ለሚ ኩራ ክ/ከተማ
ወረዳ 3 የቤት ቁጥር B91/17

**ም/ዋና አዘጋጅ**
ሰውነት ኃ/ጊዮርጊስ
መለስ ተሰጋ

**ከፍተኛ አርታኢያን**
ደረጀ ታደሰ
ጊዜው አማረ
ስንታየሁ ምትኩ
ሳህሉ ብርሃኑ
ቶለሳ መብራቴ

# የዲፕሎማሲው... ከገጽ 1 የዞረ

በዓድዋ ተራሮች የታየውን የኢትዮጵያውያን ብርቱ ክንድ ተከትሎ ከድሉ ማግስት ዓለም ወደ ኢትዮጵያ ፊቱን ለማዞር ተገደደ፡፡ እንግሊዝ፣ ፈረንሳይ፣ ጣሊያን፣ ሩሲያ፣ አሜሪካ እና ጀርመንን የመሳሰሉ የምድሪቱ ታላላቅ ሀገራት በአዲስ አበባ ኤምባሲዎቻቸውን ከፈቱ፡፡ ይህንን መልካም ዕድል መሰረት በማድረግም ኢትዮጵያውያን የተከተሉት ጥበብ የተሞላበት ዲፕሎማሲ ሀገሪቱን በዓለም አደባባይ እያነገሰ ዛሬም ከፍታውን ጨምሮ ቀጥሏል፡፡

ኢትዮጵያ፣ ለአፍሪካ የነጻነት ትግል ከፍተኛ አስተዋፅዖ ከማድረግ በተጨማሪ በዓለም ላይ የነበራትን ተጽዕኖ ተጠቅማ ለተጨቆኑ ጥቁሮች ድምጿን አሰምታለች፡፡ ለአብነትም አፄ ኃይለ ሥላሴ እ.ኤ.አ ጥቅምት 4 ቀን 1963 በተባበሩት መንግስታት ድርጅት መድረክ "በአንጎላ፣ በሞዛምቢክና በደቡብ አፍሪካ ወንድሞቻችንን በኢ-ሰብዓዊ ባርነት የሚያስቀምጡ አሳዛኝና ክፉ አገዛዞች እስኪወገዱ፤ ሁሉም አፍሪካውያን እንደ ነፃ ሰዎች በእኩልነት እስኪቆሙና እስኪናገሩ ድረስ፣ የአፍሪካ አህጉር ሰላምን አታውቅም። እኛ አፍሪካውያንም ካስፈለገ እንታገላለን፤ እንደምናሸንፍም እናውቃለን፤ ምክንያቱም መልካም ነገር ክፉን እንደሚያሸንፍ እምነት አለን።" በማለት የኢትዮጵያን ብርቱ ክንድ፣ የዲፕሎማሲ አቅምና ታሪካዊ ከፍታ መመስከራቸው ይታወሳል፡፡

ዛሬም ኢትዮጵያ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) መሪነት ብሪክስን ጨምሮ በተለያዩ ዓለም አቀፍ መድረኮች ከራስ ባለፈ ለአፍሪካውያን ሰላም፣ ብልፅግናና ሁለንተናዊ እኩልነት በመሟገት እና የተለያዩ ውጤቶችን በማስመዝገብ ላይ ናት፡፡ ለአብነትም "አፍሪካ በፀጥታው ምክር ቤት ቋሚ መቀመጫ ሊኖራት ይገባል" በማለት ጠቅላይ ሚኒስትሩ በተለያዩ መድረኮች እያደረጉት ያለውን ዲፕሎማሲያዊ ትግል መጥቀስ እንችላለን።

በእርግጥም የአንድ ሀገር ከፍታ በዛሬ እውነትና በታሪኳም ይለካል፤ የብራዚል ዲፕሎማት ዶክተር ፈርናንዶ ዴ ሜሎ ባሬቶ "Diplomacy: Traditions, Changes, and Challenges" በሚል ርዕስ እ.ኤ.አ በ2024 ባሳተሙት መጽሐፋቸው እንደጠቀሱት የአንድ ሀገር ለዘመናት ከፍታውን ጠብቆ የዘለቀ ዲፕሎማሲ፣ ታሪክና ድል ለዛሬ ብቻ ሳይሆን ለነገም የሚተርፍ የማይነጥፍ እርሾና ሀብት ነው። የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ በረከትም ከዚህ የታሪክ ወንዝ ይቀዳል፡፡

ዛሬ ደግሞ የዓለም አቀፍ ፖለቲካ ሥርዓት ከጊዜ ወደ ጊዜ በፍጥነት እየተለዋወጠ፣ የአንድ ዋልታ የበላይነት እያከተመ እና የባለብዙ ዋልታ (Multipolar) ሥርዓት እየመጣ በሚገኝበት ወቅት ኢትዮጵያ ዘመኑን በዋጀ የዲፕሎማሲ ከፍታ ላይ ናት።




ፎቶ:- ከገጸ ድር

ኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ በዓለም አቀፍ መድረኮች ላይ በአባልነት ስትሳተፍና ስትደመጥ መቆየቷ የዲፕሎማሲ ጥንካሬዋ ምልክት ነው

እንዲህ ባለው ተለዋዋጭ ዓለም አቀፍ ግንኙነት ውስጥ፣ የኢትዮጵያ መንግሥት ባደረገው የላቀ የመሪዎች ዲፕሎማሲ ጥረት ኢትዮጵያ ከታህሳስ 23 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ የብሪክስ ሙሉ አባል መሆን ችላለች።

ይህም አብዛኛው የአፍሪካ ክፍል በአውሮፓውያን ቅኝ ግዛት ሥር በነበረበት ወቅት ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ መስከረም 28 ቀን በ1923 ዓ.ም የዓለም አቀፉ ማኅበረ-መንግሥታት (League of Nations) አባል መሆኗን ተከትሎ በታሪክ ምዕራፍ ላይ የተጨመረና በኢትዮጵያውያን ዲፕሎማሲያዊ ጥበብ የተገኘ የዘመናችን ሌላኛው ታላቅ ድል ነው፤ ይላሉ የፖለቲካ ሳይንስ እና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ባለሙያው አቶ አሕመድ ሰይድ በሽር፡፡

በታሪክ ምዕራፍ ላይ ኢትዮጵያ በዓለም ስርዓት ውስጥ ጉልህ ሚና ስትጫወት ቆይታለች የሚሉት የፖለቲካ ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ባለሙያው፣ ኢትዮጵያ፣ በየዘመናቱ በዓለም ላይ በነበሩ ማህበራት ውስጥ ተሳታፊ፣ ተቀባይነትና ውክልና ያላት ሆና የመቆየቷ ምስጢር በእኩልነት፣ በአብሮ ማደግ እና በሰላማዊ መርህ ላይ የተመሰረተ ስልጡን የዲፕሎማሲ መንገድን በመከተሏ እንደሆነም በብሪክስ ያስመዘገበችውን ከፍታ ዋቢ በማድረግ ጠቁመዋል፡፡ ይህ ድል ታሪክን ወደ ኃይል፣ ዲፕሎማሲን ወደ ልማት፣ አባልነትን ወደ ውጤት የመቀየር ማሳያ እንደሆነም እንዲሁ።

የዓለም ፖለቲካ ዛሬ ከ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ይለያል። የኃይል ማዕከላት በብዙ አቅጣጫ ተስፋፍተዋል። የኢኮኖሚ ኃይል፣ የቴክኖሎጂ አቅም፣ የሕዝብ ብዛት፣ የተፈጥሮ ሀብትና የገበያ መጠን የዓለም ኃይልን አዲስ ቅርፅ እያስያዘው ነው። ኢትዮጵያ ደግሞ በዓለም ስርዓት ውስጥ ጉልህ ሚና የምትጫወት ሀገር ሆና እንደመቆየቷ መጠን ዛሬም ወደየትኛውም ጎራ ሳታደላ ነገር ግን የራሷንና የአፍሪካውያንን ከፍታ በሚያፀና መልኩ የቆየ የብዙ ወገን ዲፕሎማሲ መርህን ተከትላ በከፍታ ዘልቃለች፡፡ ይህ መስመር ከዓድዋ እስከ ብሪክስ የዘለቀ በተለያዩ ዓለማት መካከል የራስን ድምፅ ማስጠበቅ ያስቻለ አዋጭ መንገድ ነው ይላሉ የፖለቲካ ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ባለሙያው።

በእርግጥም ኢትዮጵያ እንደ ብሪክስ ባሉ ዓለም አቀፍ መድረኮች ድምጿን ከፍ አድርጋ ታሪካዊ ከፍታዋን እና በፍትሐዊነት ላይ የተመሰረተ ተጠቃሚነቷን ለማረጋገጥ እየተጋች ነው፡፡ ለአብነትም በሕንድ ኒው ዴልሂ በተካሄደው 18ኛው የብሪክስ የመሪዎች ጉባኤ ላይም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የኢትዮጵያን ታሪካዊና አንገብጋቢ አጀንዳ ከፍ አድርገው አሰምተዋል፡፡

ይሄውም የባሕር በር ማግኘት ለኢትዮጵያ ከምንም በላይ ቀዳሚው እና እጅግ አስፈላጊው የኢኮኖሚ ጉዳይ መሆኑን በአጽንኦት አንስተዋል። ይህ የኢትዮጵያ አቋም፤ ሀገሪቱ ጥያቄዋን በውይይት፣ በሰላም እና በጋራ ተጠቃሚነት መርህ ለማሳካት የጀመረችው የዲፕሎማሲ ጉዞ እንደሚቀጥል ያረጋገጠ ነው።

በዚህ መድረክ ኢትዮጵያ የብሪክስ ስብስብ አባል መሆኗን ተከትሎ በብሪክስ ማዕቀፍ ውስጥ ባለው አዲሱ የልማት ባንክ አባል ለመሆን የምታደርገው ጥረት ከፍ ያለ እንደሆነም ታይቷል፡፡ ይህ ታሪካዊ እርምጃ ለኢትዮጵያ የረዥም ጊዜ ልማት ጉልህ አስተዋጽኦ የሚያበረክት ከመሆኑም በላይ በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት አዲስ የትብብር ምዕራፍ የሚከፍት ነው።

ኢትዮጵያ በአፍሪካ የምትጫወተውን የአመራርነትና የዲፕሎማሲ ማዕከልነት ሚና በመጠቀም፤ የባለብዙ ወገን ትብብር ሥርዓት እንዲጎለብትና የአዳጊ ሀገራት ድምፅ በዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲሰማ የማድረግ አቅሟ ከመቼውም ጊዜ በላይ የተጠናከረ መሆኑን የሚጠቁም ነው፡፡

በሌላ በኩል በጉባኤው ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ያደረጓቸው የጎንዮሽ ውይይቶች የትብብር መስኮችን ያጠናከሩና የዲፕሎማሲ ድል የተመዘገበባቸው አጋጣሚዎች ናቸው። በዚህም በምጣኔ ሀብት፣ በጸጥታ፣ በንግድ እና በግሎባል ሳውዝ (Global South) ትብብር ላይ ያተኮሩ ጉዳዮች ላይ መክረዋል።

የፖለቲካ ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ባለሙያው አቶ አህመድ ሰይድ እንደሚሉት ኢትዮጵያ በብሪክስ ውስጥ ሚናዋ ከተሳታፊነት ወደ አጀንዳ ሰጪነት ከፍ ብሏል፡፡ ኢትዮጵያ በጠንካራ ዲፕሎማሲ ስራ በ2016 ዓመተ ምህረት የብሪክስ አባል መሆኗንና ባለፉት ሁለት ዓመታት ተሳትፎ ላይ ያተኮረ እንደነበር አስታውሰው፣ ነገር ግን በዘንድሮው የመሪዎች ጉባዔ ሚናዋ ወደ አጀንዳ ሰጪነት ማደጉን በባሕር በርና መሰል አንገብጋቢ ጉዳዮች ላይ ያደረጓቸውን ንግግሮች እና ከተለያዩ ታላላቅ ሀገራት መሪዎች ጋር ያደረጓቸውን ምክክሮች ዋቢ በማድረግ አብራርተዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በዚሁ ጉባኤ ላይ የኢትዮጵያን ልምድና የደቡብ ክፍለ ዓለምን የተመለከቱ ቁልፍ ጉዳዮችን አቅርበዋል፡፡ ለአብነትም የኢትዮጵያን የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር፣ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ትግበራ እንዲሁም የኢትዮጵያን የባሕር በር ጥያቄን አስመልክቶ ያደረጓቸው ማብራሪያዎች ይጠቀሳሉ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ለደቡብ ክፍለ ዓለም አማራጭ የፋይናንስ ምንጭ፣ የዓለም ሰላምና ፀጥታ፣ የዕዳ ሽግሽግ፣ በዓለም አቀፍ የባለብዙ ወገን ተቋማት ተገቢ ውክልና ማግኘትን፣ የአየር ንብረት ጉባኤን የተመለከቱ ጉዳዮችንም አንስተዋል፡፡

ኢትዮጵያ በቀጣይ በብሪክስ ውስጥ ሚናዋ ወደ መሪነት ከፍ እንደሚል የገለፁት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ለዚህም የዳበረ የዲፕሎማሲ ልምድ ታሪኳ፣ ፈጣን ኢኮኖሚ ያላት የሕዝብ ቁጥር አስቻይ ሁኔታዎች መሆናቸውን አስረድተዋል። በእርግጥም ኢትዮጵያ በብሪክስ ጉባኤ ላይ ያደረገችው ንቁ ተሳትፎ በዓድዋ ድል ያስመዘገበችውን ከፍታ፣ በአፍሪካ ህብረትና በተባበሩት መንግስታት የነበራትን የመስራችነት ተሳትፎና ደማቅ ታሪክ በዓለም የዲፕሎማሲ መድረክ አጠናክራ መቀጠሏን የሚመሰክር ነው፡፡

# የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ የ2019 ብስራት

- **አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ እና ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ በስድስት ከተሞች የሚካሄደውን የ2019 “ልወቅሽ ኢትዮጵያ ክላሲክስ” የሩጫ ውድድር ለማስተላለፍ የሚያስችል ስምምነት ተፈራርመዋል**

**በቶለሳ መብራቴ**



ፎቶ- ከገፀ ድር
የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ ሰለሞን ዲባባ እና የታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ዋና ስራ አስኪያጅ ዳግማዊት አማረ የስራ ስምምነት ሲያደርጉ

የሀገራችንን የተፈጥሮ ፀጋዎች፣ የበለፀገ ባህልና ታሪክ ከስፖርቱ ዓለም ጋር በማስተሳሰር ለዓለም ለማስተዋወቅ የሚደረጉ ጥረቶች አዲስ ምዕራፍ ላይ ደርሰዋል። የትውልድ ድምፅ የሆነው አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ እና ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ በስድስት የሀገራችን ከተሞች የሚካሄዱትን የ2019 “ልወቅሽ ኢትዮጵያ ክላሲክስ” የሩጫ ውድድሮች በቴሌቪዥን፣ በሬዲዮ፣ በህትመትና በዲጂታል አማራጮች በቀጥታ ለሕዝብ ለማቅረብ የሚያስችላቸውን የስምምነት ሰነድ ተፈራርመዋል። የስምምነት ስነ-ስርዓቱ በኤኤምኤን ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ ሰለሞን ዲባባ እና የታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ዋና ስራ አስኪያጅ ዳግማዊት አማረ መካከል የተፈረመ ሲሆን፣ ዋና ዓላማውም በውድድሮቹ አማካኝነት የየከተሞቹን ስፖርታዊ እንቅስቃሴ፣ የቱሪዝም መስህቦችና ማህበረሰባዊ ባህሎች በስፋት ማስተዋወቅ ነው።

ይህ ተከታታይ የስድስት ውድድሮች መርሃ-ግብር ሯጮችን፣ ጎብኚዎችን እና የባህል ወዳጆችን የሚያገናኝ ልዩ የሀገር ውስጥ ጉዞ ነው። በ2019 የውድድር ዘመን ተሳታፊዎችን ወደ ደብረ ብርሃን፣ ሐዋሳ፣ ጅማ፣ በቆጂ፣ አርባ ምንጭ እና ሐረር የሚወስድ ሲሆን፣ ስፖርቱን ከተፈጥሮ፣ ከባህላዊ ምግቦችና ከህዝቡ ሞቅ ያለ እንግዳ ተቀባይነት ጋር አዋህዶ ያቀርባል። ከቱሪዝም ሚኒስቴርና ከሌሎች አጋር ድርጅቶች ጋር በመተባበር የተዘጋጀው የ“ልወቅሽ ኢትዮጵያ ክላሲክስ” የምዝገባ ሂደት አሁን ላይ ይፋ የተደረገ ሲሆን፣ የኤኤምኤን ሰፊ ተደራሽነትም የውድድሩን ድምቀትና የከተሞቹን እጣ-ፋንታ ወደ አዲስ ከፍታ ያሸጋግረዋል ተብሎ ይጠበቃል።

የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ ሰለሞን ዲባባ ይህ የይፋዊ የትብብር ስምምነት የታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ አዘጋጅ ቡድን በየዓመቱ የሚያከናውናቸውን ሁለገብ የስፖርት ውድድሮች በስፋት ለአየር ለማብቃት፣ ተደራሽነታቸውን ለማስፋት እና የሀገር ውስጥ የስፖርት ቱሪዝምን ለማጎልበት ያለመ ነው ብለዋል፡፡

በስምምነቱ መሰረት አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ የታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ዋና የመገናኛ ብዙኃን አጋር በመሆን የሚሰራ ሲሆን፣ በዋናነት በዓመት ውስጥ የሚካሄዱ ከ20 በላይ የተለያዩ ውድድሮችን፣ የእንጦጦ ፓርክ የሩጫ ዝግጅቶችን፣ የሴቶች የሩጫ ውድድርን እና በተለያዩ የሀገሪቱ ክልሎችና ከተሞች የሚካሄደውን “ልወቅሽ ኢትዮጵያ ክላሲክስ” (Discover Ethiopia Classics) የሩጫ ውድድር ተከታታይ ዝግጅቶችን በስፋት ይሸፍናል።

አቶ ሰለሞን በስምምነቱ ወቅት እንደገለጹት፣ አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ከዚህ ቀደም የተለያዩ ሀገራዊ፣ ህዝባዊ እና ኃይማኖታዊ በዓላትን እንዲሁም ሀገራዊ ምርጫዎችን ያለ ምንም እንከን በቀጥታ ስርጭት በማስተላለፍ ከፍተኛ ልምድ ማካበቱን ተናግረዋል። በተለይም የመስቀል፣ የጥምቀት እና የኢሬቻ በዓላትን ከጠዋት ጀምሮ እስከ ምሽት ድረስ ሙሉ ቀን ሽፋን በመስጠት እንዲሁም የሞተር ባይክ፣ የማውንቴን ባይክ እና የሩጫ ውድድሮችን ጨምሮ በርካታ ዓለም አቀፍ እና ሀገር አቀፍ ዝግጅቶችን በስኬት ማስተላለፉን አውስተዋል።

አቶ ሰለሞን አክለውም፣ አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ አሁን ላይ ራሱን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ እና በሰው ኃይል በማደራጀት ላይ የሚገኝ በመሆኑ፣ የታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ዝግጅቶችን በይዘት፣ በአቀራረብ፣ በፕሮዳክሽን ጥራት እና በዘመናዊ የቴሌቪዥን ስርጭት አሻሽሎ ለማቅረብ ሙሉ ዝግጅት አድርጓል ብለዋል። ሚዲያው ስርጭቱን በቴሌቪዥን ብቻ ሳይሆን በኤፍ ኤም 96.3 ሬዲዮ፣ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ እንዲሁም በተለያዩ የዲጂታል ፕላትፎርሞች (ዩቲዩብ፣ ቲክቶክ እና የማህበራዊ ሚዲያ ገጾች) በ5 የሀገር ውስጥ እና በ2 የውጭ ቋንቋዎች ተደራሽ እንደሚያደርግ ገልጸዋል። በቅርቡም ተጨማሪ የውጭ ቋንቋዎችን በማካተት ዓለም አቀፍ ተጽዕኖ ፈጣሪ ሚዲያ ለመሆን እየሰራ መሆኑን ጠቁመዋል።

> “አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ እና ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ በስድስት ከተሞች የሚካሄደውን የ2019 “ልወቅሽ ኢትዮጵያ ክላሲክስ” ውድድር ለአድማጭ ተመልካቾች ለማስተላለፍ የስምምነት ፊርማ ማድረጋቸው የሀገሪቱን መልካም ገጽታ ለመገንባት ትልቅ አቅም ይፈጥራል”

የታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ዋና ስራ አስኪያጅ ዳግማዊት አማረ በበኩላቸው፣ ብዙ ህዝብ የታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ አዘጋጅ ቡድን በዓመት አንድ ጊዜ በህዳር ወር የሚካሄደውን ዋና ውድድር ብቻ እንደሚያከናውን እንደሚያስብ ገልጸው፣ ከአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ጋር የተደረገው የስራ ስምምነት ይህንን የህዝብ ግንዛቤ ክፍተት ለመሙላት ትልቅ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ተናግረዋል። ተቋሙ በየዓመቱ ከ20 በላይ ውድድሮችን የሚያካሂድ ሲሆን፣ ባለፉት ሁለት ዓመታት ከቱሪዝም ሚኒስቴር ጋር በመተባበር “ልወቅሽ ኢትዮጵያ ክላሲክስ” በሚል መርሃ ግብር በክልል ከተሞች ውድድሮችን ሲያዘጋጅ ቆይቷል።

ዳግማዊት እንደገለጹት፣ የመጀመሪያው ዓመት በ4 ከተሞች፣ በሁለተኛው ዓመት ደግሞ በ6 ከተሞች የተካሄደው ይህ ውድድር አሁን ላይ እንደ አንድ ትልቅ ብራንድ እየጎለበተ ይገኛል። ውድድሩ የአካባቢውን የሀገር ውስጥ ቱሪዝም ለማጎልበት፣ ተሳታፊዎች በሩጫ አጋጣሚ የተለያዩ የኢትዮጵያ ከተሞችን፣ ባህልና ተፈጥሮ እንዲጎበኙ ለማድረግ ያለመ ነው። አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ቀደም ሲል ከአዲስ አበባ ወሰን አልፎ አሁን ሙሉ ሀገራዊ እና ዓለም አቀፍ ተደራሽነት ያለው ሚዲያ በመሆኑ፣ የዚህን ውድድር መልካም ገጽታ እና የቱሪዝም እሴት ለብዙኃኑ ተመልካች ለማድረስ አቅም ይሆነናል ብለዋል።

ቀደም ሲል ከአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ጋር በተካሄደው “የዛይድ ቻሪቲ ሩጫ” እና በሴቶች ውድድር ላይ የታየው ፕሮዳክሽን እና የስፖርቱን ስሜት የመግለጽ አቅም የሚደነቅ እንደነበር ዳግማዊት አውስተዋል። የስፖርት ውድድሮችን በተለይም የ5 ኪሎ ሜትር እና የረጅም ርቀት ሩጫዎችን ሙሉ ሽፋን መስጠት ከፍተኛ ሀብት፣ የካሜራ ባለሙያዎችን ክህሎት እና የቴክኖሎጂ ዝግጅት የሚጠይቅ ቢሆንም፣ አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ በስኬት መወጣቱን ገልጸዋል።

ይህ የጋራ ስምምነት ስፖርታዊ ውድድሮችን ከማስተላለፍ ባለፈ የሀገሪቱን መልካም ገጽታ ለመገንባት፣ የቱሪዝም መስህቦችን ለማስተዋወቅ እና የህዝቦችን ማህበራዊ አንድነት፣ ባህልና ወግ ለማጎልበት ትልቅ አቅም እንደሚፈጥር ተመልክቷል።

አቶ ሰለሞን ዲባባ እንደገለጹት፣ ውድድሮቹ በየክልሎቹ እና በየከተሞቹ በሚካሄዱበት ወቅት ስፖርቱ ብቻ ሳይሆን የአካባቢው ህዝብ ባህል፣ የማህበራዊ ገጽታ፣ የነዋሪዎች አንድነት እና ብዝሃነት በጋዜጣ፣ በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥን እና በዲጂታል ሚዲያዎች ጎልቶ ይወጣል። ይህም ህዝቡ እውነተኛውን የማህበረሰብ እሴት እንዲመለከት ያስችለዋል።

ዳግማዊት በበኩላቸው፣ በሩጫ ሀገርን እና የክልል ከተሞችን ማየት እየተለመደ በመጣበት በዚህ ወቅት፣ ከአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ጋር የተደረገው አጋርነት ተሳታፊዎች እና ተመልካቾች በሩጫው የመሳተፍ እና ሀገራቸውን የማወቅ ፍላጎት እንዲያዳብሩ ያደርጋል ብለዋል። የስፖርት ቱሪዝም በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ትኩረት እያገኘ የመጣ ዘርፍ በመሆኑ፣ ይህ ስምምነት ለሀገር ውስጥ ቱሪዝም እድገት አዲስ ምዕራፍ እንደሚከፍት ያላቸውን እምነት ገልጸዋል።

ሁለቱም ተቋማት በቀጣይነት በተቀራረበ መልኩ በመመካከር፣ በጋራ ብራንዲንግ፣ በዜና፣ በዶክመንተሪ እና በቀጥታ ስርጭት ፕሮግራሞች የውድድሮቹን ዝግጅት ለህዝብ ለማድረስ ቁርጠኝነታቸውን አረጋግጠዋል። አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ዝግጅቶቹን በብዙ ቋንቋዎች እና በተለያዩ የመገናኛ ብዙኃን አማራጮች ተደራሽ በማድረግ የታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ብራንድ ከፍ እንዲል እና የሀገሪቱ ስፖርታዊ ባህል እንዲጎለብት የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ እንደሚሆን ተገልጿል።

## የበዓላቱ... ከገጽ 1 የዞረ



ፎቶ፦ ከገፀ ድር
የመስቀል ደመራ እና ኢሬቻ በአዲስ አበባ ሲከበሩ

ዛሬ ላይ የከተማዋ የቀደመ ገጽታ ተለውጧል። በኮሪደር ልማት የተሻሻሉና ሰፋፊ መንገዶች፣ የተዋቡ አረንጓዴ አካባቢዎች፣ የማረፊያና የመዝናኛ ስፍራዎች እንዲሁም የተሻሻለ ጽዳት ለነዋሪዎች ምቾትን መፍጠር ጀምረዋል። ለውጡ በመንገድ ላይ ብቻ አልተገደበም። የወንዝና የወንዝ ዳርቻ ልማትም ከተማዋን ከተፈጥሮ ጋር የሚያስታርቅ አዲስ ገጽታ እየፈጠረ መሆኑን የሚገልጹት አቶ ከተማ፣ የጎበኟቸውን ከእንጦጦ እስከ ፒኮክ ድረስ ያሉ የወንዝና የወንዝ ዳርቻ የልማት ስራዎችን በማሳያነት በመጥቀስ፣ ለእንቅስቃሴ የማይመቸው መሰረተ ልማት ለመዝናኛና ለእግር ጉዞ ምቹ ወደመሆን እየተሸጋገረ እንደሆነ አብራርተዋል።

ከልጅነታቸው ጀምሮ የመስቀል በዓልን እያከበሩ ነው፡፡ የዘንድሮውን በተለየ ጉጉት እየጠበቁ ነው። ምክንያቱም የኮሪደር እንዲሁም የወንዝና ወንዝ ዳርቻ ልማቱ በአንድ ጊዜ በርካታ የህብረተሰብ ክፍል ለሚታደምበት ለዚህ አይነቱ በዓል ልዩ ድባብ እና ምቾት እንደሚፈጥር ጥርጥር የለውም። ልማቱ በዓሉ ላይ ለሚታደመው ሰው ያለምንም መገፋፋትና መጨናነቅ በነጻነት ለማክበር እድል እንደሚሰጠው የጠቆሙት አቶ ከተማ፣ "ብራዚል፣ ሲንጋፖር፣ ካይሮ፣ ዱባይ፣ ታይላንድ፣ አቴንስ እና ፓሪስ የመሳሰሉ ሀገራትን የኮሪደር ልማት ስራዎች ጎብኝቻለሁ። ውጪ ሀገር ለማየት እሄድበት የነበረውን እዚሁ በትውልድ ሀገሬ አዲስ አበባ ማየት መቻሌ አስደምሞኛል፤ በሀገሬም ኩራት ተሰምቶኛል።" ብለዋል።

ሌላው የከተማዋን ለውጥ በበዓል አከባበር ልምዱ የሚያስረዳው ወጣት

> **አንድ ቱሪስት ወይም ጎብኚ የሚፈልገው በዓሉን ማየት ብቻ አይደለም። የበዓሉን ስፍራ፣ የከተማዋን ጽዳትና ውበት፣ የመጓጓዢያ ምቾትን፣ የማረፊያ ስፍራዎችንና አጠቃላይ የከተማዋን ገጽታ ይመለከታል። ስለዚህ የኮሪደርና የወንዝ ዳርቻ ልማት የበዓላትን አከባበር በማድመቅ የከተማዋን የቱሪዝም አቅም ለማሳደግ የሚያግዝ አንድ መሠረት ነው**

ቶሎሳ ጃለታ ነው። ወጣት ቶሎሳ በመሶብ የአንድ ማዕከል ሰራተኛ ሲሆን ኢሬቻን በየዓመቱ እንደሚያከብር ይናገራል። በበዓሉ አከባበር ወቅት የሚፈጠረው የመንገድ መጨናነቅ ለበርካታ ታዳሚዎች ይፈጥር የነበረውን ፈተና ከአሁኑ ጋር በማነጻጸር፣ "ከዚህ ቀደም በዓሉን ለመታደም ከሌሊቱ 11 ሰዓት ብንነሳም በመንገዱ መጨናነቅ የተነሳ በምንፈልግበት ሰዓት ካለመድረሳችን በተጨማሪ በመገፋፋቱ እና የማረፊያና የመዝናኛ ስፍራዎች ባለመኖራቸው ምክንያት ጉዟችን አድካሚ እንዲሆን አድርጎት ቆይቷል። አሁን ግን መንገዶቹ ሰፋ ብለው በመሰራታቸው፣ የማረፊያ ቦታዎች ያላቸው በመሆኑ ለበዓሉ ተጨማሪ ድምቀት መፍጠር ችለዋል" ሲል ገልጾታል፡፡

ኮሪደርና የወንዝ ዳርቻ ልማት በአደባባይ በዓላት ላይ የሚፈጥሩት ተጨማሪ ድምቀት ምንድ ነው? ሲል የዝግጅት ክፍሉ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የፎክሎር ትምህርት ክፍል መምህር ፊሌ ጃለታን (ዶ/ር) አነጋግሯቸዋል፡፡ ፊሌ (ዶ/ር) እንደሚገልጹት፤ የአደባባይ በዓላት ማለት የአንድ ሕዝብ ወይም ብሔር መገለጫ ሆነው በብዙ ሕዝብ የሚከበሩ በዓላት ናቸው። ሃይማኖታዊ ወይም ባህላዊ ሊሆኑ፣ በተራራ፣ በወንዝ፣ በሜዳ ወይም በተወሰነ የአደባባይ ስፍራም ሊከበሩ ይችላሉ። ዋናው ነጥብ ግን ሕዝቡ በዓሉን በሚያከብርበት ጊዜ የራሱን ማህበራዊና ባህላዊ እሴቶች የሚያንጸባርቅበት መድረክ መሆኑ ነው። በዚህ እሳቤ የኮሪደር ልማት የመንገድ ማስፋትና ውበት መጨመር ብቻ አይደለም። አንድን ቦታ ወይም ተራራ፣ ወንዝ ወይም ሌላ የከተማ ስፍራ ለተጠቃሚዎች ሳቢና ምቹ በሆነ መልኩ በማልማት ሰዎች በነፃነት እንዲጠቀሙበት ሁኔታ መፍጠር ነው።

ፊሌ (ዶ/ር) እንደሚገልጹት፣ ኢሬቻ ከአደባባይ በዓላት አንዱ ሲሆን፣ በቅርብ ዓመታት በተሻለ ሁኔታ እየተከበረ መጥቷል። ይህም ለበዓሉ ተሳታፊዎች ብቻ ሳይሆን ከውጭ ለሚመጡ ጎብኚዎችና ቱሪስቶችም ምቹ ሁኔታ እየፈጠረ ነው። ከዚህ ቀደም እንደአሁኑ ዓይነት ምቹ መሰረተ ልማት አለመኖሩ በዓላትን በሰፊው ለማክበር እንቅፋት ነበር። በተለይም አቅመ ደካሞች፣ ነፍሰ ጡር እናቶች፣ ሕጻናትና አካል ጉዳተኞች በበዓሉ በምቾት እንዲሳተፉ ማስቻል ላይ ውስንነቶች ነበሩ። የመንገዶች ጥበት፣ የወጣ ገባ መሆን (አለመመቸት)፣ የመጓጓዢያ እና የወንዝ ዳርቻዎች የነበራቸው የጽዳት ችግር የአካባቢውን ምቾት ይቀንስ ነበር።

ዛሬ ግን በልማቱ ሁኔታው ተለውጧል። አካባቢዎች ፀድተዋል፤ በተለያዩ ቀለማት ተውበዋል፡፡ መንገዶች ተስተካክለዋል፡፡ ለመራመድና ለማረፍ የሚያስችሉ ስፍራዎች ተፈጥረዋል። ይህም ለበዓላቱ ተሳታፊዎች ብቻ ሳይሆን በዓላቱን ለዓለም ለማስተዋወቅም አዲስ ዕድል ከፍቷል። የአደባባይ በዓላት የአንድ ሕዝብ የባህል መገለጫ ብቻ አይደሉም። በትክክል ሲዘጋጁና ሲተዋወቁ የቱሪዝም መስህብም ናቸው።

አንድ ቱሪስት ወይም ጎብኚ የሚፈልገው በዓሉን ማየት ብቻ አይደለም። የበዓሉን ስፍራ፣ የከተማዋን ጽዳትና ውበት፣ የመጓጓዢያ ምቾትን፣ የማረፊያ ስፍራዎችንና አጠቃላይ የከተማ ልምድን ይመለከታል። ስለዚህ የኮሪደርና የወንዝ ዳርቻ ልማት የበዓላትን አከባበር በማድመቅ የከተማዋን የቱሪዝም አቅም ለማሳደግ የሚያግዝ አንድ መሠረት ነው። ሰዎች በዓላቸውን ሲያከብሩ መዝፈን ካለባቸው ይዘፍናሉ፤ ሃይማኖታዊ በዓል ከሆነም መዝሙራቸውን ይዘምራሉ፡፡ ይጓዛሉ፣ ይገናኛሉ፣ ይደሰታሉ። ይህ ሁሉ የሚከናወነው ምቹ በሆነ የከተማ አካባቢ ውስጥ ሲሆን የበዓሉ ትርጉም የበለጠ ይጎላል።

ፊሌ (ዶ/ር) አያይዘውም፤ እነዚህን ለመኖሪያነትም ሆነ ለአደባባይ በዓላት አከባበር ምቹ ሁኔታ የፈጠሩ መሰረተ ልማቶችን መጠበቅ የልማቱ አንድ አካል ነው። ከተማዋ በዓላትን ለማክበር የተሻለ መድረክ እያገኘች በመሆኑ ይህንን ሀብት የመጠበቅ ኃላፊነት በመንግሥት ብቻ ሊገደብ አይችልም። ነዋሪው ሕዝብ የተሰሩትን መንገዶች፣ መናፈሻዎች፣ የእግረኛ መንገዶች፣ የወንዝ ዳርቻዎችና የመዝናኛ ስፍራዎች መጠበቅ ይኖርበታል። ቆሻሻን በተገቢው ቦታ መጣል፣ የሕዝብ ንብረትን አለመጉዳትና ለሌሎች ተጠቃሚዎች አክብሮት ማሳየት ከዜግነት ኃላፊነት መካከል ተጠቃሾች ናቸው። መንግስትም የተገነቡ ስፍራዎችን በዘላቂነት ማስተዳደር፣ ጽዳትና ጥገናን ማረጋገጥ እና ለሁሉም ተጠቃሚ ምቹ ሁኔታ ማስቀጠል ይጠበቅበታል። ከዚህ አንጻር መገናኛ ብዙሃንም የራሳቸው ድርሻ አላቸው። ልማቱን ማስተዋወቅ ብቻ ሳይሆን የተገነባው ለትውልድ እንዲቆይ የሕዝብን ግንዛቤ ማሳደግ ይጠበቅባቸዋል።

በአዲስ አበባ እየተከናወነ ያለው የኮሪደር ልማት የከተማዋን መሠረተ ልማት ከማሻሻሉም በላይ የህዝቡ ማህበራዊና ባህላዊ እሴቶች በነፃነትና በደስታ እንዲንጸባረቁ አዲስ ምዕራፍ ከፍቷል ሲሉ ፊሌ (ዶ/ር) አብራርተዋል።

ይህ ገፅ ዜጎች በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ሃሳባቸውን የሚያንፀባርቁበት ሲሆን ይህም የጋዜጣዋን የዝግጅት ክፍል አቋም አይገልፅም

# ከምናባዊ ከፍታ ወደ ተጨባጭ እውነታ



**በአሌክስ ብርሀኑ (የሰላምና ደህንነት መምህር እና ተመራማሪ)**

ኢሜል፡- alexbirhanu81@gmail.com

መንግሥትን በእውነተኛ አቅሙ ለመመዘን የሚያስፈልገው ስንት ፖሊሲ አወጣ ወይም ስንት ዕቅድ አዘጋጀ በሚል ብቻ አይደለም። ዋናው መስፈርት የታሰበውን ርዕይ ወደ ተጨባጭ ውጤት ምን ያህል መቀየር እንደቻለ ነው። በዚህ መስፈርት ሲታይ፣ የመደመር መንግሥት ፍልስፍናን በመጽሐፍ ገጽ ላይ ብቻ ያስቀመጠ ሳይሆን፣ በመንግሥታዊ አሠራር፣ በዲጂታል ለውጥ፣ በሕግ ማስከበር፣ በሙስና ትግልና በተቋማዊ ማሻሻያ ውስጥ በተግባር ያሳየ መንግሥት ሆኗል።

የመደመር መንግሥት ዋና መለያዎች የሆኑት የምናባዊ ከፍታ፣ የተቋማት ቅንጅት፣ መላመድና ተለማጭነት፣ እንዲሁም በአሠራር ውስጥ የሚገኙ ክፍተቶችን መሙላት እንደ ንድፈ ሐሳብዊ መገለጫ ብቻ ሆነው አልቀሩም።

እነዚህ ሀሳቦች በተለያዩ የመንግሥት የለውጥ ሥራዎች ውስጥ በተጨባጭ መልክ ተገልጠዋል። ይህም የመደመር ፍልስፍና ከ“ምን እንደሚደረግ” የሚናገር ሀሳብ ብቻ ሳይሆን፣ “ምን ተደርጓል” በሚለው የሚመዘን የመንግሥት አሠራር መሆኑን አሳይቷል።

ከዚህ ለውጥ ጀርባ ያለው መሠረታዊ ግንዛቤ የኢትዮጵያ ችግሮች በአንድ ዘመን የተፈጠሩ እንዳልሆኑ እና በአንድ ዘመንም ብቻ እንደማይፈቱ መቀበል ነው። አስተዳደሩ የተወረሱ ችግሮችን፣ የዛሬን ችግሮችንና ለመጪው ትውልድ ሊተላለፉ የሚችሉ ችግሮችን በአንድ የትውልድ ኃላፊነት ማዕቀፍ ውስጥ በማየት የአሁኑ ትውልድ ሥራ የዛሬን ችግር ብቻ መፍታት ሳይሆን፣ ለነገ የተሻለ ተቋም መገንባት መሆኑን አስቀምጧል።

በዚህ የመደመር እይታ ውስጥ ሙስና እንደ መደበኛ የሕግ ጥሰት ብቻ ሊታይ የሚችል ሳንካ አይደለም። ሙስና የመንግሥትን የአፈጻጸም አቅም በቀጥታ የሚያዳክም ችግር ነው። ሙስና የመንግሥትን ሀብት ብቻ አይዘርፍም፤ መንግሥት የሚያስበውን እንዲያደርግ የሚያስችለውን የአፈጻጸም አቅም ይሸረሽራል። የሕዝብን ሀብት ከታቀደለት ዓላማ ያስቀይራል፣ የውሳኔ አሰጣጥን ያዛባል፣ የተቋማትን ቅንጅት ያዳክማል፣ የሕዝብን እምነት ያሳንሳል፤ በመጨረሻም የመንግሥትን ፖሊሲ ወደ ተግባር የመቀየር አቅም አደጋ ላይ ይጥላል።

በዚህ ሂደት “መሶብ” የተለየ ቦታ ይይዛል። መሶብ የመንግሥትን አገልግሎት ወደ ዲጂታል መድረክ ማሸጋገር ብቻ አይደለም፤ በዜጋና በመንግሥት መካከል ያለውን የአገልግሎት ግንኙነት የቀየረ የአሠራር ለውጥ ነው። ዜጋው ከቢሮ ወደ ቢሮ በመመላለስ ጊዜና ገንዘብ እንዲያባክን የሚያደርገውን አሠራር በመቀነስ፣ አገልግሎትን በዲጂታል መንገድ ወደ ዜጋው አቅርቧል።

ይህ ለውጥ ከአገልግሎት ፍጥነት በላይ ትልቅ ተቋማዊ ትርጉም አለው። ሂደት ዲጂታል ሲሆን የማመልከቻ መዝገብ ይኖራል፤ የውሳኔ ሂደት ይከታተላል፤ ክፍያ በመደበኛ የዲጂታል ሂደት ይፈጸማል፤ የተጠያቂነት ወሰንም ይጠናከራል። በዚህ መልኩ “መሶብ” የሙስና ክፍተቶችን በመቀነስ ረገድ አስፈላጊ የመከላከያ መሣሪያ ሆኗል።

የመንግሥት ዲጂታል መድረኮች በሚያመነጩት የመረጃ ትስስርና የሂደት መዝገብ አማካይነት ሙስና ከተፈጸመ በኋላ ብቻ ለመያዝ ከመጠበቅ ይልቅ፣ እንዲፈጠር የሚያስችሉ የአሠራር ክፍተቶችን ቀድሞ ለመቀነስ አቅም ፈጥረዋል። በዚህ መልኩ “መሶብ” የመደመር መንግሥት የቴክኖሎጂ አቅምን ከተቋማዊ ለውጥ ጋር ያጣመረበት ግልጽ ምሳሌ ሆኗል።

ዲጂታል አሠራር የሙስናን ክፍተት የሚቀንስ ሲሆን፣ ሕግን የሚጥሱ ግለሰቦችን ደግሞ ተጠያቂ እንዲሆኑ ያደርጋል። ከዚህ አንጻር የተወሰዱ የሕግ ማስከበር እርምጃዎች የተጠያቂነትን መርህ በተግባር አሳይተዋል። ከፍተኛ የሕዝብ ኃላፊነት የያዙ ግለሰቦችም ከሕግ በላይ እንዳልሆኑ ያሳየው ይህ እርምጃ ተቋማዊ ተጠያቂነትንም አጉልቶ አሳይቷል።

ነገር ግን የፀረ-ሙስና ሥራ በግለሰብ መያዝና መክሰስ ብቻ አያበቃም። ምርመራን በማስረጃ መምራት፣ የፍርድ ሂደቱ በሕግ መሠረት መከናወኑ፣ የተገኘን ሀብት ምንጭ በጥልቀት መመርመርና በሕግ የተደነገገውን የማስመለስ ሂደት መከተል የፀረ-ሙስና ትግሉን ተቋማዊ ትርጉም ያጠናክራል። በዚህም ማንም የመንግስት አገልጋይ ወይንም ሹመኛ በሙስና የተገኘን ሀብት ሊበላበት የማትፈቀድ ሀገር ከመገንባት አኳያ ብዙ የህግ እና አሰራር ለውጦች ግዜዉ በሚጠይቀው አውድ እየተስተካከለ የሚሄድ ተለማጭ እና ተለማማጅ መንግስት ሆኖ መገኘት የግድ ይላል፡፡

የፀረ-ሙስና ትግል ተጠያቂነትን ብቻ ካስቀመጠ የተሟላ ውጤት አያመጣም። ሙስና በሕዝብ ሀብት ላይ ጉዳት ስላደረሰ፣ በሕግ የተፈቀደ የንብረት ማገድ፣ የሀብት ምንጭ መመርመርና የተረጋገጠ ሕገ-ወጥ ሀብትን ማስመለስ የፀረ-ሙስና ሥርዓቱ ዋና ክፍሎች ናቸው። ይህ ሥራ ሲጠናከር የሕዝብ ሀብት ወደ ሕዝብ ተመልሶ የልማት አቅም ይሆናል።

ጠንካራ የሕግ ማስከበር፣ የዲጂታል አሠራር፣ የውስጥ ቁጥጥርና የሀብት ማስመለስ በአንድ ላይ ሲሠሩ የመንግሥት ተቋማት ከግለሰቦች ፈቃድ ይልቅ በሥርዓትና በሕግ ላይ የተመሠረቱ እንዲሆኑ ያግዛሉ። ይህ ደግሞ የመደመር መንግሥት የሚያተኩርበትን የተቋማዊ አቅም ግንባታ ወደ ተጨባጭ ሁኔታ ያመጣል።

የመደመር ፍልስፍና ከሚያቀርበው ዋና የትውልድ እይታ አንጻር፣ የዛሬ መንግሥታዊ ውሳኔ የነገን መንግሥት አሠራር ይወስናል። የሙስና ትግሉም የዛሬን ጥፋተኛ ለመቅጣት ብቻ የሚደረግ ሥራ አይደለም፤ የነገን የመንግሥት ተቋም ለመገንባት የሚደረግ የትውልድ ሥራ ነው።

በመጨረሻ፣ የመደመር መንግሥት ትርጉም በአንድ አረፍተ ነገር ሲጠቃለል፣ ርዕይን ወደ አቅም፣ አቅምን ወደ አፈጻጸም፣ አፈጻጸምን ወደ ተጨባጭ ውጤት መቀየር ነው። መሶብ የዚህ ለውጥ የዲጂታል መገለጫ ሆኗል፤ የሕግ ማስከበር የተጠያቂነት መገለጫ ሆኗል፤ የሕዝብ ሀብት ማስመለስ የፍትሕና የሀብት ጥበቃ መገለጫ ሆኗል፤ ተቋማዊ ማሻሻያዎቹ ደግሞ እነዚህ ለውጦች በግለሰብ ፈቃድ ሳይሆን በሥርዓትና በተቋም እንዲቀጥሉ መሠረት ጥለዋል።

ስለዚህ የመደመር መንግሥት ወደፊት የሚመጣ ፕሮጀክት ሳይሆን፣ በተለያዩ የመንግሥት የለውጥ ሥራዎች ውስጥ መገለጥ የጀመረና በተግባር የተፈተነ አሠራር ሆኗል። ፍልስፍናው በመጽሐፍ ገጽ ላይ ተገልጾ ብቻ አልቀረም፤ ከፍጹም ምናብ ወደ ተጨባጭ እውነታ የተሸጋገረ መንግሥታዊ አሠራር ሆኖ በተግባር ተገልጧል። የመደመር መንግሥት ትልቁ ውጤት የተከናወኑ ፕሮጀክቶች ብቻ ሳይሆኑ፣ መንግሥት የሚያስብበትን፣ የሚወስንበትን፣ የሚያገለግልበትንና ተጠያቂ የሚሆንበትን አሠራር መቀየሩ ነው። ይህ ነው ከምናብ ወደ እውነታ የተደረገው የተቋማት ግንባታና የአፈጻጸም አብዮት ጉዞ።

# በብሪክስ ስብሰባ ላይ የተንጸባረቁ የ“መደመር” መርሆዎች

**በሻሎም አብርሃም**

በኒው ዴልሂ በተካሄደው 18ኛው የBRICS የመሪዎች ጉባኤ ላይ፣ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) “መደመር” የሚለውን ቃል በቀጥታ ባይጠቀሙም ከዚህ ፍልስፍና ጋር የተሳሰረ መልእክት አስተላልፈዋል። ንግግራቸው የመደመር ፍልስፍና ዋና ሀሳብ የሆነውን ዓለም አቀፋዊ አተገባበር ያሳያል፤ ይኸውም በተናጠል የሚታዩ አቅሞች ለጋራ ዓላማ ሲጣመሩ የበለጠ ውጤታማ ይሆናሉ የሚለው ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በብሪክስ ውስጥ ስላሉት ዕድሎች ሲናገሩ፡- “በአባል ሀገራቱ ዘንድ ካፒታል፣ ቴክኖሎጂ እና ገበያዎች አሉ። ዕድሉ ያለው እነዚህን በማጣመር ተጨማሪ እሴት መፍጠር እና ያ እሴት ሀብቱ በሚገኝበት ቦታ ላይ ማዋል ነው” ብለዋል።

ይህ አገላለጽ ግልጽ የሆነውን የመደመር ሀሳብ የያዘ ነው። ካፒታል፣ ቴክኖሎጂ እና ገበያዎች በተናጠል ዋጋ ቢኖራቸውም፣ ሆን ብሎ ማጣመር ደግሞ የበለጠ ውጤት ያስገኛል።

በመደመር ፍልስፍና ሀብትንና አቅምን በዝግታ ወይም በዘፈቀደ ማከማቸት ተፅዕኖ አይፈጥርም። ይልቁንም የተለያዩ ጥንካሬዎችን ለጋራ ዓላማ በማዋል ከተናጠል ጥረት ድምር የሚበልጥ የላቀ የተቀናጀ አቅም (synergy) መገንባት ዋናው መርህ ነው።

ይህ ሀሳብ በአፍሪካ የተፈጥሮ ሀብት ላይ ሲተገበር ይበልጥ ግልጽ ይሆናል። ኢትዮጵያ በማዕድን፣ በታዳሽ ኃይል እና በኢንዱስትሪ መሰረቷ ላይ አጋርነት ለመፍጠር ዝግጁ ናት። የተፈጥሮ ሀብት፣ ካፒታል፣ ቴክኖሎጂ እና ገበያ ሳይጣመሩ ብቻቸውን ሰፊ ልማት አያመጡም። ሲጣመሩ ደግሞ ሀብቱ ወደ ውጤታማ ኢኮኖሚያዊ አቅም የመቀየር ዕድል ይፈጥራል። ይህ ከመደመር "የመደጋገፍ" (complementarity) መርህ ጋር ይጣጣማል። ልዩነቶች በጋራ ዓላማ ዙሪያ ሲጣጣሙ የጋራ ውጤት ያመጣሉ።

እሴት የሚፈጠረው ሀብቱ በሚገኝበት ቦታ መሆኑን ማመልከታቸው ሌላው አስፈላጊ ገጽታ ነው። ትብብር ማለት ሸቀጦችን መለዋወጥ ብቻ ሳይሆን ጥሬ ዕቃዎችን፣ ቴክኖሎጂን እና ኢንቨስትመንትን ወደ አገር ውስጥ ሥራ እና መሠረተ ልማት መለወጥ ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ “አንድ ላይ፣ ብሪክስ ትብብርን ወደ የጋራ እሴት፣ የመቋቋም አቅም እና ዘላቂ እድገት ሊለውጡት ይችላሉ” ብለዋል። እዚህ ላይ ትብብር የጋራ እሴትን ለማምረት እንደ ዘዴ የቀረበ ሲሆን፣ ይህም ከዜሮ ድምር አስተሳሰብ ወደ የጋራ ጥቅም የመሸጋገር አቅጣጫን ያሳያል።

የመደመር ፍልስፍና ማዕከላዊ ሀሳብ የተበታተኑ አቅሞችና ልዩነቶች ለጋራ ዓላማ ሲቀናጁ የላቀ ውጤት እንደሚፈጥሩ ማመን ነው። ይህ አስተሳሰብ አገሮች በብቸኝነት ከመንቀሳቀስ ይልቅ ጥንካሬዎቻቸውን አስተባብረው የጋራ ዕድገትና እሴት እንዲገነቡ ያበረታታል። በባለብዙ ወገን ግንኙነት ውስጥም ትብብርንና መደጋገፍን በማስቀደም የሁሉንም ወገን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ ዘላቂ መፍትሔ ያመጣል፤ ይህ መደመር ነው፡፡

## "እንጦጦ ... ከገጽ 1 የዞረ

እንጦጦ ፓርክን ሲጎበኙ የመጀመሪያቸው እንደሆነ በመግለጽ፣ አየሩን እና አረንጓዴ ስፍራውን እንደወደዱት ሀሳባቸውን አካፍለውናል፡፡

"አዲስ አበባ የተለያዩ የሚጎበኙ ቦታዎች አሏት፡፡ ከእነዚህ መካከል እንጦጦ ፓርክ አንዱ ነው፡፡ ከሚጎበኙት የመስህብ ቦታዎች ባለፈ ኢትዮጵያውያን እንግዳ ተቀባይነታቸው ደስ ይላል። ከአየር መንገድ ጀምሮ በፈገግታና በአክብሮት ነው የተቀበሉን" ሲሉም አቶ አህመድ አክለዋል፡፡

"እኔ እና ወንድሜ ከአዲስ አበባም ወጣ ብለን ላንጋኖ ሃይቅና ጨበራ ጩርጩራን ጨምሮ የተለያዩ የቱሪስት መስህቦችን የመጎብኘት ዕቅድ አለን። የኢትዮጵያ አየር ንብረት፣ ለምለምነቷ ሰውን ይስባል፡፡ እኛም አሁን ጎብኝተን ሄደን አንቀርም በድጋሜ ቤተሰቦቻችንን ይዘን እንመጣለን፡፡ ባህላዊ ምግቦቹም ተበልተው አይጠገቡም፡፡ ቡናውም ይጣፍጣል" ሲሉም ኢትዮጵያ በመምጣታቸው ደስተኛ መሆናቸውን በአስጎብኛቸው አስተርጓሚነት ስሜታቸውን ገልጸውልናል፡፡

ፓርኩን ለሶስተኛ ጊዜ ሊጎበኙ እንደመጡ የሚናገሩት ሌላኛዋ አስተያየት ሰጪ ወይዘሮ ፍቅር ኤሊያስ ናቸው። በአዲስ አበባ የተሰሩትን ወዳጅነት አደባባይ፣ አራዳ ፓርክን እና የቀበናን የወንዝ ዳርቻ ልማት መጎብኘታቸውን ይናገራሉ፡፡

"በእንጦጦ ፓርክ በተለየ ሁኔታ ተፈጥሯዊ የሆኑ ነገሮች ይታያሉ። ይህም ትልቅ ደስታን ይፈጥራል፡፡ ዋናውና ትልቁ ነገር ንፁህ አየሩ ነው፡፡ ከዚህ በተለየ ከተማ ውስጥ የሌለና የተለየ ነገር ወጣ ብሎ አይቶ መመለስም ደስ ይላል"፡፡ ያሉት ወይዘሮ ፍቅር ከዚህ በፊት በነበራቸው ጉብኚት ልጆቻቸውን እንዳስጎበኟቸው ነግረውናል፡፡

"ከተማዋ ከዚህ በፊት ያላት ገፅታ በዚህ ልክ ቱሪስቶችን የሚስብ፣ የመንገድ እና ሌሎች መሰረተ ልማቶች የተሟሉ አልነበሩም፡፡ በአሁኑ ወቅት ግን እያደገችና እየተለወጠች መምጣቷን እንጦጦ ፓርክ ምስክር ነው፡፡ የፓርኩ መግቢያን ጨምሮ የተለያየ ክፍያ የሚፈጸመው በዲጂታል መንገድ ነው፡፡ አቀባበላቸውና መስተንግዷቸውም ደስ ይላል፡፡" ሲሉም አክለዋል፡፡

ወይዘሮ አሜን እሸቱ የእንጦጦ ፓርክ አስጎብኚ ናቸው፡፡ ለአራት ዓመት ያህል የማስጎብኘት ተሞክሮም እንዳላቸው ይናገራሉ፡፡ ቱሪስቶች ኢትዮጵያን በተለይ ደግሞ እንደ ስሟ አዲስ የሆነችውን አዲስ አበባን በሚፈልጉት ልክ አውቀዋትና ተዝናንተው እንዲመለሱ ማድረግ የአስጎብኚዎች ሚና ነው ይላሉ፡፡

እርሳቸው እንደሚሉት፣ ከተማችን አዲስ አበባ እየለማችና እየተዋበች ነው። ቱሪስቶችን ለመሳብ እና ለማቆየት የሚያስችሉ በርካታ ተጨማሪ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ ይህ ለቱሪዝሙ ትልቅ አበርክቶ አለው፡፡ የቱሪዝም መዳረሻነቷ



ፎቶ፡- ከገፀ ድር
የእንጦጦ ፓርክ ከፊል ገፅታ

መስፋቱ ደግሞ ለአስጎብኚዎች ትልቅ እድል ነው፡፡

"ጎብኚዎች እንደ ከዚህ በፊቱ አዲስ አበባን አልፈዋት አይሄዱም፡፡ አሁን የተሰሩ ሙዚየሞችንና ፓርኮችን እንዲሁም ጎዳናዎችን እናስጎበኛቸዋለን። አዲስ ፕሮጀክት ሲመረቅ የጉብኝት ዝርዝራችን ውስጥ በማካተት ቱሪስቶችን ለማቆየት እና ከተማዋንም፣ ራሳችንንም ለመጥቀም የሚያስችሉ ስራዎችን እንሰራለን፡፡" ብለዋል፡፡

"የመስከረም ወር እንደ መስቀልና ኢሬቻ ያሉ የአደባባይ በዓላት የሚከበሩበት ነው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞም የቱሪስት ወር በመሆኑ በውጭ ሀገራት የሚኖሩ አትዮጵያውያን ለጉብኝት የሚመጡበት ነው፡፡ ለዚህ እኔ እንደ አንድ አስጎብኚ በተለያዩ የማህበራዊ ትስስር ገጾች አዳዲስና ነባር መዳረሻዎችን አስተዋውቃለሁ፡፡ ከአየር መንገድ ጋር በመነጋገር አቀባበል አድርገው እንጦጦ ፓርክን እንዲጎበኙ በቦታው የማድረስ ስራ ሲሰሩ እኔና የስራ ባልደረቦቼ ተቀብለን የእንጦጦ ፓርክን ታሪክ ለጎብኚዎች የማሳወቅ ስራ እንሰራለን። ስለምናስጎበኘው ቦታ በደንብ አውቀን ሳናዛባ መናገር መቻል ይጠበቅብናል። ከዚያም እንደ ፍላጎታቸው እናስጎበኛቸዋለን፡፡ በዚህም እንጦጦ ፓርክን በፊት የሚያውቁት ጎብኚዎች አሁን ላይ ቀልብን የሚስቡና አጓጊ አዳዲስ ነገሮችን እንዲያዩ ይደረጋል። ጎብኚዎችም ከበፊቱ ጋር እያነጻጸሩ ይደነቃሉ፡፡ ይህም ለእኔ ኩራትም ደስታም ይፈጥርልኛል" ሲሉ ወይዘሮ አሜን ተናግረዋል፡፡

አንድ አስጎብኚ ኢትዮጵያ ምንድን ናት? የሚለውን አውቆ እንዲሄድ የማድረግ ስራ ነው የምሰራው የሚሉት አስጎብኚዋ፤ ለዚህ ደግሞ አንዱ ያደረጉት ዝግጅት የቋንቋዎችን ችሎታ ማሳደግ ነው፡፡ በዚህም በብዛት በእንግሊዘኛ፣ አማርኛ፣ አረብኛ እንዲሁም ቻይንኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ጎብኚዎችን ያስተናግዳሉ፡፡ ይህንን እውቀት የበለጠ ከፍ ለማድረግና ለጎብኚዎች ተገቢውን አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል እውቀት ለማግኘት ዝግጁ መሆናቸውን

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

# ምን ልርዳዎ?

## የበዓል ሰሞን የጥንቃቄ እርምጃ

የመስቀል ደመራ በዓልን ምክንያት በማድረግ የእሳት ቃጠሎን ጨምሮ ሊደርሱ የሚችሉ ድንገተኛ አደጋዎች አስቀድሞ ለመከላከል ከሚደረጉ ጥንቃቄዎች መካከል የሚከተሉትን ተግባራት መከወን ጠቃሚ ነው፡-

- ችቦው ርጥብ ሆኖ አልነድ ካለ በፈሳሽ ነዳጅ በማራስ ከማቀጣጠል መቆጠብ፣
- ችቦ ቤት ውስጥ ሲለኮስ በቤት ወስጥ የሚገኙ ምንጣፎችና መጋረጃዎች እንዳይቀጣጠሉ መጠንቀቅ፣
- ዘመናዊ ችቦ ወይም ርችት ሲለኮስ የአጠቃቀም ጥንቃቄ ማድረግ፣
- ርችቱ ተወርውሮ ሲሄድ በአካባቢው በሚገኙ በሳር ክምር፣ የሳር ክዳን ባላቸው ጎጆ ቤቶች፣ ነዳጅ ማደያ ዴፖዎችና ማደያ ጣቢያ ላይ እንዳያርፍ የጥንቃቄ መመሪያዎችን ተግባራዊ ማድረግ፣
- ደመራ የሚደመርበት ስፍራ ከነዳጅ ማደያ፣ ከኤሌክትሪክና ስልክ ምሰሶዎችና መስመሮች የራቀ መሆኑን ማረጋገጥ፣
- ደመራ ተለኩሶ ተቀጣጥሎ ካለቀ በኋላ በውሃ ማጥፋት ያስፈልጋል።
- በምግብ ማብሰያ አካባቢ የኤሌክትሪክ ምድጃዎች፣ የቡታ ጋዝ፣ የጧፍና የከሰል ምድጃዎችን በአግባቡና በጥንቃቄ መጠቀም፣
- ሻማና ጧፍ በምንጠቀምበት ወቅት ከተቀጣጣይ ነገር ማራቅ፣
- ጠጥቶ አለማሽከርከር ይገኙበታል።

እነዚህንና መሰል ጥንቃቄዎችን አድርገው ባልታወቀ ምክንያት በቤትዎም ሆነ በአካባቢዎ የእሳትና ሌሎች ድንገተኛ አደጋዎች ቢከሰት ለእሳትና ድንገተኛ አደጋዎች፣ ለወላድና የድንገተኛ ህክምናና አምቡላንስ አገልግሎት በነፃ መስመር 939፣ በቀጥታ መስመሮች 011-1-55 53 00 ወይም 011-1-56 86 01 ይደውሉ።

ምንጭ፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የእሳትና አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን

# ስማርት ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጁን ምን ልዩ ያደርገዋል?

**በለይላ መሀመድ**

በአሁኑ ወቅት የከተሞች እድገትና የኢኮኖሚ ለውጥ በቴክኖሎጂ፣ በፈጠራና ብቃት ባለው የሰው ኃይል የተመሰረተ ነው። በተለይም በኢንዱስትሪ፣ በግንባታ፣ በአውቶሞቲቭ፣ በኤሌክትሪክ፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በመሳሰሉ የሙያ ዘርፎች የተሟላ ክህሎት ያላቸው ዜጎች ፍላጎት እየጨመረ መጥቷል። ስማርት ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ደግሞ የዘመኑን የሙያ ትምህርት ፍላጎት ለመመለስ የሚያግዝ ተቋም ስለመሆኑ አጠያያቂ አይደለም። አዲስ አበባም በቅርቡ ለስማርት ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ የህንጻ ግንባታ አስጀምራለች፡፡

የአዲስ አበባ ከንቲባ አዳነች አቤቤ፣ የኮሌጁን ግንባታ ባስጀመሩበት ወቅት እንደተናገሩት፣ የስማርት ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ለዛሬው ብቻ ሳይሆን ለነገውም ትውልድ ትልቅ አሻራ የሚተውና የሀገርን የኢኮኖሚ ዕድገት በዕውቀትና በክህሎት ለመደገፍ ታስቦ እየተገነባ ያለ የፈጠራ ማዕከል ነው። ፕሮጀክቱ በተቀመጠለት የጊዜ ሰሌዳና ዓለም አቀፍ ጥራቱን በጠበቀ መልኩ ተጠናቅቆ ለአገልግሎት እንዲበቃ የከተማ አስተዳደሩ አስፈላጊውን እገዛ እና ድጋፍ ከማድረግ ባለፈ ጥብቅ ክትትል እንደሚያደርግ አብራርተዋል።



ፎቶ፡- ከገፀ ድር
በቅርቡ ግንባታው የተጀመረው የአዲስ አበባ ስማርት ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ዲዛይን

ለመሆኑ ስማርት ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ሲባል ምን ማለት ነው? በቅርቡ ግንባታው የተጀመረው የስማርት ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ግንባታ ሲጠናቀቅ ምን ምን ተግባራትን ያከናውናል? በተለይም ለቴክኒክና ሙያ ዘርፍ ምን አይነት ተጨማሪ አቅም ይፈጥራል? የሚሉትን ጨምሮ በጉዳዩ ላይ ሰፊ ማብራሪያ ይሰጡን ዘንድ የዝግጅት ክፍላችን በአዲስ አበባ ስራና ክህሎት ቢሮ የውጤት ተኮርና ተቋማት ልማት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ ዳግማዊት ግርማን አነጋግሯቸዋል፡፡

እንደ ምክትል ቢሮ ኃላፊዋ ገለጻ፤ ስማርት ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ማለት የባህላዊ የሙያ ትምህርት አሰጣጥን ከዘመናዊ ቴክኖሎጂ፣ ከተግባራዊ ስልጠና፣ ከፈጠራና ከኢንዱስትሪ ፍላጎት ጋር የሚያጣምር የሙያ ማሰልጠኛ ማዕከል ነው። ስማርት የተባለበት ምክንያትም ትምህርቱ በዘመናዊ ዲጂታል መሳሪያዎችና በላቦራቶሪዎች የተደገፈ የመማር ማስተማር ሂደት ሲሆን ተማሪዎች በመጽሐፍ መማር ብቻ ሳይሆን በተግባር በመስራት፣ ችግር በመፍታትና አዳዲስ ሀሳቦችን በማመንጨት የሙያ ብቃታቸውን እንዲያዳብሩ በሚያስችል መልኩ የተቃኘ በመሆኑ ነው።

በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ አያት ጣፎ አካባቢ በግንባታ ላይ ያለው ስማርት ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ እንደሀገር የመጀመሪያው ነው፡፡ ኮሌጁ በአዲስ አበባ ከተማ ብቁ እና ተወዳዳሪ ሰልጣኞችን ለማፍራት በከተማዋ ከሚገኙት 15 የቴክኒክ እና ሙያ ኮሌጆች በተጨማሪ ለሰልጣኞች የተሻለ ዕድልን ይዞ የመጣ ነው። ከከተማም አልፎ እንደ ሀገር የተጀመረውን ብቃት ያለው የሰው ሀይል የማፍራት ርዕይ እውን በማድረግ ቁልፍ ሚና የሚጫወት ነው።

ምክትል ቢሮ ኃላፊዋ አያይዘው እንደገለጹት፤ ኮሌጁ ግንባታው ተጠናቅቆ ስራ ሲጀምር ወጣቶችን ከንድፈ ሀሳብ ባለፈ በተግባር ላይ ያተኮረ እና ዘመናዊ ዲጂታል ቴክኖሎጂን የሚጠቀም ስልጠና በመስጠት ከስራ ፈላጊነት ወደ ስራ ፈጣሪነት የሚያሸጋግር ነው። የኮሌጁ ግንባታ ተጠናቅቆ ወደ ስራ ሲገባ ከ400 በላይ የሙያ ዘርፎች ላይ ስልጠና ይሰጣል። ጠቅለል ባለ መልኩ ማኑፋክቸሪንግ፣ አውቶሞቲቭ ቴክኖሎጂ፣ ኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክስ፣ ኮሙዩኒኬሽን፣ ቴክስታይል፣ የሲኤንሲ (የተለያየ መጠን ያላቸው ብረት መቁረጪያ እና ቅርጽ ማውጫ) ማሽነሪ ቴክኖሎጂ ላይ ትኩረት ተደርጎ ስልጠና ይሰጣል፡፡ ኮሌጁ በሂደት ተጨማሪ ገበያ መር የሆኑ የስልጠና ዘርፎችን እያሰፋ ይሄዳል፡፡

የኮሌጁ ዋነኛ ተግባር የሰልጣኞችን ተግባራዊ ክህሎት ማጠናከር ነው። ሰልጣኞች ፍላጎታቸውን መሰረት አድርገው በሚሰለጥኑባቸው ዘርፎች በተግባር የሚያስፈልጋቸውን ክህሎት እንዲያዳብሩ ያስችላቸዋል። ከስማርት ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ የሚጠበቀው ውጤትም በትምህርትና በስራ መካከል ያለውን ክፍተት ማጥበብ ነው። ሰልጣኞች በክፍል ውስጥ የሚማሩትን የንድፈ ሀሳብ ዕውቀት በላብራቶሪና በዎርክሾፕ በመተግበር በሙያቸው ተፈላጊ የሆነ የተግባር ክህሎት ያገኛሉ። ይህም ከተመረቁ በኋላ በስራ ቦታ ላይ በፍጥነት እንዲላመዱና የሚያጋጥማቸውን ሙያዊ ክፍተት በራሳቸው እንዲፈቱ ያግዛቸዋል።

> **ስማርት ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ማለት የባህላዊ የሙያ ትምህርት አሰጣጥን ከዘመናዊ ቴክኖሎጂ፣ ከተግባራዊ ስልጠና፣ ከፈጠራና ከኢንዱስትሪ ፍላጎት ጋር የሚያጣምር የሙያ ማሰልጠኛ ማዕከል ነው**

## ኮሌጁ ከነባር ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች በምን ይለያል?

ስማርት ኮሌጆች ከሌሎች የሚለዩት በአደረጃጀታቸውና በሚጠቀሙት የውስጥ ማሽነሪዎቻቸው ነው። ዘመኑን የሚመጥኑ ማሽነሪዎችን መጠቀማቸው ነው፡፡ ለምሳሌ፡- አሁን ያለንበት የቴክኖሎጂ ደረጃ ከ“4 ነጥብ 0” (አራተኛውን የኢንዱስትሪ አብዮት የሚገልፅ ፅንሰ ሀሳብ ነው) በላይ እያለፈ ነው፡፡ ቴክኖሎጂው ዘመኑን የዋጀ ሲሆን፤ ሰልጣኞችን የማብቃት አቅም ከማሳደጉም ባለፈ ሰልጣኞችም ጓጉተው እንዲሰለጥኑ የሚያደርግ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

ወይዘሮ ዳግማዊት እንደገለፁት፤ ሰልጣኞችን የሚያሰለጥኑበት መንገድ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ ነው፡፡ ተማሪዎች በዲጂታል መሣሪያዎች እና ዘመናዊ ላብራቶሪዎችን በመጠቀም እንዲማሩ ያደርጋል። ሌላው መለያው ከንድፈ ሀሳብ ይልቅ ተግባር ላይ ያተኩራል፡፡ ሰልጣኞች እንዲያውቁ ብቻ ሳይሆን መስራት እንዲችሉ በዎርክሾፕና በላብራቶሪ የተግባር ስልጠና ያገኛሉ። በተጨማሪም የሚሰጠው ሙያና ክህሎት የኢንዱስትሪዎችንና የወቅቱን የገበያ ፍላጎት በመመርኮዝ የሚዘጋጅ ነው። አሁን ላይ ዓለም ከዲጂታል ቴክኖሎጂ ጋር የተያያዘ ስለሆነ ከሙያ እውቀት ጎን ለጎን የዲጂታል ክህሎትንም የሚያጠናክር ነው። በስልጠናው ወቅት ሰልጣኞችን ከኩባንያዎችና ከኢንዱስትሪዎች ጋር ትስስር በመፍጠር የስራ ቦታን በተግባር እንዲያውቁ የሚያደርግ አቀራረብ ነው የሚኖረው፡፡

## ለቴክኒክና ሙያ ዘርፉ የሚፈጥረው ተጨማሪ አቅም

ስማርት ኮሌጁ እነዚህን ልዩ የሚያደርጉትን መስፈርቶች አሟልቶ የሚገኝ በመሆኑ እንደ ልህቀት ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፡፡ በዘርፉ ከበቂ ጣሊያን፣ ጀርመን፣ አውስትራሊያ... ሀገራት የሚመጡ ባለሙያዎች የአሰልጣኞች አሰልጣኝ ሥልጠና እንዲሰጡ ይደረጋል። በዚህም የሰልጣኞችን ሙሉ አቅም በመገንባት ቴክኒክና ሙያ ይበልጥ ተመራጭ እንዲሆን ለማድረግ ይሰራል። ብዙ ያደጉ ሀገራት የእድገታቸው ምንጭ የቴክኒክና ሙያ ዘርፍን እንደ አቅም መጠቀማቸው ነው፡፡ “ኢትዮጵያን ወደተሻለ እድገት ደረጃ ለማሻገር ቴክኒክና ሙያ የጀርባ አጥንት ሆኖ ኢንዱስትሪውን እንዲያሻግር የማድረግ ስራ መሰራት አለበት” በሚል እየተሰራ እንደሆነ ወይዘሮ ዳግማዊት ያስረዳሉ።

በአዲስ አበባ ከተማ ያሉ 15 ፖሊ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆችን ወደ ስማርት ደረጃ ለማምጣት ራሳቸውን አዘምነው እና የስልጠና አገልግሎታቸውን በቴክኖሎጂ እንዲታገዝ አድርገው እየሰጡ ቢሆንም በሚፈለገው ልክ ባለመሆኑ የነበረውን ችግር ለመፍታት ኮሌጁ የሚኖረው ፋይዳ የላቀ ነው፡፡

“ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች ወደ ዘመናዊ ምዕራፍ መሻገር አለባቸው” የሚሉት ወይዘሮ ዳግማዊት፣ ስልጠናውን ማዘመን ካልተቻለ ከተማዋን ወደሚፈለገው ስማርት ከተማ ማሻገር አይቻልም፡፡ ለምሳሌ፡- ስለ ስራ እድል ፈጠራ ሲወራ ደረጃውን በጠበቀ ሁኔታ ያልሰለጠነና ያልበቃ ሰልጣኝ ገበያውን መሸከም አይችልም፡፡ ስለዚህ ሁሉም ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች ስማርት የሚሆኑበትና ዕርስ በዕርሳቸው ተናብበውና ተባብረው

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

# ማስታወቂያ




አመልካች ካፒቴን ሳምሶን ሀዲስ ተድላ ስም የተመዘገበ ነዋሪነቴ በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 አያት ዞን 2 መንገድ 10 የቤት ቁጥር 2/19/2/ ነዋሪ ሲሆን የቤት ካርታ ስለጠፋብኝ ካርታ ቁጥር ቦሌ10/4/8/1/0623/670/01 ማረጋገጫ ካርታ ስለጠፋብኝ ሌላ ካርታ ምትክ እንዲሰጠኝ በማለት ያቀረቡ በመሆኑ ካርታ የጠፋ መሆኑን በማመልከቻ ያሳወቁን ስለሆነ ይዞታ ቤቱን በዕዳ ይዤዋለሁ፤ አስይዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለተቋሙ እንዲያሳውቁን እያልን በዚህ ምክንያት ለ30 ቀናት የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገበት በኋላ ሀላፊነት የምንወስድ ይሆናል፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ከአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 12 የቤት ቁጥር 158 የይዞታ ካርታ ቁጥር ወ11/ውዝ01/123/7069/00፤ ሴሪ ቁጥር 002001 የሆነው በሽፈራው ነጋሽ ስም የተመዘገበው የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) እንደጠፋባቸው በቀን 03/13/2018 ዓ/ም ያመለከቱ ሲሆን ይሁንኑን የይዞታ ካርታ ይዤዋለሁ (አግኝቼዋለሁ) የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ በ 30 ቀናት ውስጥ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ ቅ/ፅ/ቤት ማቅረብ የሚችል ሲሆን ይህ የማይሆን ከሆነ ግን ምትክ የማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

በአዲስ አባበ ከተማ አስተዳደር በጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 01 የካርታ ቁጥር 1/71/379929/01 ሴሪ ቁጥር 051321 የተሰጠበት ቀን 12/06/2010 ዓ.ም በእነ መስታወት ከበደ ወልደኪዳን ስም ተመዝግቦ የሚገኝ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ወይም ሰርተፊኬት ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት ይዤዋለሁ ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት (አንድ ወር) ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረበ በምትኩ ሌላ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ወይም ሰርተፊኬት የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ጉለሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ክልል ውስጥ የሚገኝ በካርታ ቁጥር የካ/22616/13 ሴሪ ቁጥር 151899 አለምፀሃይ አለሙ መንገሻ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ የኮንደሚንየም ቤት ማህደር ከለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በማህደር ክፍላችን ተፈልጎ ባለመገኘቱ ማህደራቸውን ተደራጅቶ በመመሪያ መሠረት ለማስተናገድ በሂደት ላይ ስለሆንን ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ በ 30 ቀናት ውስጥ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ተቃውሞውን እንዲያቀርብ እያሳሰብን፣ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ተቃውሞ የማያቀርቡ ከሆነ በምትኩ በመመሪያው በሚፈቅደው መሠረት ተገቢውን ምላሽ የምንሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ ዳንኤል አባዲ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 03 ይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000060300576 ሴሪ ቁጥር L 059323 የሆነው በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ/ ይዤዋለሁ የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የቦሌ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ክልል ውስጥ የሚገኝ በካርታ ቁጥር ቦሌ/15/63/8/4/58538/00 ሴሪ ቁጥር 1563937 ቅድስት ኃይለማርያም ሽፈራው ስም ተመዝግቦ የሚገኝ የኮንዶሚንየም ቤት ማህደር ከለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በማህደር ክፍላችን ተፈልጎ ባለመገኘቱ ማህደራቸውን ተደራጅቶ በመመሪያ መሰረት ለማስተናገድ በሂደት ላይ ስለሆንን ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ ከ30 ቀናት ውስጥ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ተቃውሞውን እንዲያቀርቡ እያሳሰብን፣ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ተቃውሞ የማያቀርቡ ከሆነ በምትኩ በመመሪያው በሚፈቅደው መሠረት ተገቢውን ምላሽ የምንሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት**

---

በእነ እጨልቱ ገሜሳ (ሁለት ሰዎች) አድራሻው በልደታ ክ/ከተማ ወረዳ 07 የቤት ቁጥር 885 ይዞታ መለያ ቁጥር AA000030700227 ሴሪ ቁጥር R032603 የጠፋባቸው በመሆኑ በጋዜጣ ታውጆ አገልግሎት እንዲሰጣቸው አመልክተዋል፡፡ በመሆኑም በጠየቁት መሰረት የምትክ ካርታ አገልግሎት ለመስጠት ያመች ዘንድ ከላይ በተጠቀሱት ካርታ ቁጥሮች እና በባለጉዳዮቹ ስም የተመዘገበውን የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት /ኦርጂናል ካርታም ሆነ ኮፒውን/ ይዤዋለሁ የሚል ማንኛውም አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ልደታ ክ/ከተማ የመሬት ይዞታ ሙብት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ካልቀረበ በመመሪያ ቁጥር 61/2010 አንቀጽ 72 ንኡስ አንቀጽ 3 መሰረት በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ ሙብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ልደታ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

# በመዲናችን የተዘጋጁ የኪነ ጥበብ መሰናዶዎች

**በአብርሃም ገብሬ**

ባሳለፍነው ሳምንት በመዲናችን አዲስ አበባ የተለያዩ ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች ለጥበብ አፍቃሪያን ሲደርሱ ቆይተዋል። ዛሬን ጨምሮ በሚቀጥሉት ቀናትም መሰል መሰናዶዎች ይቀርባሉ፡፡ ከእነዚህ ኪነ ጥበባዊ መሰናዶዎች መካከል የመጽሐፍ ውይይት፣ የመጽሐፍ ምርቃት፣ የሙዚቃ ዝግጅት፣ የስዕል አውደ ርዕይ እና የቴአትር መርሃ ግብር ይገኙበታል። ለመረጃ ይሆንዎት ዘንድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል እንደሚከተለው አዘጋጅቷቸዋል፡፡

### መጻሕፍት

ዛሬ በደራሲ ቤተማርያም ተሾመ መጽሐፍ ላይ ውይይት ይደረጋል፡፡ የደራሲው የመጨረሻ መጽሐፍ በሆነው “ቡናዬ እስኪሰክን” መጽሐፍ ላይ ዛሬ ከ8:00 ሰዓት ጀምሮ ነገረ ውይይት ይደረጋል፡፡ በውይይት መድረኩ ላይ ደራሲ ቤተማርያም ተጋባዥ እንግዳ ሆኖ ይቀርባል፡፡ የመጽሐፍ ውይይቱ አዘጋጅና አቅራቢ ደራሲ እንዳለጌታ ከበደ ሲሆን፣ ዛጎል የመጻሕፍት ባንክ ዝግጅቱን አሰናድቶታል፡፡ የመጽሐፍ ውይይት የሚካሄድበት የዝግጅት ቦታ የማህበራዊ ጥናቶች መድረክ (Forum for Social Studies-FSS) ሕንጻ፣ አንደኛ ፎቅ ላይ ይሆናል፡፡ በዝግጅቱ ላይ በአካል በመገኘት መሳተፍ የምትፈልጉ የጥበብ አፍቃሪያን ቀበና ካቶሊክ ኪዳነምሕረት ቤተ ክርስቲያን አቅራቢያ፣ ወደ ሳንፎርድ ትምህርት ቤት በሚወስደው መንገድ፣ ባማ አዲስ ሕንጻ አጠገብ ይገኛል፡፡

ዛሬ የጋዜጠኛና ደራሲ እሸቴ አሰፋ “እነሆ መቆያ” የመጽሐፍ ፊርማ መርሃ ግብር ይደረጋል፡፡ ከቀኑ 8:00 ሰዓት ጀምሮ በጃዕፈር መጽሐፍ መደብር የሚካሄደው የመጽሐፍ ፊርማ መርሃ ግብር ላይ ደራሲና ጋዜጠኛ እሸቴ አሰፋ ይገኛል፡፡ በመርሃ ግብሩ ከደራሲው ጋር የፎቶና የመጽሐፍ ፊርማ ይኖራል፡፡ መርሃ ግብሩ የተሰናዳው ለገሃር፣ ተወልደ ሕንጻ ስር በሚገኘው አዲሱ ጃዕፈር መጻሕፍት መደብር ውስጥ ነው፡፡

ታዋቂ የቴአትር ምሁርና ተዋናይ በነበሩት ተባባሪ ፕሮፌሰር ተስፋዬ ገሰሰ ሕይወት ላይ የሚያተኩረው የሕይወት ታሪክ መጽሐፍ ሊመረቅ ነው፡፡ “ተስፋዬ ገሰሰ ጉምቱ የጥበብ ባለሟል” በሚል ርዕስ፣ በደራሲና ጋዜጠኛ ደረጀ ትዕዛዙ የተጻፈው የሕይወት ታሪክ መጽሐፍ የፊታችን ሐሙስ መስከረም 14 ቀን፣ 2019 ዓ.ም ይመረቃል፡፡ ምርቃቱ የሚደረገው በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር ቤት ሲሆን፣ ከቀኑ 8:30 ሰዓት ጀምሮ የተለያዩ ታዋቂ የጥበብ ሰዎች በተገኙበት በይፋ ይመረቃል፡፡ የጥበብ አፍቃሪያን በዚህ ዝግጅት እንድትገኙ ተጋብዛችኋል፡፡




ፎቶ :- ከገፀ ድር
ከመዲናዋ የጥበብ መሰናዶዎች በከፊል

### ሙዚቃ

አንጋፋው ሙዚቀኛ ግርማ በየነ የሙዚቃ ሥራዎቹን ሊያቀርብ ነው፡፡ ከ1960ዎቹ አንስቶ በሙዚቃ ሥራ ውስጥ የሚገኘው ሙዚቀኛ ግርማ በየነ የፊታችን ሐሙስ መስከረም 14 ቀን፣ 2019 ዓ.ም መስቀል አደባባይ በሚገኘው በፈንድቃ ባህል ማዕከል ሀያት ሪጀንሲ ሆቴል ውስጥ የሙዚቃ ሥራዎቹን ለአድናቂዎቹ ያቀርባል፡፡ ሌላኛው አንጋፋ ሙዚቀኛ ዳዊት ይፍሩ ግርማ በየነን በኪቦር ያጅበዋል፡፡ በዕለቱ እቴጌ የሴቶች ባንድም ሥራዎቻቸውን ያቀርባሉ፡፡ ዝግጅቱ ከምሽቱ 2:00 ሰዓት ይጀምራል፡፡ በቀጣይ ጊዜያት በመደበኛነት የሙዚቃ ሥራዎቹን ሐሙስ ቀን እንደሚያቀርብ ታውቋል፡፡

### የሥነ ጥበብ አውደ ርዕይ

“ፍቅር እስከ መቃብር በስዕል” የተሰኘ አውደ ርዕይ በእይታ ላይ ይገኛል፡፡ የሰዓሊ ነጋልኝ ሉሌ የስዕል ስራዎች የቀረቡበት ይህ አውደ ርዕይ እስከ ፊታችን መስከረም 11 ቀን 2019 ዓ.ም እንደሚቆይ ተገልጿል። አውደ ርዕይው እየታየ የሚገኘው ሃያት ሪጀንሲ ሆቴል በሚገኘው ፈንድቃ የባህል ማዕከል ሲሆን መግቢያው በቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን በኩል በሚገኘው በር ነው፡፡

### የቴአትር መርሃ-ግብር

በመዲናችን አዲስ አበባ ቅዳሜ እና እሁድ የተለያዩ ቴአትሮች ይታያሉ። በብሔራዊ ቴአትር ቤት ቅዳሜ 7:30 ሰዓት “12ቱ እንግዶች” እንዲሁም በ11:30 “በር የሌለው ቤት” ቴአትሮች ይታያሉ። እሁድ ደግሞ በ7:30 ሰዓት “ንጉስ አርማሕ” እንዲሁም በ11:30 ደግሞ “እምዬ ብረቷ” ይታያሉ፡፡ ተመልካቾችም ጊዜያቸውን ለመቆጠብ የ“ሁሉ በጄ” መተግበሪያን በመጠቀም ትኬቶችን አስቀድመው መግዛት እንደሚችሉ ተገልጿል።

በአዲስ አበባ ቴአትርና ባህል አዳራሽ ደግሞ “እሳት ወይ አበባ” ዘወትር ቅዳሜ በ11:00 ሰዓት እንዲሁም “ባልቻ አባነፍሶ” ቴአትር እሁድ በ8:00 ሰዓት የሚታዩ ሲሆን ትኬቱን በኦንላይን የክፍያ ስርዓት መቁረጥ እንደሚቻል ተጠቁሟል፡፡

ቦሌ ፍላሚንጎ በህፃናትና ወጣቶች የቴአትርና ሲኒማ ኮምፕሌክስ እሁድ ጠዋት 4:00 ሰዓት “የንባብ ከተማ” የተሰኘው አዲስ የልጆች ቴአትር ለእይታ ይበቃል፡፡ እሁድ በ8:00 ሰዓት “ወህኒ አምባ ቴአትር” እንዲሁም 11:30 ሰዓት ደግሞ “አትጥሪኝ” የተሰኙ ቴአትሮች ለተመልካች ይደርሳሉ፡፡

እንዲሁም በሀገር ፍቅር ቴአትር ረዕቡ በ11:00 ሰዓት “አሉ” የተሰኘው አዲስ ቴአትር፣ ሐሙስ 11:30 ሰዓት “ነገሩ አይቆምም፣ እሑድ በ8:00 ሰዓት ሰዴታ (በአፋን ኦሮሞ) እና በ12:00 ሰዓት “የመጨረሻው ፍርድ” ለቴአትር አፍቃሪያን ይቀርባሉ፡፡

## የቁጥር ጨዋታ

### ያለፈው ጥያቄ መልስ

ውድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ አንባቢዎቻችን ባለፈው ሳምንት በልዩ ዕትም ምክንያት የጥያቄውን መልስ ባለማቅረባችን ይቅርታ እንጠይቃለን፡፡ የጥያቄው ትክክለኛ አሰራርና መልስ የሚከተለው ነው፡፡ የመጀመሪያው (5 + 11 + 4) - (3 + 1) = 20 - 4 = 16 ይሆናል። ሁለተኛው (14 + 9 + 9) - (6 + 8) = 32 -14 = 18 ነው፡፡ በዚህ መሰረት ሶስተኛው እና የመጨሻው (12 + 3 + 12) - (6 + 7) = 27 - 13 =14 ይሆናል። ስለዚህ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ የሚገባው ትክክለኛ ቁጥር **14** ነው፡፡




### የዚህ ሳምንት የቁጥር ጨዋታ

ውድ አንባቢዎቻችን ከታች በምስሉ ላይ የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችኋል፡፡ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛው ቁጥር ስንት ነው? በጥያቄው ራስዎን እየፈተኑ ይዝናኑ፡፡ የጥያቄውን መልስ በቀጣይ ሳምንት እትማችን ይዘን እንቀርባለን፡፡



# ወርቃማው የቱሪዝም ወቅት

በጊዜው አማረ

በአሁኑ ወቅት የቱሪዝም ዘርፍ የበርካታ ሀገራት ዋነኛ የኢኮኖሚ አቅም፣ ለዜጎችም ትልቅ የመዝናኛ፣ የስራ ፈጠራ እንዲሁም የገቢ ምንጭ እየሆነ ነው። ምክንያቱም ሰዎች አዳዲስ ባህሎችን ለማወቅ፣ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ መስህቦችን ለመጎብኘትና ከዕለት ተዕለት የስራ ጫና እረፍት ለማግኘት ወደ ተለያዩ ስፍራዎች ይጓዛሉ። ይህ የእንቅስቃሴ ፍላጎት መጨመር ደግሞ አገልግሎት ሰጪ ለሆኑ ተቋማት ትልቅ የንግድ እድል በመክፈት የኢኮኖሚ እንቅስቃሴውን በእጅጉ እያሳደገው ይገኛል።

በርካታ የዓለም ሀገራት የዚህን ዘርፍ ሁለገብ ጠቀሜታ በመረዳታቸው የቱሪዝም መዳረሻዎቻቸውን የማስፋትና የማሻሻል ስራ ላይ በከፍተኛ ትኩረት እየሰሩ ነው። ነባር ታሪካዊና ተፈጥሯዊ ቅርሶችን ከመንከባከብ ባለፈ፣ አዳዲስ ሰው ሰራሽ መስህቦችን በመገንባት፣ የትራንስፖርትና የሆቴል አገልግሎቶችን በማዘመን እንዲሁም ለጎብኚዎች ምቹና ደህንነቱ የተጠበቀ አካባቢ በመፍጠር ላይ ናቸው። ይህም አገራት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ሆነው እንዲቀጥሉ ያስችላቸዋል።



ግራፊክስ ፦ እዮብ ተፈራ
አዲስ አበባ ካከናወነቻቸውና ለቱሪዝም ዘርፉ ከፍተኛ ፋይዳ ከሚያስገኙ የልማት ስራዎች ጥቂቶቹ

የቱሪዝም መስፋፋት ከሚያስገኛቸው ቀጥተኛ የኢኮኖሚ ጥቅሞች በተጨማሪ በርካታና አዳዲስ የስራ እድሎችን የመፍጠር አቅም አለው። በሆቴል፣ በትራንስፖርት፣ በምግብ ዝግጅት፣ በቅርሳ ቅርስ ምርቶችና በአስጎብኚነት ዘርፎች ለሚሰማሩ ወጣቶችና የአካባቢው ማህበረሰብ አባላት የገቢ ምንጭ ይሆናል። በተጨማሪም ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በቱሪዝም እሴት ሰንሰለት ውስጥ በመሳተፍ የራሳቸውን ስራ እንዲፈጥሩና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነታቸውን እንዲያረጋግጡ ትልቅ መንገድ ይከፍታል። ለዚህም የዓለም የቱሪዝም ቀን በየዓመቱ መስከረም 17 (በፈረንጆቹ 27) ይከበራል፡፡

እለቱ የሚከበረው የዓለም አቀፉ የቱሪዝም ድርጅት ህግና ደንብ በፈረንሳይ እ.ኤ.አ. በ1970 የፀደቀበትን ታሪካዊ ቀን ለማሰብ ነው። በዓሉ ለመጀመሪያ ጊዜ በ1980 መከበር የጀመረ ሲሆን ዋና ዓላማውም የቱሪዝም ዘርፍ ስለሚያበረክተው ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ እሴት ማህበረሰቡ ያለውን ግንዛቤ ለማሳደግና ለማስገንዘብ ነው።

ይህ ቀን ቱሪዝም በሀገራት መካከል ያለውን ግንኙነትና ሰላም ለማጠናከር እንዲሁም የባህል ትውውቅን ለማሳደግ ያለውን ሚና አጉልቶ ያሳያል። በተጨማሪም የቱሪዝም ልማት የአካባቢ ጥበቃን ባገናዘበና የተፈጥሮ ሀብቶችን ሳይጎዳ ዘላቂ በሆነ መንገድ እንዲካሄድ የማንቂያ ደወል በመሆን ያገለግላል። ጎብኚዎች አዳዲስ ባህሎችንና ታሪኮችን እንዲረዱ በማድረግም የጋራ መከባበርን፣ እህትማማችነትን እና ወንድማማችነትን ያጎለብታል።

በሌላ በኩል ቀኑ የቱሪዝም ዘርፍ ለዓለም አቀፍ ኢኮኖሚ፣ ለስራ እድል ፈጠራና ለድህነት ቅነሳ ለሚያበረክተው አስተዋጽኦ ትኩረት ለመስጠት ይውላል። መንግስታት፣ የዘርፉ ባለድርሻ አካላትና የዘርፉ ባለድርሻዎች የቱሪዝም መሠረተ ልማቶችን ለማስፋፋት፣ አዳዲስ የቴክኖሎጂ አሰራሮችን ለመተግበርና የቱሪዝም መዳረሻዎችን ዘላቂነት ባለው መልኩ ለማልማት ያላቸውን ቁርጠኝነት የሚያሳዩበት አጋጣሚም ነው፡፡

ይህ ቀን በመስከረም ወር መከበሩ ለኢትዮጵያ ልዩና ጥልቅ ትርጉም አለው። መስከረም ለሀገራችን የመታደስ፣ የምድር አረንጓዴነትና የብርሃን ወር እንደመሆኑ አዳዲስ ተስፋዎች የሚፈነጥቅበት ወቅት ነው። ክረምቱ አልፎ ሰማይ የሚጠራበት፣ አበቦች የሚያብቡበትና ወንዞች የሚጎድሉበት በመሆኑ፣ ለሀገር ውስጥና ለውጭ ሀገር ቱሪስቶች ተንቀሳቅሶ ለመጎብኘት እጅግ አመቺና ማራኪ ሁኔታን ይፈጥርላቸዋል።

በዚህ ወር የሚከበሩት ታላላቅ በዓላት የኢትዮጵያን የቱሪዝም እንቅስቃሴ በከፍተኛ ደረጃ ያደምቁታል። በወሩ መጀመሪያ የሚከበረው የዘመን መለወጫ (እንቁጣጣሽ)፣ በመቀጠል በታላቅ ድምቀት የሚከበረው የመስቀል ደመራ እና የኢሬቻ በዓላት ሀገሪቱን የቱሪዝም ማዕከል ያደርጓታል።

> ኢትዮጵያ የገነባቻቸው የመሰረተ ልማትና የቱሪስት መዳረሻ ስፍራዎች ሀገሪቱን ቀዳሚ የጎብኚዎች ምርጫ የሚያደርጓት ናቸው። አሁን የሚጠበቀው ይህንን ትልቅ ስራ በትክክለኛው መንገድ ለዓለም ማስተዋወቅ ነው

ኢትዮጵያ በቱሪዝም ዘርፍ የምታስመዘግበውን ሁለገብ ጠቀሜታ ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር ባለፉት ጥቂት ዓመታት ዘርፈ ብዙና አዳዲስ ፕሮጀክቶችን ስትሰራ ቆይታለች። ከእነዚህም መካከል ነባር ታሪካዊና ባህላዊ ቅርሶችን ጠብቆ ለማቆየት የተሰሩ ሰፊ የማደስ ስራዎች እንዲሁም በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የተፈጥሮ ሥነ-ምህዳርን ያገናዘቡ የኮሪደርና የኢኮ-ቱሪዝም ልማት ስራዎች ተጠቃሾች ናቸው ይላሉ፤ የቱሪዝም ጉዳዮች ከፍተኛ ተመራማሪና አማካሪ አያሌው ሲሳይ (ዶ/ር)። እነዚህ ስራዎች የሀገሪቱን የተፈጥሮ ውበትና ታሪካዊ እሴት ሳይበርዙ፣ ለዘመኑ የቱሪዝም ፍላጎት ምቹና ማራኪ አድርገው ለመቅረፅ ትልቅ መሰረት ጥለዋል፡፡ በዚህ ረገድ የመዲናችን አዲስ አበባ ሽግግር እጅግ አስደናቂ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የከተማ ዲዛይንና ፕላን ተባባሪ ፕሮፌሰር ዳንኤል ሊሬቦ (ዶ/ር) በበኩላቸው ከተማዋ ቀደም ሲል ለቱሪስቶች ወደ ሌሎች ክልሎችና መስህቦች ለመሸጋገር እንደ ጊዜያዊ ማረፊያ (Transit) ብቻ ታገለግል ነበር፡፡ አሁን ግን በርካታ ቀናትን የሚያስቆዩ ድንቅ መስህቦች ባለቤት ሆናለች ሲሉ ለዝግጅት ክፍላችን ሃሳባቸውን ሰጥተዋል፡፡

የአዲስ አበባ የኮሪደር ልማት ፕሮጀክት ከተማዋን ውብና ዘመናዊ በማድረግ ለቱሪዝም ዘርፉ ማደግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከተ ይገኛል። መንገዶች ማስፋታቸው፣ እግረኛ መንገዶች መመቻቸታቸው፣ አረንጓዴ ቦታዎች መልማታቸውና የምሽት መብራቶች መገንባታቸው ከተማዋ ለጎብኚዎች ምቹና ሳቢ እንድትሆን አድርጓታል። ይህም ቀደም ሲል አዲስ አበባን እንደ መሸጋሪያ (Transit) ብቻ ይጠቀሙ የነበሩ የውጭ ሀገር ቱሪስቶች በመዲናዋ ውስጥ ረጅም ጊዜ እንዲቆዩና እንዲዝናኑ ትልቅ እድል ፈጥሯል ብለዋል።

ከዚህም ባሻገር የኮሪደር ልማቱ አዲስ አበባ የያዘቻቸውን ታሪካዊና ባህላዊ እሴቶች ከዘመናዊ መሰረተ ልማቶች ጋር በማጣመር ልዩ ውበት እንዲላበሱ አድርጓቸዋል። የታሪካዊ ህንፃዎች መታደስ፣ የጎዳና ላይ ጥበባት፣ የፋውንቴኖችና የህዝብ መዝናኛ አደባባዮች መስፋፋት የከተማዋን የታሪክና የባህል ገጽታ በጥሩ ሁኔታ አጉልተውታል። ይህም የሀገር ውስጥና የውጭ ጎብኚዎች በነፃነት ተንቀሳቅሰው የከተማዋን ልዩ ባህል፣ ውበት እና ድምቀት እንዲለማመዱ ሰፊ እድል ፈጥሯል።

የቱሪዝም ጉዳዮች ከፍተኛ ተመራማሪና አማካሪ አያሌው ሲሳይ (ዶ/ር)፣ እንደ ወዳጅነት አደባባይ፣ እንጦጦ እና አንድነት ፓርኮች፣ የቀበና ወንዝ ዳርቻ ልማት፣ በአትላስ አካባቢ የተሰራው ልማት እና እንደ የዓድዋ ድል መታሰቢያ ያሉ ግዙፍ ፕሮጀክቶች መገንባታቸው አዲስ አበባን ተመራጭ የቱሪዝም መዳረሻ እንድትሆን አድርገዋታል ሲሉ ሃሳባቸውን አጋርተዋል፡፡

መዲናዋ ከዚህ ዘርፍ ተጠቃሚ እንድትሆን የማስተዋወቅ ስራው በዘመናዊ የዲጂታል ሚዲያ ቴክኖሎጂዎች፣ በመገናኛ ብዙሃን እንዲሁም በዓለም አቀፍ የቱሪዝም ኤግዚቢሽኖች ላይ በስፋትና በተቀናጀ መልኩ መስራትና ማስተዋወቅ ያስፈልጋል። የውጭ ሀገር ቱሪስቶችና በስደት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ወደ ሀገር ውስጥ ሲመጡ የት መሄድና ምን መጎብኘት እንዳለባቸው ግልጽ መረጃ የሚያገኙበትን መንገድ ማመቻቸት አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም አስተዋዋቂዎች የሚያደርጉት ጥረት የቱሪስቶችን ፍሰት በመጨመር ለሀገሪቱ የውጭ ምንዛሬን ያመጣል፤ ለአካባቢው ማህበረሰብም ሰፊ የስራ እድል በመፍጠር የኢኮኖሚ እድገቱን ያፋጥነዋል። በመሆኑም አዳዲስ ፕሮጀክቶችን በቱሪዝም መዳረሻ ዝርዝራቸው ውስጥ የማካተት እና በዲጂታል ሚዲያ የማስተዋወቅ ስራ በመስራት ላይ እንደሚገኙ አዲስ ልሳን በተለያየ ጊዜ ያነጋገረቻቸው አስጎብኚዎች ገልጸዋል፡፡

በአጠቃላይ ኢትዮጵያ ያከናወነቻቸውና እያከናወነቻቸው ያሉ የመሰረተ ልማትና የቱሪስት መዳረሻ ስፍራዎች ሀገሪቱን ቀዳሚ የጎብኚዎች ምርጫ የሚያደርጓት ናቸው። አሁን የሚጠበቀው ይህንን ትልቅ ስራ በትክክለኛው መንገድ ለዓለም ማስተዋወቅ ነው። በመሆኑም የዘርፉ ባለድርሻ አካላት፣ አስጎብኚ ድርጅቶች እና የመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎች የተሰሩትን አዳዲስና ነባር መስህቦች በስፋት ማስተዋወቅ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አርሶ አደር እና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# የከተማ ግብርና የበዓል ገበያውን የማረጋጋት ሚና

- **የከተማ ግብርና የምርት አቅርቦትን በማሳደግ በበዓላት ወቅት የሚከሰተውን የዋጋ ንረት በመግታት ገበያን የማረጋጋት አስተዋጽኦ እያበረከተ እንደሚገኝ ተገልጿል**

**በይግለጡ ጓዴ**

በዓለም አቀፍ ደረጃ ፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገትና የከተሜነት መስፋፋት በግብርና ምርቶች ፍላጎትና አቅርቦት መካከል ክፍተት እንዲፈጠር አድርጓል። ከገጠር አካባቢዎች የሚጓጓዙ የግብርና ምርቶች በረጅም የትራንስፖርት መስመር፣ በደላሎች ጣልቃ ገብነትና በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት ለከፍተኛ የዋጋ ንረትና ለጥራት መጓደል ይዳረጋሉ። ይህንን ፈተና ለመቋቋም 'የከተማ ግብርና' አቅርቦትን በቀጥታ በከተሞች ውስጥ በማምረት፣ የትራንስፖርት ወጪን በመቀነስ፣ የሸማችና አምራች ትስስርን በማጠናከርና ገበያን በማረጋጋት ረገድ ዓለም አቀፋዊ ወሳኝ መፍትሔ ሆኖ አገልግሏል።

በዚህ ዘርፍ የተሳካላቸው በርካታ የዓለም ከተሞች የከተማ ግብርናን በመተግበር ዘላቂ ጥቅም አግኝተዋል። ለምሳሌ የኩባ ከተማ ሃቫና ባካሄደችው የከተማ ግብርና ንቅናቄ 90 በመቶ የሚሆነውን የአትክልትና ፍራፍሬ ፍላጎቷን በከተማዋ ውስጥ በማምረት የምግብ ዋስትናዋን አረጋግጣለች። የሲንጋፖር ከተማ ሲንጋፖር ደግሞ በቴክኖሎጂ የተደገፈ የከተማ ግብርናን በመተግበር ውስን መሬቷን ተጠቅማ የምርት አቅርቦቷን በማሳደግ የገበያ አለመረጋጋትን በብቃት ተቆጣጥራለች። ሁለቱም ከተሞች በምግብ አቅርቦት እጥረት ሳቢያ የሚፈጠርን የዋጋ ንረት በመግታት፣ የአካባቢ ጥበቃን በማጠናከርና ለዜጎቻቸው የሥራ ዕድል በመፍጠር ረገድ ከፍተኛ ተሞክሮ አስመዝግበዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን በከተማዋ የሚስተዋለውን የኑሮ ውድነት ለመቀነስ ሰፊ እንቅስቃሴ እያደረገ ይገኛል። በተለይ በመስከረም ወር ለሚከበሩት ለአዲስ ዓመት፣ ለመስቀል እና ለኢሬቻ በዓላት የሚኖረውን ከፍተኛ የምርት ፍላጎት ታሳቢ በማድረግ እንቁላል፣ የዶሮና የሰብል ምርቶችን፣ የወተት ተዋጽኦዎችንና የአትክልትና ፍራፍሬዎችን በየክፍለ ከተማው በስፋት ለገበያ በማቅረብ ላይ ነው። ይህም አቅርቦቱ ሳይቋረጥ ለሸማቹ በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲደርስ በማድረግ የበዓላትን የገበያ ግብይት ያረጋጋና የነዋሪውን ኢኮኖሚያዊ ጫና በእጅጉ ያቃለለ አዎንታዊ አስተዋፅኦ እያበረከተ ይገኛል።



ፎቶ፡- ከገጾ ድር
በመስከረም ወር የሚከበሩ በዓላትን ታሳቢ በማድረግ ከፍተኛ መጠን ያለው የከተማ ግብርና ምርቶች ለገበያ ቀርበዋል

በዓላት በመጡ ቁጥር በማኅበረሰቡ ውስጥ ትልቅ ደስታና የመገናኘት ጉጉት መፈጠሩ የተለመደ ቢሆንም፣ ከዚሁ ጎን ለጎን የዕለት ተዕለት የፍጆታ ምርቶች ፍላጎት በከፍተኛ ሁኔታ ማናሩ ግን አይቀሬ ነው። ይህ የፍላጎት መጨመር በተለይም በአትክልት፣ ፍራፍሬ፣ ዶሮ፣ እንቁላልና ወተት ምርቶች ላይ ግልጽ የሆነ የዋጋ ንረትን ያስከትላል። የከተማ ግብርና ምርት የከተማዋን ከፍተኛ የፍጆታ ፍላጎት በመሙላት እና ገበያን በማረጋጋት ረገድ እገዛው የጎላ ነው፡፡

በየካ ክፍለ ከተማ የአርሶ አደርና የከተማ ግብርና ልማት ጽህፈት ቤት ኃላፊ ወይዘሮ መሰረት መካሻ እንደገለጹት፤ በከተማ ግብርና በራስ አቅም በማምረት ለበዓላት የተለያዩ ምርቶች ለገበያ ቀርበዋል። ከቀረቡት ምርቶች መካከል 1 ሚሊዮን 52 ሺህ 450 እንቁላል፣ 125 ሺህ 340 የሥጋ ዶሮ፣ 352 በግ፣ 185 በሬ፣ 15 ሺህ ኪሎ ግራም ሽንኩርት፣ 4 ሺህ 500 ኪሎ ግራም ቲማቲም፣ 120 ኩንታል ጤፍ እና 1 ሺህ 100 ኪሎ ግራም ቃሪያ ይገኙበታል። እነዚህ ምርቶች ከአዲስ ዓመት ጀምሮ እስከ መስከረም ወር መጨረሻ ድረስ በራስ አቅም ተመርተው ለህብረተሰቡ የቀረቡ ናቸው።

በቦሌ ክፍለ ከተማ አስተዳደር የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ጽህፈት ቤት የመስኖ ባለሙያ አቶ ያዕቆብ ቦንጋ በበኩላቸው፣ ለ2019 አዲስ ዓመት ባዛርና የበዓል ገበያ በከተማ ግብርና የተመረተ የግብርና ምርት እጥረት እንዳይኖርና ህብረተሰቡ ለበዓል የሚፈልገውን ምርት በአቅራቢያው እንዲያገኝ መደረጉን ገልጸዋል። ይህም የተረጋጋ የበዓል ገበያ ግብይት እንዲኖር አስችሏል። ለበዓላቱ በጣም ተፈላጊ የሆኑ ምርቶች በተመጣጣኝ ዋጋ በስፋት እየቀረበ እንደሚገኝ የተናገሩት አቶ ያዕቆብ፣ 295 ሺህ እንቁላል፣ 4 ቶን የዶሮ ሥጋ፣ 1 ቶን የትልልቅ እንስሳት ሥጋ፣ 700 ኪሎ ግራም አይብ፣ 295 ቶን ሽንኩርት፣ 39 ነጥብ 9 ቶን ቲማቲም እና 190 ኪሎግራም ብርቱካን የቀረበ ሲሆን እስከ በዓሉ መዳረሻም አቅርቦቱ ሳይቋረጥ የሚቀጥል መሆኑን ገልጸዋል።

የኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ አስተዳደር የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ጽህፈት ቤት የኑሮ ማረጋጋት ግብረ ኃይል በበኩሉ፤ የከተማ ግብርና ምርት አቅርቦት የአዲስ ዓመት፣ የመስቀል እንዲሁም የኢሬቻን በዓላት ታሳቢ በማድረግ የተለያዩ የከተማ ግብርና ምርቶችን በጽህፈት ቤቱ መረጃ መሠረት ለ2019 አዲስ ዓመት 2 ነጥብ 5 ሚሊዮን እንቁላል፣ 125 ቶን የዶሮ ሥጋ፣ 206 ቶን የትልልቅ እንስሳት ሥጋ፣ 911 ሺህ 620 ሊትር ወተት እና 153 ቶን የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ቀርቧል።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ሥር የሚገኘው የእንስሳት ልማትና ልህቀት ማዕከል፣ በዓላትን ምክንያት በማድረግ የገበያ ዋጋን ለማረጋጋት የእንስሳትና የእንስሳት ተዋጽኦ ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ለህብረተሰቡ እያቀረበ ይገኛል። የማዕከሉ ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ አሌክስ ደመቀ እንደገለጹት፣ ማዕከሉ አርሶ አደሮችን ለማቋቋም፣ የሥራ ዕድል ለመፍጠርና ገበያን ለማረጋጋት ዓላማ አድርጎ የተቋቋመ ነው። በአሁኑ ወቅት የደለቡ በሬዎችንና የእንስሳት ተዋጽኦዎችን በማዕከሉና በተለያዩ ቦታዎች በማቅረብ ላይ እንደሚገኝም ተናግረዋል። በተጨማሪም በዓሉን ምክንያት በማድረግ በተዘጋጁ ባዛሮች ላይ ከ350 ሺህ በላይ እንቁላል ማቅረቡን ጠቅሰው፣ ይህም አቅርቦት ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አረጋግጠዋል።

በማዕከሉ የተሰማሩ አምራቾች በበኩላቸው መንግሥት ባመቻቸላቸው ዕድል ተጠቅመው ምርቶቻቸውን በተመጣጣኝ ዋጋ እያቀረቡ መሆናቸውን ገልጸዋል። የእንቁላል አምራቿ አበራሽ ንጉሤ ምርታቸውን በተመጣጣኝ ዋጋ ለህብረተሰቡ እያቀረቡ እንደሚገኝ የገለጹ ሲሆን፣ የወተት ተዋጽኦ አምራቿ ወይዘሮ የሺወርቅ ዳኛቸው በበኩላቸው እንደ ቅቤና አይብ ያሉ ምርቶችን በቅናሽ ዋጋ ለህብረተሰቡ በማቅረብ ላይ እንደሆኑ ተናግረዋል። ማዕከሉ ከተቋቋመበት ከ2015 ዓ.ም መጨረሻ ጀምሮ በእንቁላል ጣይ ዶሮ እርባታ፣ በእንስሳት ማድለብና በወተት ላም እርባታ ላይ ትኩረት አድርጎ በመስራት ላይ ይገኛል።

በአርሶ አደርና የከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን የኮሚኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ወንድወሰን አካሌ፣ መጪውን የበዓላት ጊዜ ታሳቢ በማድረግ የእንስሳትና የአትክልት ምርት ለህብረተሰቡ በሁሉም ክፍለ ከተሞች ተደራሽ እየሆነ መሆኑን ገልጸዋል። አቶ ወንድወሰን እንደተናገሩት፣ የ2019 በጀት ዓመት የአዲስ ዓመት ዘመን መለወጫ በዓልን ምክንያት በማድረግ የህብረተሰቡን ፍላጎት ለማርካት የሚያስችል በቂ የከተማ ግብርና ምርት በሁሉም ክፍለ ከተሞችና ወረዳዎች ለገበያ እየቀረበ ነው።

የከተማ ግብርና የኑሮ ውድነትንና የዋጋ ንረትን ለመቋቋም የከተማዋ ነዋሪዎች በእጃቸው ላይ የሚገኝ ትልቅ መፍትሔ ነው። በበዓላት ወቅት የሚስተዋለውን የገበያ መናወጥ ለመግታት ይኸው የከተማ ግብርና ምርት በስፋት እንዲስፋፋ፣ ዘመናዊ የቴክኖሎጂ ግብዓቶች እንዲሟሉለትና ለዘርፉ ልዩ ትኩረትና ድጋፍ ሊሰጠው ይገባል።

# ልጆችና የአሸዋ ጨዋታዎች

**በፋንታነሽ ተፈራ**

ልጆች፤ እንዴት ናችሁ? አዲስ አበባ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየሰራቻቸው ያሉ የመዝናኛ ስራዎች እናንተንም ከግምት ያስገቡ እንደሆነ ከዚህ በፊት ባዘጋጀናቸው ጽሁፎች ላይ ሀሳባችሁን አጋርታችሁናል። በዛሬው ዕትማች ደግሞ የዚሁ አካል ስለሆነው በአሸዋ ወይም ሰው ሰራሽ ጭቃ ላይ ስለመጫወት እና ይህ የፈጠራ ስራን ምን ያህል እንደሚያሳድግ ሲጫወቱ ያገኘናቸውን ልጆች አስተያየት አካትተን እንደሚከተለው አቅርበነዋል፡፡



ፎቶ፡- በገነት ወንድሙ
ልጆች ቀበና በተሰራው ሰው ሰራሽ አሸዋ ላይ ሲጫወቱ

መሃመድ አብዱ እባላለሁ፡፡ 12 ዓመቴ ነው፡፡ ኳስ፣ ውሃ ዋና እንዲሁም አሸዋ እያቦካሁ እጫወታለሁ፡፡ ቀበና (የእንጦጦ-ቀበና የወንዝ ዳርቻ ልማት) በአሸዋ ለመጫወት ስመጣ ለሶስተኛ ጊዜ ነው። ይህን መጫወቴ ለመዝናናት፣ ችሎታዬን አውጥቼ ለማሳየት ጠቅሞኛል። ለምሳሌ የቤት ቅርፅ ሰርቻለሁ፡፡

ቤት በምሰራበት ወቅት ችግርን እንዴት መፍታት እንደሚቻል አስተምሮኛል። ቤቱን በአሸዋ ስሰራ ሲበላሽብኝ ወይም አልሳካ ሲለኝ አሸዋው ላይ ውሃ በመጨመርና እንዲያያዝ በማድረግ መፍትሄ ለመስጠት እሞክራለሁ። ያልተስተካከለውንም ለማስተካከል ምን ላድርግ በሚል በማደርገው ማሰላሰል የማሰብ ችሎታዬ ይዳብራል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በአዕምሮዬ የሳልኩትን ነገር በእጄ እንድሰራ በማድረግ የፈጠራ ችሎታዬን አዳብሮልኛል፡፡ ወደፊት ሃኪም የመሆን ህልም አለኝ፡፡ ለዚህም የሰው ምስል እየሰራሁ የተጎዳውን እግሩን እየቆረጥኩ፤ ሰው ሰራሽ እግር ነው እያልኩ አዲስ እግር እሰካለታለሁ፡፡ ይህ ደግሞ ህልሜን እውን እንዳደርግ ያግዘኛል፡፡

ሃና ፈይሰል እባላለሁ፡፡ 12 ዓመቴ ነው። ቀበና ስመጣ የሚያስደስተኝ ሰው ሰራሽ ጭቃ ማቡካት፣ መጫወት እንዲሁም መዝናናት ነው፡፡ የተበተነውን አሸዋ ቅርፅ ወዳለው ነገር መቀየር አስችሎኛል፡፡ ከምሰራቸው ቅርፃ ቅርፆች ውስጥ ልብ ቅርፅ፣ ቢራቢሮ እንዲሁም የአክሱም ሃውልት ይጠቀሳሉ። ከጓደኞቼ ጋር በመወዳደር ይህን እናደርጋለን፡፡ ይህ የመስራት ችሎታዬን ከማሳደጉም ባለፈ ተወዳድሮ ማሸነፍ እንደሚቻል አስተምሮኛል፡፡

ነፃነት ኖሮኝ እየሰራሁ፣ እያፈረስኩ፣ መቀየርና የፈለግኩትን መፍጠር ስለምችል ያለ ስጋት አዳዲስ ሀሳቦችን እንድሞክር አድርጎኛል፡፡ በተጨማሪም ልሰራው ያሰብኩት ነገር ካልተሳካ እንዴት ማስተካከል እንዳለብኝ ደጋግሜ እሞክራለሁ፡፡ ይህም በማንኛውም ስራ ላይ ተስፋ መቁረጥ እንደሌለብኝና ትዕግስተኛ እንድሆን ያደርገኛል፡፡ ብዙ ነገሮችን ስለምሞክር የችግር መፍቻ መንገዶችንም ለማግኘት ይረዳኛል፡፡

ዳዊት አወቀ እባላለሁ፡፡ 11 ዓመቴ ነው፡፡ ኳስ መጫወት ያስደስተኛል፡፡ ቀበና በመምጣት ሰው ሰራሽ ጭቃውን (አሸዋ) ላይ እጫወታለሁ፤ የተለያዩ ቅርፆችንም እሰራለሁ፡፡ ከወንድሜ ጋር በመሆን አሸዋውን በማገጣጠም አጥር ያለው ቤት ሰርተናል፡፡ አሸዋውን ሳነሳ፣ ስጨምቅ እንዲሁም ሳስተካክል የእጆቼን እና የጣቶቼን ጡንቻዎች ያጠነክርልኛል። አሸዋውን ወይም ጭቃውን ስነካካ አዕምሮዬ ይነቃቃል፡፡

የተለያዩ ስዕሎችን እስላለሁ። ፊደሎችን ትክክለኛ ቅርፃቸውን ለማስቀመጥ እጥራለሁ፡፡ የምፈልገው ምስል እስከሚሳካልኝ እያፈረስኩ እሞክራለሁ። ይህ የጀመሩትን ስራ ለመጨረስ መታገስ እንደሚያስፈልግ አስተምሮኛል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ መተባበር፣ መነጋገርና መግባባት እንደሚጠቅም አውቄበታለሁ።

በዚህ አሸዋ ትኩረቴን ሰብስቤ ስለምጫወት ሃሳቤን በአንድ ነገር ላይ እንዳደርግ፣ የምሰራውን ስራ በራሴ እንድወስን እና እንድተማመን ይጠቅመኛል ብዬ አስባለሁ፡፡ በአጠቃላይ እንድፈላሰፍና ወደፊትም የተለያዩ ነገሮችን መሞከር እንዳለብኝ ተረድቼበታለሁ፡፡

## የመስቀል ወፍ



በሀገራችን ልዩ ትኩረት የምንሰጠው የመስቀል ወፍ ማኅበረሰቡ በተለምዶ ከመስከረም ውጭ ባሉ ወራት ጠፍተው ቆይተው፣ በመስቀል ሰሞን ብቻ ከሩቅ አገር የሚመጡ (ስደተኛ ወፍ) ይመስሉናል። ነገር ግን የአእዋፍ ተመራማሪዎች እንደሚያስረዱት የመስቀል ወፎች ሁልጊዜም አብረውን ያሉ ናቸው፡፡ ነገር ግን በመስከረም ወር የሚከሰት አስደናቂ የተፈጥሮ ለውጥ (የላባ ቀለም መቀየር) ስለሚያደርጉ ከመስከረም ወርና ከመስቀል በዓል መግባት ጋር ተያይዘው የሚታወቁ ናቸው፡፡

አእዋፋቱ በስፋት ታይተው በበርካቶች ዐይን ውስጥ የሚገቡት የክረምቱ ወራት አብቅቶ የበጋው ወቅት በሚጀምርበት መስከረም ወር ላይ ነው። አእዋፋቱ በአብዛኛው ዘር በል በመሆናቸው በዚህ ወቅት ደግሞ የሚደርሱ ሰብሎች በስፋት የሚገኙበት እና ወፎቹም የሚራቡበት አመቺ ወቅት በመሆኑ በስፋት ይስተዋላሉ፡፡

ይህ ደግሞ ከመስቀል በዓል ጋር ተቀራራቢ በመሆኑ የተለየ ገጽታን ተላብሰው እንዲታዩ ያደርጋቸዋል።

ቀለማቸው እና ዝማሬያቸው ከአዲስ ዓመት እና ከመስከረም የፀሐይ ወቅት ጋር ተዳምሮ ከሚፈጠረው መልካም ስሜት ጋር የሁሉንም ቀልብ ስለሚስቡ ሁሉም ይመለከታቸዋል፡፡ በዚህ ሳቢያም አዲስ ወፍ የመስቀል ወቅትን ጠብቆ እንደመጣ ይታመናል።

የመስቀል ወፍ ብለን የምንጠራቸው አእዋፋት ከሌሎች ለየት የሚሉት ተባዕቶቹ በጣም ደማቅ ቀለም ሲኖራቸው፣ ሴቷ ግን ቡኒ ወይም ወደ ግራጫ የሚያደላ ቀለም ነው ያላት፡፡

በመሆኑም የመስቀል ወፎች ለረጅም ጊዜ ሳይታዩ ቆይተው መስከረም ወር ላይ የሚከሰቱ ዓመታዊ እንግዶች ሳይሆኑ አብረውን ቆይተው በተፈጥሮ ሂደት (የላባቸው ቀለም) የሚቀየር ቤተኛ አእዋፋት ናቸው ማለት ነው።

## 5 ልዩነቶችን ፈልጉ





## እንቆቅልሽ

### ያለፈው ሳምንት ጥያቄ

**ላዩ ሰርዶ ውስጡ ብርንዶ?**

**መልስ፡- ለ. ቀይ ሽንኩርት**

### የዚህ ሳምንት ጥያቄ

**ሊሰርቅ ሲመጣ በስውር፤ ሰርቆ ሲወጣ በግርግር**

ሀ. ሌባ
ለ. ሰርግ
ሐ. ሞት

**ልጆች፤ መልሱን ከጓደኞቻችሁ እና ከቤተሰቦቻችሁ ጋር ተወያዩበት።**

ከአዲስ አበባ ኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# አዲስ አበባ በስሉጥ ከተማነት መነፅር

**በደረጀ ታደሰ**

የመረጃና ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ (ICT) ፈጠራና ዕድገት እዚህ ደረጃ ከመድረሱ አስቀድሞ የነበረው የከተማነት ብያኔ፣ በዋናነት ሦስት መሰረታዊ መገለጫዎች ላይ የተመሰረተ ነው:: እነዚህም፡- ስነ-ሕዝባዊ እና ኢኮኖሚያዊ መገለጫዎች (Demographic & Economic)፣ መሠረተ-ልማትና አገልግሎት (Infrastructure & Services) እንዲሁም ማኅበራዊና ባህላዊ ብዝሃነት (Social & Cultural Diversity) ናቸው::

አሁን ላይ አንድ ከተማ የከተማነትን ብያኔ ወይም መመዘኛ ስላሟላ ብቻ ተመራጭ ሊሆን አይችልም:: ከተማ የተሟላ እና ተመራጭ ለመሆን ወደ ስሉጥ ከተማነት (Smart City) ማደግ ግድ ይለዋል:: ለዚህ ደግሞ ከተሞች የመረጃና ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂን (ICT)፣ የነገሮች ኢንተርኔት (IoT) እና የመረጃ ትንተናን (Data Analytics) በመጠቀም የሚሰጡትን አገልግሎቶች የሚያቀላጥፍ፣ የሃብት አጠቃቀምን የሚያሻሽል እና ለነዋሪዎች እና ለጎብኚዎች የሚመች የከተማ ልማት ስልት መተግበር እና ለውጤት ማብቃት ይኖርባቸዋል::

ከከተማነት ወደ ስሉጥ ከተማነት የሚደረግን ወሳኝ የዕድገት ምዕራፍ ውጤታማነት ለመረዳት እንደ ዙሪክ፣ አስሎ፣ ጀኔቫ፣ ሴውል፣ ሲንጋፖር የመሳሰሉትን ለመመልከት ሩቅ መሄድ አያሻም:: የኢትዮጵያ መዲና፣ የአፍሪካዊያን ከተማ፣ የዓለም ሦስተኛዋ ትልቅ የዲፕሎማሲ ማዕከል የሆነችውን የአዲስ አበባ ፈጣን ዕድገትና ለውጥ ማጤን በቂ ነው:: አዲስ አበባ አሁን ላይ የስሉጥ ከተማነትን ዓለም አቀፍ መመዘኛዎችን በተሻለ ጥራትና ብቃት እያሟላች ስለመገኘቷ ዓለም ራሱ ምስክርነት እየሰጠ ነው:: በደቡብ ኮሪያ በተካሄደው የሴውል ስማርት ሲቲ 2024 ምርጥ የአመራር ሽልማትን የአዲስ አበባ ከንቲባ አዳነች አቤቤ ማሸነፋቸው ለዚህ ማሳያነት የሚጠቀስ ነው::

## የአዲስ አበባ የስሉጥ ከተማነት ምሰሶዎች ምንነት

መዲናዋን ስሉጥ ከተማ እንድትሆን በጥናት ላይ የተመሰረተ ዕቅድ አቅዶ በቁርጠኝነት ተፈጻሚ እስከማድረግ የሚጠይቅ ሥራ ተሠርቷል፤ እየተሠራም ይገኛል:: ለሥራው ስኬታማነት ብዙዎች ተሳትፈዋል:: በተሳትፏቸው ወሳኝ ከሆኑ ተቋማት መካከል፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ አንዱ ነው:: ምክንያቱም በጥናት ላይ ተመስርቶ ወደ ተግባር እየተለወጠ ባለው የአዲስ አበባ የስሉጥ ከተማነት ዕቅድ ተፈጻሚነት ላይ ጉልህ ኃላፊነት ስላለው ነው:: በዚህ መነሻነት "አዲስ አበባን ስሉጥ ከተማ የማድረጉ ተግባር ተፈጻሚ እየሆኑባቸው ያሉ ቁልፍ ጉዳዮች ምንድን ናቸው?" የሚለውን ጥያቄ፤ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ምክትል ኃላፊ እና የስማርት ሲቲ ዘርፍ ኃላፊ ቱሉ ጥላሁን (ዶ/ር) ጋር ቆይታ አድርገናል::



ፎቶ፡- በገነት ወንድሙ
የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ምክትል ኃላፊ እና የስማርት ሲቲ ዘርፍ ኃላፊ ቱሉ ጥላሁን (ዶ/ር)

በአዲስ አበባ ከተማ እየተተገበረ ያለው የስሉጥ ከተማነት ዕቅድ ስድስት መሰረታዊ ምሰሶዎች ላይ ስለማተኮሩ ያብራሩት ቱሉ (ዶ/ር)፤ እነዚህም፡- ስማርት ኢኮኖሚ፣ ስማርት ኢንቫሮመንት (አካባቢ)፣ ስማርት ገቨርናንስ (አስተዳደር)፣ ስማርት ሊቪንግ (አኗኗር)፣ ስማርት ሞቢሊቲ (እንቅስቃሴ) እና ስማርት ፒፕል (ነዋሪ) መሆናቸውን ዘርዝረዋል:: የስማርት ሲቲ ልማት ውጤታማነት የሚረጋገጠው በጣም ውድ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን በብዛትና በዓይነት በመጠቀም ብቻ እንዳልሆነ፤ ይልቁንም በከተማዋ እና በነዋሪው ላይ የሚታዩ ችግሮችን (የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ፣ የመልካም አስተዳደር፣ የትራፊክ እንቅስቃሴ፣ የጽዳት፣ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም...) መፍትሄ ለመስጠት የሚያስችሉ የተለያዩ ቁልፍ ተግባራትን አቀናጅቶ መፈጸም ወሳኝ እንደሆነም ገልጸዋል::

የአዲስ አበባን ስሉጥ ከተማነት ለማረጋገጥ የተለዩ እና እየተፈጸሙ ያሉ ስድስት ዋና ዋና ምሰሶዎች እንደ ዓለም አቀፍ የደረጃዎች ድርጅት (ISO)፣ የተባበሩት መንግሥታት የዓለም አቀፍ ቴሌኮሙኒኬሽን ህብረት (ITU) እና መሰል ዓለም አቀፍ ተቋማት የታወቁና የተረጋገጡ ናቸው::

የከተማ አስተዳደሩ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ምክትል ኃላፊ እና የስማርት ሲቲ ዘርፍ ኃላፊ ቱሉ ጥላሁን (ዶ/ር) በአዲስ አበባ እየተተገበረ ባለው የስማርት ሲቲነት ጉዞ ውስጥ ትኩረት ከተደረገባቸው ስድስት ምሰሶዎች መካከል "ስማርት ኢኮኖሚ"ን በማስቀደም አብራርተዋል:: እንደሳቸው ገለጻ፤ ስማርት ኢኮኖሚ፤ የምርት ማሳደግ፣ የስርጭትና የፍጆታ ሂደትን ከሚያሳልጡ ቴክኖሎጂዎች ጋር የተማከለ ነው:: ከለውጡ ማግስት ባሉት ዓመታት በከተማዋ አራቱም በሮች የተገነቡትን ዘመናዊና ግዙፍ የግብርና ምርት ማከማቻና መሸጫ ማዕከላት በቴክኖሎጂ የተደገፈ አገልግሎት ለስማርት ኢኮኖሚ በምሳሌነት ይጠቀሳል:: በከተማዋ የተገነቡ እና እየተገነቡ ያሉ ግዙፍ እና ቴክኖሎጂን በአግባቡ የሚጠቀሙ እጅግ ዘመናዊ የገበያ ማዕከላትም የዚሁ አካል ናቸው:: የሸማች ሕብረት ሥራ ማህበራት የምርት አቅርቦት እና ስርጭት ሂደትን ለማዘመን የተደረገው ጥረትም የዚሁ ተጠቃሽ ነው::

የከተማዋን ከባቢያዊ ሁኔታ ንፁህ፣ ፅዱ፣ ውብ፣ ማራኪና ለኑሮ ተስማሚ ለማድረግ የሚሠራው ሥራ፤ በስማርት ሲቲ ልማት ሁለተኛው ምሰሶ "ስማርት ኢንቫሮመንት (አካባቢ)" የሚካተት መሆኑን ኃላፊው ጠቅሰዋል:: በኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አነሳሽነትና መሪነት ለዓመታት የቀጠለው የአረንጓዴ አሻራ ልማት መርሃ ግብር በከተማዋ ያለውን የአረንጓዴ ዕፅዋት ሽፋን በከፍተኛ ሁኔታ አሳድጎታል:: ከዚህ በተጨማሪም፤ በዋና መንገዶች ዳር እና ዳር እንዲሁም በመንገድ አካፋዮች፣ ከዚህ በፊት ባልነበሩ አዳዲስና ትላልቅ ፓርኮች፣ በአነስተኛና መካከለኛ መናፈሻዎች፣ በወንዝ ዳርቻ ልማት... የተተከሉ እና የለሙ የተለያዩ የዕጽዋት ዝርያዎች የስማርት ኢንቫሮመንት (አካባቢን) ምሰሶ በከተማዋ በተግባር ለመግለጥ ከተከናወኑ ውጤታማ ሥራዎች መካከል በማሳያነት ጠቅሰዋል::

"የስማርት ኢንቫሮመንት (አካባቢ)" መፈጠር፤ ከተማዋ ለነዋሪዎቿ እና ለእንግዶቿ የተመቸች እንድትሆን ከማድረጉ በተጓዳኝ፤ ከተጨናነቀ የአኗኗር ዘይቤ በመውጣት ራስን ማዳመጥ፣ ማንበብ፣ መወያየት፣ አዳዲስ ሃሳብ እና ፈጠራ ማፍለቅ ... የሚያበረታታ ዐውድን ያስገኛል:: እንደ አገር በርካታ ችግር ፈቺ አዳዲስ የምርምር፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ፈጠራዎችን ያሳድጋል" ያሉት ቱሉ (ዶ/ር)፤ የከተማዋን ፍሳሽ እና ደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ እና አስተዳደር ሥርዓት ለማሻሻል የዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ አቅም ጥቅም ላይ እየዋለ ስለመሆኑ አንስተዋል::

በከተማ አስተዳደሩ ሥር ያሉት የመንግስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት፤ ለህብረተሰቡ (ለተገልጋዮች) የሚያቀርቧቸው አገልግሎቶች ዘመናዊ፣ ቀልጣፋ፣ ፈጣን፣ ወጪ ቆጣቢ እና ፍትሐዊ ሊሆኑ ይገባል:: ተቋማት አገልግሎታቸውን የማዘመንና የማሻሻል ጉዳይ ግዴታቸው ብቻ ሳይሆን የህልውናቸው መሰረትም ነው:: ምክንያቱም የአገልግሎት አሰጣጥ ጉዳይ ከዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ እና ከመልካም አስተዳደር ጋር የተቆራኘ ነው:: ከዚህ ጋር በተያያዘ በአዲስ አበባ የስማርት ሲቲነት ጉዞ ወሳኝ ተደርገው ከተቀመጡት ምሰሶዎች አንዱ የሆነው ስማርት ገቨርናንስ (አስተዳደር) አጋዥ አቅም ይሆናል:: ይህንን አቅም ውጤታማ ለማድረግ አሠራሮችን ማዘመን፣ በቴክኖሎጂ መደገፍ፣ ከነባራዊው ዓለም ጋር መጓዝ ያስፈልጋል:: እንደ ከተማ አስተዳደር ባለፉት ጥቂት ዓመታት የተሠሩ ሥራዎች (የአዲስ መሶብን ጨምሮ) አበረታች ውጤት ታይቷል:: በ2019 በጀት ዓመት በዚህ ዘርፍ ከፍተኛ ሥራ በመሥራት ሁሉም ተቋማት አገልግሎታቸውን በኦንላይን የሚሰጡበት ደረጃ ላይ ለማድረስ መታቀዱን ቱሉ (ዶ/ር) ተናግረዋል::

በኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዘመን የከተማንና የከተሜነትን ደረጃ ከሚወስኑ መሰረታዊያን ውስጥ ከእንቅስቃሴ ጋር የተያያዘው ይገኝበታል። በአዲስ አበባ የስማርት ሲቲነት ዕቅድ ውስጥ የስማርት ሞቢሊቲ (እንቅስቃሴ) እንደ አንድ ምሰሶ የመካተቱ ምክንያትም ለዚህ ነው:: ከትራንስፖርት አገልግሎት ጋር በቀጥታ የሚያያዘውን የስማርት ሞቢሊቲ (እንቅስቃሴ) ዘርፍ ዘመኑን በሚመጥን ደረጃ ላይ ለማድረስ እንደ ከተማ በቴክኖሎጂ የታገዙ ሰፋፊና ግዙፍ ሥራዎች ሲሠሩ ቆይተዋል፤ አሁንም ያለማቋረጥ እየተሠሩ ይገኛሉ:: የሥራዎቹ ዋና ዓላማ የከተማዋን ትራንስፖርት ቀልጣፋ፣ ዘላቂ እና ለተጠቃሚ ምቹ ማድረግ ሲሆን፤ ዘመናዊ የትራፊክ አስተዳደር (Smart Traffic Management)፣ ስማርት የአውቶቡስ እና የህዝብ ማመላለሻ ስርዓቶች ዝርጋታ (Smart Bus and Public Transport Systems)፣ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች ውህደት (Electric Vehicle -EV Integration)፣ ስማርት የመንገድ መብራት (Smart Street Lighting)፣ ዘመናዊ የመኪና ማቆሚያዎች (Smart Parking Solutions) የመሳሰሉትን ያካትታል::

በአዲስ አበባ ከተማ የስማርት ሞቢሊቲ (እንቅስቃሴን) የተሳለጠ ለማድረግ የኮሪደር ልማቱ የስማርት ሲቲ አጋዥ ቴክኖሎጂዎችን እና አሠራሮችን ጥቅም ላይ ማዋሉን የጠቆሙት ቱሉ (ዶ/ር)፤ ደረጃቸውን የጠበቁ ሰፋፊ የተሽከርካሪ፣ የእግረኛ እና የሞተር አልባ (ሳይክል) መንገዶች ግንባታ፣ የስማርት መብራት እና የአካባቢ መረጃ ሰጪ መሳሪያዎች (Smart Lighting and Environmental Sensors) በከተማዋ በስፋት ለአገልግሎት መብቃታቸውን አክለዋል:: ከፍተኛ የትራፊክ ፍሰት እና መጨናነቅ በነበረባቸው የከተማዋ አካባቢዎች ተገንብተው ለአገልግሎት የበቁ ሰፋፊና ዘመናዊ የመኪና ማቆሚያዎች የከተማዋ ነዋሪዎች እና እንግዶች ጥሩ እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ አስተዋፅኦቸው የጎላ መሆኑን አስረድተዋል::

የከተማዋን ዘመናዊነት እና ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት ከፍ ለማድረግ በጥናት ተለይተው እየተፈጸሙ ካሉት ምሰሶዎች ስማርት ሊቪንግ (አኗኗር) እና ስማርት ፒፕል (ነዋሪ) ይጠቀሳሉ:: እነዚህም በተለያየ አግባብ በተሠሩ ሥራዎች ውጤት አሳይተዋል:: እንደ ቱሉ (ዶ/ር) ገለጻ፤ ስማርት ሊቪንግ (አኗኗር) በዋናነት ከጤና፣ ከቱሪዝም፣ ከሠላምና ጸጥታ እንዲሁም መሰል አገልግሎቶች ጋር ይያያዛል:: በዚህ ዙሪያ እንደ ከተማ አስተዳደር ግዙፍ እና ወሳኝ ሥራዎች ተከናውነዋል:: በተመሳሳይ የስማርት ፒፕል (ነዋሪ) ላይም በትኩረት ሥራዎች ተፈጻሚ ተደርገዋል፤ እየተደረጉም ነው:: የስማርት ሲቲ ውጤታማነትና ቀጣይነት የሚወሰነው በነዋሪው ብቃት፣ ንቃትና ዕውቀት ነው:: ከዚህ አንጻር የ5 ሚሊዮን ኮደርስ መርሃ ግብር ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጓል::

ከዳግማዊ ምኒልክ ሕክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ጋር በመተባበር በየአስራ አምስት ቀኑ የሚቀርብ

# የእውቅና ሽልማት የተቋማዊ ልህቀት መሠረት

• ለዳግማዊ ምኒልክ ሕክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የተሰጠው የእውቅና ሽልማት ለቀጣይ ተቋማዊ ዕድገቱ ሞተር ሆኖ እንደሚያገለግል ተገልጿል

**በሸዋርካብሽ ቦጋለ**



ፎቶ፦ ከገፀ ድር

ዳግማዊ ምኒልክ ሕክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ በ2018 ዓ.ም በተለያዩ የስራ ዘርፎች ላበረከተው ከፍተኛ አስተዋጽኦ የምስጋናና እውቅና ሽልማት ተበርክቶለታል

መልካምና የተሻለ ሥራ የሠራን ማበረታታት፣ መሸለምና ማመስገን፤ በሌላ በኩል ደግሞ በሥራው ላይ ውጤታማ ያልሆነን መኮነን ወይም የተሻለ ሠርቶ ውጤታማ እንዲሆን መንገድ መምራትና ማስተማር የማኅበረሰባችን የቆየና በጎ ልማድ ነው፡፡ ከሌሎች በተሻለና በጥሩ ሁኔታ ሥራውን ላከናወነ የትኛውም አካል የሚበረከቱ የምስጋና እና የእውቅና ሰርተፍኬቶች ለተቀጣዩ ጊዜ የተሻለ ሥራ ለመሥራት በማነሳሳት ረገድ የሚሰጡት ጥቅም በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡ በተለይም ተሸላሚው አካል የድካሙን ውጤት በተጨባጭ በመመልከቱ የኩራትና የደስታ ስሜት፣ የስነ-ልቦና እርካታ እንዲሁም ከፍተኛ የሥራ ተነሳሽነት እንደሚፈጥርበት እሙን ነው፡፡

ለሽልማት ሰጪው አካልም ቢሆን መልካም የሥራ አካባቢን በመፍጠር፣ ሰራተኞች የሚከበሩበት እና እውቅና የሚያገኙበት አዎንታዊ የሥራ ባህል ከመገንባት ባሻገር፤ ሰራተኞች ወይም አጋር አካላት ለተቋሙ ያላቸውን ታማኝነት፣ ፍቅርና ቁርጠኝነት በእጅጉ ይጨምራል። በተለይ ደግሞ ለተቋማት የሚበረከቱ የምስጋናና የእውቅና ሽልማቶች ለቀጣይ የላቀ ሥራ ለመሥራት ያላቸው ፋይዳ እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡ እነዚህ እውቅናዎች ተቋማት ካለፈው ስኬታቸው ተነስተው ለበለጠ ውጤት እንዲተጉ የሚያስችሉ በርካታ ጥቅሞች አሏቸው፡፡

ከእነዚህ ጥቅሞች መካከልም ተቋማዊ ተነሳሽነትንና የጤናማ ውድድር መንፈስን ማሳደግ፣ የተቋሙን ተዓማኒነትና መልካም ገጽታ መገንባት፣ ለቀጣይ ሥራ እንደ መለኪያና መነሻ ማገልገል እንዲሁም ስልታዊ ግቦችን ለማሳካት መርዳት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ይህንን እውነታ የሚያረጋግጠው በ2018 የሥራ ዘመን የላቀ የሥራ አፈጻጸም በማስመዝገቡ የእውቅና ሽልማት ከተሰጠው የዳግማዊ ምኒልክ ሕክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ያገኘነው መረጃ ነው፡፡

የኮሌጁ ቺፍ ኤክስኪዩቲቭ ዳይሬክተር አለሙ ዳንኤል እንደሚያስረዱት፤ የሕክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጁ ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ ለከተማዋም ሆነ ለሀገሪቱ በተለይም ለጤናው ዘርፍ የሰለጠነ የሰው ኃይል በማፍራት ረገድ ከፍተኛ ሚና እየተጫወተ ያለ አንጋፋ ተቋም ነው፡፡ በ2018 ዓ.ም የሥራ ዘመንም ብቁና የተማረ የሰው ኃይል በማፍራት፣ በጥናትና ምርምር እንዲሁም በማኅበረሰብ አገልግሎት ዘርፍ ላበረከተው ከፍተኛ አስተዋጽኦ የምስጋናና እውቅና ሽልማት ማግኘቱን ጠቅሰዋል፡፡

ኮሌጁ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮና ከአዲስ አበባ ምግብና መድኃኒት ቁጥጥር ባለሥልጣን ጋር በመተባበር ትልልቅና ስልታዊ ፕሮጀክቶችን ሲሠራ መቆየቱን ያስታወሱት ዳይሬክተሩ፣ እነዚህ ፕሮጀክቶች ዝም ብለው በመደርደሪያ ላይ የሚቀመጡ ሳይሆኑ ለሀገሪቱ የጤና ፖሊሲና ስትራቴጂ አስፈላጊ ግብዓት ሊሆኑ የሚችሉ ተግባራዊ ሥራዎች መሆናቸውን አረጋግጠዋል፡፡

የአዲስ አበባ ጤና ቢሮም የተከናወኑትን እነዚህን ዘመነኛና ውጤታማ ተግባራት ከግምት በማስገባት የምስጋናና እውቅና ሽልማት ማበርከቱን የጠቆሙት ቺፍ ኤክስኪዩቲቭ ዳይሬክተሩ፣ ሽልማቱ የተቋሙን የጋራ ስኬትና ድካም የሚያሳይ በመሆኑ የሰራተኞችን ሞራል በመገንባት፣ በሥራቸው እንዲኮሩና ይበልጥ እንዲተጉ ከማድረግ ባሻገር በተቋማት መካከል ጤናማ የሥራ ውድድር ይፈጥራል ብለዋል፡፡

እንደ አቶ አለሙ ማብራሪያ፣ እንደዚህ ያሉ የእውቅና ሽልማቶች ተቋማት ካለፈው ስኬታቸው ተነስተው በዘርፉ ካሉ ሌሎች ተቋማት የተሻሉ ሆኖ ለመገኘትና የተሰጣቸውን ክብር ጠብቀው ለመቀጠል ያስችላቸዋል። በተጨማሪም በላቀ አፈጻጸም ላይ እንዲያተኩሩ፣ የተቋሙን ተዓማኒነትና ገጽታ ለመገንባት፣ ለቀጣይ ሥራ እንደ መለኪያና መነሻ ለማገልገል ብሎም የተቀመጡ ስልታዊ ግቦችን በስኬት ለማሳካት ከፍተኛ እገዛ ያደርጋሉ። ለተቋማት የሚበረከቱ መሰል ሽልማቶች ተቋማቱ አዳዲስ አጋሮችን ወይም ደንበኞችን በቀላሉ ለመሳብ እንዲችሉ እንደ ማረጋገጫ (ምስክር) በመሆን ያገለግላሉ፤ በዚህም ረገድ ጠቃሚና ስትራቴጂካዊ ትስስር ከመፍጠር አኳያ ያላቸው ፋይዳ የጎላ ነው፡፡ አሁን የተገኘው እውቅና ለተቋሙ ቀጣይ ሥራ እንደ መለኪያና መነሻ ከማገልገሉ በላይ፣ ተቋሙ አሁን ካለበት የብቃት ደረጃ በታች እንዳይወርድና ይልቁንም የራሱን የመለኪያ መስፈርት (Standard) ከፍ እንዲያደርግ የሚያስገድድ የኃላፊነት ስሜት ይፈጥራል፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን ሽልማቱ የልህቀት ባህልን በሠራተኞች ዘንድ በማስረፅ ሥራን በተሻለና በጥራት ለማከናወን ከማነሳሳቱም በላይ፣ ሁልጊዜም ተወዳዳሪና የተሻለ ሆኖ የመገኘት ባህል እንዲቀጥል መሠረት ይጥላል፡፡

ዳግማዊ ምኒልክ ሕክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ከተመሠረተበት ከ1941 ዓመተ ምሕረት ጀምሮ በርካታ ታሪካዊና አገራዊ ሥራዎችን ሲሠራ የቆየ አንጋፋ የትምህርት ተቋም ነው፡፡ በመሆኑም አሁን ያገኘው ሽልማት ተቋሙ ለወደፊቱም ለበለጠ ስኬትና ውጤት እንዲተጋ ትልቅ መንፈሳዊ ጥንካሬ እንደሚሰጠው ዳይሬክተሩ ገልጸዋል፡፡

ኮሌጁ በዘንድሮው የትምህርት ዘመንም በተለያዩ የሕክምናና ጤና ዘርፎች ያሰለጠናቸውን 700 ገደማ ተማሪዎችን በቅርቡ ለማስመረቅ ከፍተኛ ዝግጅት እያደረገ ይገኛል፡፡ በሀገር አቀፍ ደረጃ የመጀመሪያ ዲግሪ ተማሪዎች ትምህርታቸውን ሲያጠናቅቁ የሚወስዱትን የመውጫ ፈተና የኮሌጁ አብዛኞቹ ተማሪዎች 100 በመቶ፣ ሌሎች በርካታ ተማሪዎች ደግሞ 95 በመቶና ከዚያ በላይ ውጤት አምጥተው ማለፋቸው ይታወቃል፡፡ ይህም ኮሌጁ ሀገሪቱ የምትፈልጋቸውን ብቁ፣ ሞያተኞችና ተወዳዳሪ ባለሙያዎችን በማፍራት ረገድ ጉልህ ሚና እየተጫወተ መሆኑን በተግባር የሚያስመሰክር ማረጋገጫ ነው፡፡

ለኮሌጁ የእውቅና ሽልማት ሊሰጠው የቻለው በመማር ማስተማሩ ረገድ ካሳየው የላቀ ብቃት በተጨማሪ፣ በተለይ በጤናው ዘርፍ ክፍተት ያለባቸውን፣ በሌሎች ቦታዎች በስፋት የማይገኙ የሙያ መስኮችን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮን ፍላጎት መሠረት በማድረግ አዲስ ዲፓርትመንቶችን በመክፈት፣ በማሰልጠን፣ ብቁ በማድረግና በማስመረቅ ረገድ ባከናወነው አርአያነት ያለው ሥራ ነው፡፡ ከዚህም ባሻገር ዘመኑን ያገናዘቡ ልዩ ልዩ ጥናትና ምርምሮችን በመሥራት እንዲሁም የማኅበረሰብ አቀፍ አገልግሎቶችን በብቃትና ጥራት በመስጠቱ ጭምር እንደሆነ ተገልጿል፡፡

ይህ አንጋፋና ቀደምት ተቋም በረጅም ዘመን ጉዞው የአሁኑ ሽልማት የመጀመሪያው አይደለም፤ እስካሁንም በርካታ አገራዊና አካባቢያዊ ሽልማቶች ሲበረከቱለት ቆይቷል፡፡ ባለፉት ሁለት ዓመታት ብቻ ከጤና ሚኒስቴር ያገኘውን የዋንጫና የሰርተፍኬት ሽልማት ጨምሮ፣ ከጤና ቢሮም በየዓመቱ እንዲሁም በየሩብና ግማሽ ዓመቱ በሚደረጉ የእቅድ አፈጻጸም ግምገማዎች እየተሸለመ መምጣቱን ከተቋሙ ያገኘነው መረጃ ያረጋግጣል፡፡

አዲስ አበባ የሀገሪቱ ዋና ከተማና የዲፕሎማሲ ማዕከል እንደ መሆኗ መጠን፣ አብዛኞቹ የጤና ባለሙያዎች የሙያ ማጎልበቻና ተከታታይ ስልጠናዎችን (CPD) የሚወስዱት በዳግማዊ ምኒልክ ሕክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ኮሌጁ በመማር ማስተማር፣ በጥናትና ምርምር፣ በማኅበረሰብ አገልግሎት እንዲሁም በተከታታይ የሙያ ስልጠናዎች ከሚሰጠው አገልግሎት አኳያ እንደ አንድ ግዙፍ የከፍተኛ ትምህርት ተቋምነቱ የሚጠበቁበትን አገራዊ አበርክቶዎች በብቃት እየተወጣ ይገኛል፡፡

ሥራን ማዕከል አድርጎ በትክክለኛ መንገድ የሚበረከት ማንኛውም እውቅናና ሽልማት ለተሻለ ሥራ መነሳሳት እንደሚፈጥር አጠራጣሪ አይደለም። ተቋሙ ያገኘው ሽልማትም ለበለጠ ሥራ የሚያነሳሳው በመሆኑ፣ ወደፊትም ኮሌጁ ባስቀመጠው ስትራቴጂካዊ ዕቅድ መሠረት የአስር፣ የአምስትና የአንድ ዓመት ዕቅዶቹን ባቀደው ልክና ጥራት ለመፈጸም አጠናክሮ እንደሚቀጥል ዳይሬክተሩ አረጋግጠዋል፡፡

ከዚህ የምንረዳው ዋና ነገር ቢኖር፣ የምስጋናና የእውቅና ሽልማቶች ያለፈው ሥራ ማጠቃለያ ወይም ማብቂያ ብቻ ሳይሆኑ፣ ተቋማት ለወደፊቱ ይበልጥ ጠንካራ፣ ቀልጣፋ፣ ተወዳዳሪና ስኬታማ እንዲሆኑ የሚያነሳሱ ዋና ዋና የለውጥና የዕድገት ሞተሮች መሆናቸውን ነው፡፡

# የአዲስ አበባ የጤና ቱሪዝም ማዕከልነት ጉዞ

- ከተማዋን የጤና ቱሪዝም ማዕከል የማድረጉ ጥረት ተጠራክሮ እንደሚቀጥል ተጠቁሟል

**በደረጀ ታደሰ**

አዲስ አበባን የጤና ቱሪዝም ማዕከል ለማድረግ እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች ተስፋ ሰጪ ውጤት እያስመዘገቡ ይገኛሉ፡፡ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ከተማ አስተዳደሩ ለጤናው ዘርፍ ትልቅ ትኩረት መስጠቱ ለውጤቱ ቁልፍ ሚና በመጫወት ላይ ነው፡፡ ነባር የጤና ተቋማትን አቅም ከማሻሻል ጀምሮ አዳዲስ እና ደረጃቸውን የጠበቁ ጤና ተቋማትን ለአገልግሎት ማብቃት ተችሏል፡፡ በመሰረተ ልማት፣ በግብዓት፣ የሠው ኃይል በማደራጀት ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የሕክምና አገልግሎት መስጠት የሚያስችል አቅም እየተገነባ ይገኛል፡፡ ይህም መዲናዋ ከሀገር አልፎ የጎረቤት እና የሌሎች ዓለም ሀገራት ዜጎች ታክመው የሚድኑባት ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የሕክምና አገልግሎት መስጫ ማዕከል ለመሆን የያዘችውን ግብ እንድታሳካ ያደርጋታል፡፡



ፎቶ፡- ከገፀ ድር
ለጤና ቱሪዝም አቅም ከሚፈጥሩ አዳዲስ ግንባታዎች እና የህክምና መስጫ መሳሪያዎች በጥቂቱ

ባለፉት ጥቂት ዓመታት የተሠራው የጤናውን ዘርፍ የማሻሻል እና ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ አገልግሎት የመስጠት ጅምር ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ከተማ አስተዳደሩ አሳውቋል፡፡ ከቀናት በፊት፣ በከተማ አስተዳደር ደረጃ የተካሄደው የቀጣይ አምስት ዓመታት ስትራቴጂክ እቅድ እና የ2019 በጀት ዓመት ዝርዝር እቅድ ውይይት ላይ ከተነሱ ቁልፍ የትኩረት አቅጣጫዎች መካከል የጤናውን ዘርፍ የማሻሻል ጉዳይ ይገኝበታል። ይህም አዲስ አበባን የጤና ቱሪዝም ማዕከል የማድረግን ዓላማ ታሳቢ ያደረገ ስለመሆኑ፤ ለተከታታይ ሁለት ቀናት የተካሄደውን የዕቅድ ውይይት ማጠቃለያ አስመልክቶ የአዲስ አበባ ከንቲባ አዳነች አቤቤ በይፋዊ የማህበራዊ ትስስር ገጻቸው ላይ ያስተላለፉት መልዕክት ይጠቁማል፡፡

ከንቲባ አዳነች በመልዕክታቸው፤ በከተማ አስተዳደር ደረጃ በቀጣይ ትኩረት ከሚሰጣቸው ጉዳዮች መካከል፡- የማህበራዊ ዘርፍ (ጤና፣ ትምህርት ...) ተደራሽነትና ጥራት እንዲሁም ፍትሃዊነትን ማረጋገጥ ይገኝበታል። በተለይ በጤናው ዘርፍ የታቀዱ ተግባራትን በላቀ አፈጻጸም በመከወን፣ ዓለም አቀፍ ደረጃውን (ስታንዳርድ) ያሟላ የጤና አገልግሎት ለመስጠት፣ የጤና ቱሪዝም ማዕከል ለመሆን እና የከተማዋን የቱሪዝም መዳረሻነት ዕውን ለማድረግ ከተማ አስተዳደሩ ዝግጁ መሆኑን በመልዕክታቸው ጠቁመዋል፡፡

## ወደ ውጤት የተቀየሩት የመዲናዋ የጤና ቱሪዝም አቅሞች

ውጤት በፍላጎት ወይም በምኞት ብቻ አይሳካም፡፡ ጥራት ያለው ዕቅድ፣ ብቁ አመራር፣ ቁርጠኝነት የታከለበት አፈጻጸም፣ የተቀናጀ አሠራርና ተያያዥ መርሆችን መተግበር ይጠይቃል። አገራት ወይም ከተሞች የጤና (የሕክምና) ቱሪዝም ማዕከል ለመሆን ካሰቡ፣ ሊያሟሏቸው የሚገቡ ቅደመ ሁኔታዎችን ዕውን ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ የጤና (ሕክምና) ቱሪዝም ላይ ማዕከል አድርጎ የተሠራ እና "Grand View Research (2026) — Medical Tourism Market Size & Share Report" በሚል ርዕስ ይፋ የሆነ ሰነድ የጤና ቱሪዝም ማዕከል ለመሆን አገራት ወይም ከተሞች ሊያሟሏቸው የሚገቡ መስፈርቶችን ዘርዝሯል። እንደመረጃው ከሆነ፡- ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ እና ከሌሎች የተሻለ የህክምና መሰረተ ልማት፣ ብቁ የህክምና ባለሙያዎች፣ የህክምና መሣሪያዎች መኖር እንዲሁም ጥራት ያለው የህክምና አገልግሎትን በተመጣጣኝ ዋጋና በአጭር ጊዜ መስጠት መቻልን በተግባር ማረጋገጥ ለጤና ቱሪዝምነት ከሚያበቁ ቅድመ ሁኔታዎች መካከል ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፣ መዲናዋን የጤና ቱሪዝም ማዕከል የማድረግን ዓላማ ለማሳካት እየተጓዘበት ያለው መንገድ ለስኬት የሚያበቃ እንደሆነ፣ ከላይ በጥናቱ የተጠቆሙትን ቅድመ ሁኔታዎች ወደ ውጤት የቀየረበት አፈጻጸም ያረጋግጣል፡፡ ከተማዋ ነባር ሆስፒታሎችን የማደስ፣ የማስፋፊያ ግንባታዎችን የማከናወን፣ አዳዲስ ሆስፒታሎች እና የጤና ተቋማት ለአገልግሎት በማብቃት ... የጤና መሰረተ ልማትን እያሳደገች ትገኛለች። አገልግሎቶችን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የማስደገፍ እና ብቁ የሰው ሀይል በማፍራት ረገድም አስደናቂ ውጤቶችን ማስመዝገቧን ቀጥላለች። በዚህም ባለፉት አምስት አመታት በተከናወኑ ስራዎች የጤና አገልግሎት ጥራትና ተደራሽነት አቅም ከእጥፍ በላይ ማሳደግ ስለመቻሉ፣ የአዲስ አበባ ከንቲባ አዳነች አቤቤ የአዲስ አበባ ምክር ቤት 5ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 4ኛ መደበኛ ጉባኤው ላይ ባቀረቡት ሪፖርት ማረጋገጣቸው ይታወሳል፡፡

የጤና መሰረተ ልማትን በማስፋፋት ሂደት ውስጥ እንደ ከተማ አስተዳደር ከተከናወኑ ብዛት ያላቸው ውጤታማ ተግባራት መካከል፡- የነባር ሆስፒታሎችን አቅም የማሳደግ እና የማሻሻሉ ተግባር (የዳግማዊ ምኒልክ ኮምፕሪሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፣ ዘውዲቱ መታሰቢያ ሆስፒታል...) እንዲሁም በ40 ጤና ጣቢያዎች መሰረታዊ ማስፋፊያ እና 9 አዳዲስ የጤና ጣቢያዎች (የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል አገልግሎት መስጠት በሚችል መልኩ) ተገንብተው ለአገልግሎት መብቃታቸው መጥቀስ ይቻላል፡፡ በ5 ነጥብ 4 ሄክታር የመሬት ይዞታ፣ 17 ዘመናዊ ህንጻዎችን በማቀናጀት፣ ለአገልግሎት የበቃው የላፍቶ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል በጤናው ዘርፍ ከታዩ የለውጥ አቅሞች አንዱ ተደርጎ የሚወሰድ ነው፡፡

የጤና መሰረተ ልማትን የማሟላቱ ተግባር ለመንግስት የተተወ ብቻ አይደለም፡፡ ዘርፉ አቅም ላላቸው የግል ባለሃብቶችም ክፍት የተደረገ ነው። ነሀሴ 17 ቀን 2018 ዓ.ም. ተመርቆ ለአገልግሎት የበቃው የኒው ሊፍ ሜዲካል ኮምፕሌክስ በጤናው ዘርፍ የግል ባለሃብቱን ተሳትፎ ያረጋገጠ ነው፡፡ በዶክተር ኢማን አብዱልራህማን እና ባለቤታቸው አቡበከር መሐመድ ሳላህ አማካኝነት ተገንብቶ ለአገልግሎት የበቃው ይኸው ሜዲካል ኮምፕሌክስ፤ ባለ 13 ወለል ዘመናዊ ሜዲካል ፕላዛ፣ ከ110 በላይ የሕክምና አልጋዎችንና 8 የላቁ የቀዶ ጥገና ሕክምና ክፍሎች (Operating Theatres) በአንድ ጣራ ስር ያቀፈ ተቋም ነው። ለግንባታውም ከሦስት ቢሊዮን ብር ባላይ ወጪ ተደርጎበታል፡፡

የኒው ሊፍ ሜዲካል ኮምፕሌክስ ምረቃ ላይ የተገኙት ከንቲባ አዳነች አቤቤ ባስተላለፉት መልዕክት፤ አዲስ አበባን የጤና ቱሪዝም ማዕከል የማድረጉ ዓላማ በመንግስት እና የግሉ ዘርፍ የጋራ ጥረት የሚሳካ መሆኑን ተናግረዋል፡፡ ኮምፕሌክሱ በሃገራችን ከላፍቶ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ቀጥሎ ሁለተኛው PET-CT SCAN CAT LAB እና ሌሎች ዘመኑን የዋጁ ቴክኖሎጂዎች የተሟሉለት ትልቅ የጤና ማዕከል ነው፡፡ በጤናው ዘርፍ የሚደረገው ኢንቨስትመንት ክፍያው ከሁሉ የላቀ ነው፡፡ በዘርፉ ለሚሰሩ የግል ባለሃብቶች ከተማ አስተዳደሩ የሚያደርገውን ድጋፍ አጠናክሮ ይቀጥላልም ብለዋል፡፡

የሜዲካል ኮምፕሌክሱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ዶክተር ኢማን አብዱረህማን በበኩላቸው፤ ተቋሙ 110 አልጋዎችን፣ እጅግ ዘመናዊና ደረጃቸውን የጠበቁ ግብዓቶችን፣ ብቁ ሙያተኞችን በማቀናጀትና በማደራጀት ወደ አገልግሎት ገብቷል፡፡ ከ20 በላይ የስፔሻሊቲና የሰብ-ስፔሻሊቲ ሕክምና አገልግሎቶችን በመስጠት ሥራውን የሚጀምረው ይህ ተቋም፤ በጽኑ ሕክምና (ICU) እና የቀዶ ሕክምና አገልግሎት በምሥራቅ አፍሪካ ከሚገኙ ጥቂት ተመራጭ የሕክምና ተቋማት አንዱ ይሆናል። ኮምፕሌክሱ በቅርቡ የላቀ የካንሰር ሕክምና አገልግሎት በመጀመር አገሪቱ ውስጥ የመጀመሪያው የግል የሕክምና ተቋም ለመሆን እየሠራ እንደሆነም አመላክተዋል፡፡

## የጤና ቱሪዝም ዓለም አቀፍ ማሳያዎች

የጤና ቱሪዝም፣ አገራት ወይም ከተሞች ለዜጎቻቸውና ለነዋሪዎቻቸው ደረጃውን የጠበቀ የሕክምና አገልግሎት ከመስጠት አልፈው፣ ለሌሎች ተመራጭ

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

## “እንጦጦ ... ከገጽ 7 የዞረ

ጠቁመዋል፡፡

አቶ መዝገቡ ይስማው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሕዝብ መዝናኛ ቦታዎች እና ፓርኮች ኮርፖሬሽን አስተዳደር ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ እና የእንጦጦ ፓርክ አስተዳደር ኃላፊ ናቸው፡፡ ወርሃ መስከረምን ተከትሎ ለሚመጡ ጎብኚዎች እንደ አንድ የቱሪስት መስህብ እንጦጦ ፓርክ ያደረገውን ዝግጅት በተመለከተ ማብራሪያ ሰጥተውናል፡፡

እንጦጦ ፓርክ በአዲስ አበባ ከተማ በእንጦጦ ተራራ ላይ የሚገኝ የተፈጥሮ ፀጋ ታድሏል። ጥንታዊነቱን ሳይለቅ ተሻሽሎ የጎብኚዎችን ቀልብ በሚስብ መንገድ ተሰርቷል፡፡ በውስጡም ሠው ሠራሽ ሐይቅ፣ የሃይኪንግ ፕሮግራም ለማስኬድ የሚያስችል ቦታ፣ በእግር ለመንቀሳቀስ የሚያስችል 14 ኪሎ ሜትር የውስጥ ለውስጥ መንገድ፣ ከ20 ሺህ ሕዝብ በላይ መያዝ እና ልዩ ልዩ ኩነቶችን ማስተናገድ የሚችል፣ ሁሉም ነገር የተሟላለትና ደረጃውን የጠበቀ አምፊ ቴአትር፣ ፈረስ ግልቢያን፣ የገመድ ላይ ጨዋታን ጨምሮ ሁሉም ዓይነት የአዋቂና የህፃናት መጫዎቻዎች፣ አርት ጋለሪዎችንና ሌሎች የመዝናኛ ዓይነቶችን ይዟል፡፡ በተጨማሪም የስፓ እና የመኝታ አገልግሎትን ጨምሮ ልዩ ልዩ መስተንግዶዎችን የሚሰጡ ሬስቶራንቶችን እና ካፌዎችን በውስጡ አቅፎ የያዘ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

እንጦጦ ፓርክ ባለው ከፍታማ የመልክዓ ምድር አቀማመጥ፣ በደን የተሸፈነ እና በነፋሻማ ቀዝቃዛ አየሩ ምክንያት በጎብኚዎች ዘንድ ተመራጭ የቱሪስት መዳረሻ መሆኑን የነገሩን አቶ መዝገቡ፤ የመስከረም ወር ጎብኚዎች የቱሪስት መስህቦችን የሚጎበኙበት ወቅት በመሆኑ ይህን ታሳቢ ያደረጉ የተለያዩ ዝግጅቶችን አድርጓል። ከእነዚህም ውስጥ በብዛት እና በቡድን ሆነው ለሚመጡ ጎብኚዎች የማበረታቻ የክፍያ አመራጮች ተዘጋጅተዋል። ይህም ጎብኚዎች እያንዳንዳቸው በተናጠል ከሚከፍሉት የመግቢያ ክፍያ ይልቅ ሰብሰብ ብለው ሲመጡ ቅናሽ ማግኘት የሚችሉበት ነው፡፡ የውጭ ጎብኚዎችን ይዞ የመጣ የሀገር ውስጥ ጎብኚም በነፃ እንዲጎበኝ ይደረጋል፡፡

ከኢትዮጵያ አየር መንገድ እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆንም ቱሪስቶችን ወደ እንጦጦ ይዘው እንዲመጡ የማድረግ፣ እንጦጦ ላይ ኩነቶችን በጋራ ማዘጋጀት ለምሳሌ፡- ኢትዮ-ሆሊዴይ ከሚባለው ከኢትዮጵያ አየር መንገድ አስጎብኚ ድርጅት ጋር የመግባቢያ ስምምነት በመፈራረም የውጭ እንግዶችን በራሱ ባስ (የመጓጓዣ አማራጭ) ይዞ እንዲመጣ ተደርጓል፡፡ ይህም ሌላኛው እየተደረገ ያለው ዝግጅት ነው፡፡

ከታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ጋር በንግድ ባንክ ስፖንሠርነት በወሩ የመጨረሻው ቅዳሜ ከ700 በላይ ሯጮች የሚሳተፉበት የ5 ኪሎ ሜትር ሩጫ ውድድር በፓርኩ ውስጥ እንደሚያካሂዱ አቶ መዝገቡ፣ ፓርኪንግ የሚሠሩ ወጣቶችን ጨምሮ በፓርኩ ውስጥ ያሉ ድርጅቶች በጥሩ መስተንግዶ እንግዶችን እንዲቀበሉ እና እንዲያስተናግዱ በመግባባት ተዘጋጅተው እየጠበቁ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ከጊዜ ወደ ጊዜ የጎብኚዎች ቁጥር እየጨመረ መምጣቱን የገለፁት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሕዝብ መዝናኛ ቦታዎች እና ፓርኮች ኮርፖሬሽን አስተዳደር ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ እና የእንጦጦ ፓርክ አስተዳደር ኃላፊው፤ እንደ ሁኔታው የሚቀያየር ቢሆንም ከሰኞ እስከ አርብ በየቀኑ በአማካይ ከ1 ሺህ እስከ 1 ሺህ 600 ያህል ጎብኚዎች የሚጎበኙት ሲሆን፤ ቅዳሜ እና እሁድ ደግሞ ከ2 ሺህ እስከ 2 ሺህ 500 ይደርሳል። በተለይ የሀገር ውስጡ የተማሪ ጎብኚ ቁጥር እየጨመረ መጥቷል፡፡

### የጎብኚዎች ቁጥር ሲጨምር ገቢውም ይጨምራል።

የመግቢያ ክፍያ ማስከፈል በጀመረበት 2017 ዓ.ም 76 ሚሊዮን፣ በ2018 በጀት ዓመት ደግሞ የዕቅዱን 99 ነጥብ 3 በመቶ በማሳካት 90 ሚሊዮን ብር ገቢ ከመግቢያ ክፍያ ብቻ ማስገባት የቻለ ፓርክ መሆኑንም ነግረውናል፡፡

## ስማርት... ከገጽ 8 የዞረ

ሀገር ወደተሻለ ደረጃ ማሸጋገር የሚያስችላቸውን አቅም እንዲፈጥሩ እየተሰራ ነው፡፡ የሪፎርም ስራ በመስራትም አሰልጣኞችን የማብቃት ስራ እየተከናወነ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

ወይዘሮ ዳግማዊት እንደገለፁት፤ ቴክኒክና ሙያ ዘርፍ ባልዘመነ ቁጥር የከተማዋን እድገት ይገድባል፡፡ ከከተማዋ የእድገት ሁኔታ ጋር አብሮ የሚጓዝ የሰው ሀይል ማውጣት ይገባል፡፡ ይህም የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋማት በሚያቀርቡት የሰው ኃይል ብዛት ብቻም ሳይሆን ጥራትና ዘመናዊ ክህሎት ላይ የሚታየውን ክፍተት መቀነስ ይገባል። ዓለም እየተራመደችበት ካለችበት አንጻር ከሀገር አቀፍ ባለፈ ለዓለም አቀፍ ገበያ ጭምር የሚመጥኑ ሰልጣኞችን ለማፍራት የሚችል ተቋም ለመገንባት የሚያስችል ነው፡፡

### ኮሌጁ ለስራ ዕድል ፈጠራ

እንደ ምክትል ቢሮ ኃላፊዋ ገለጻ፤ ባሉት 15 ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች ሰልጣኞችን ማፍራትና የስራ እድል መፍጠር ተችሏል። ከእነዚህ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች ሰልጥነው የሚውጡትን ባለሙያዎች ለከተማዋ ብቻ ሳይሆን ለዓለም አቀፍ ገበያ ጭምር ማቅረብ እየተቻለ ነው፡፡ ወደ አረብ ሀገራትና አውሮፓ በማሰልጠን፣ በማብቃትና በማስመዘን እየተላከ ነው። ይህ ስማርት ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ግን ጥራት ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ተወዳዳሪና ተመራጭ የሆነ ሰልጣኝ ለማብቃት ኮሌጁ የላቀ አበርክቶ ይኖረዋል። ስማርት ኮሌጁ ሰልጣኞች የራሳቸውን የቴክኖሎጂ ሀሳቦች የሚያበለጽጉበት ኢንኩቤሽን (መፈልፈያ) ማዕከል ስለሚኖረው፤ ሰልጣኞች ተቀጣሪ ብቻ ሳይሆኑ የቴክኖሎጂ ስራ ፈጣሪ እንዲሆኑ መንገድ ይከፍታል፡፡ በዚህም ኮሌጁ በስራ ዕድል ፈጠራና በቴክኖሎጂ ላይ የተመሠረተ ክህሎት በማስጨበጥ ወጣቶች ስራ ፈጣሪ እንዲሆኑ እድል ይፈጥርላቸዋል። ሰልጣኞች በሰለጠኑበት ሙያ ስራ ፈጣሪ መሆን ከቻሉ ደግሞ ለራሳቸው ገቢ ከመፍጠር ባለፈ ለሌሎች ዜጎችም የስራ ዕድል መፍጠር ይችላሉ።

### ለስማርት ከተማ ግንባታ ስለሚኖረው አበርክቶ

አዲስ አበባ ከተማ አሁን ላይ ወደ ስማርት ከተማነት እየተቀየረች ትገኛለች። በፍጥነት እያደገች ባለች ስማርት ከተማ ውስጥ በተለያየ ዘርፍ የሰለጠኑ ባለሙያዎች ያስፈልጋሉ። በግንባታ፣ በኤሌክትሪክ፣ በማሽን፣ በአውቶሞቲቭ፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና በሌሎች ዘርፎች የተካነ የሰው ኃይል ይፈልጋሉ። ስማርት ከተማ ማለት ዲጂታል ቴክኖሎጂንና የሰው ሰራሽ አስተውሎትን (አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ) በመጠቀም የከተማ አገልግሎቶችን ቀልጣፋ፣ ተደራሽ፣ ዘላቂና ለነዋሪዎች ምቹ ማድረግ በተለይም የህዝብ አገልግሎቶችን እንደ የትራፊክ ፍሰትን፣ የቆሻሻ አወጋገድ ስርዓትን እና የኃይል አጠቃቀምን የሚያዘምን ማለት ነው። ስማርት ከተማን መገንባት የሚቻለው ደግሞ ዘመኑ የዋጃቸውን ዲጂታል ቴክኖሎጂንና የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስን የሚያንቀሳቅስ፣ የሚንከባከብ እና ከጊዜው ጋር የሚያሻሽል ብቃት ያለው የሰው ሃይል መፍጠር ሲቻል ነው። ለዚህ ደግሞ የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች ሚና ከፍተኛ ነው፡፡

እንደ ምክትል ቢሮ ኃላፊዋ ገለጻ፤ ስማርት ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጆች የስማርት ከተማ ግንባታ ውስጥ የሰው ኃይል አቅርቦት፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ የፈጠራ ስራ፣ የስራ ዕድል ፈጠራና ዘላቂ ልማት የሚያጠናክሩ ተቋማት ናቸው። ስማርት ከተማ ለመገንባት ዘመናዊ መሳሪያዎችን የሚጠቀሙ፣ የሚያስተዳድሩ፣ የሚጠግኑና አዳዲስ መፍትሄዎችን የሚፈጥሩ ባለሙያዎች ያስፈልጋሉ። ይህንን ብቁ የሆነ የሰው ኃይል በማፍራት ረገድ በቅርቡ ወደ ግንባታ የገባው ስማርት ፖሊ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ የማይተካ ሚና ይጫወታል።

### የኮሌጁ የቅበላ አቅም

የማሰልጠኛ ቁሳቁስ ማሟላትን ጨምሮ የኮሌጁን ግንባታ ለማጠናቀቅ ከአንድ ዓመት ከግማሽ እስከ ሁለት ዓመት ድረስ እንደሚወስድ የተናገሩት ምክትል ቢሮ ኃላፊዋ፤ እንደመነሻ ከ800 እስከ 1000 ሰልጣኞችን ይቀበላል፡፡ በሂደት ግን የቅበላ አቅሙ እየሰፋ ይሄዳል፡፡ እንደማዕከልነቱ በመደበኛ ስልጠና ብቻ ሳይሆን በማብቃት ላይ ስለሚሰራ በርካታ ሰልጣኞችን ተደራሽ ሊያደርግ ይችላል፡፡ በየመሀሉ ያላቸውን ብቃት ለማዳበር ጥቂት ድጋፍ ለሚሹ ሰልጣኞች በአጫጭር ስልጠና የማብቃት ስራ ይሰራል፤ ይህም የቅበላ አቅሙን ያሳድገዋል፡፡ ሰልጣኞችን የመቀበል መመዘኛ መስፈርት ሲታይ እንደከዚህ ቀደሙ በሚወሰኑ መቁረጫ ነጥብ ሆኖ የሰልጣኞችን ፍላጎት መሰረት ያደርጋል፡፡

## የአዲስ ... ከገጽ 16 የዞረ

የሕክምና ማዕከል ያደርጋቸዋል። ዜጎች ለተሻለ ሕክምና ወደ ውጭ ሀገራት በመሄድ የሚያወጡትን ወጪ ያስቀራል። ከዚህም አልፎ፤ ከፍተኛ የገቢ ምንጭ፣ የዲፕሎማሲ መሣሪያ፣ የገጽታ መገንቢያም ሆኖ ያገለግላል፡፡ አዲስ አበባ እየሠራች ያለው ሥራም ከጤና ቱሪዝም የሚገኙትን በርካታ ጠቀሜታዎች ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡

በጎርጎሮሳዊያኑ የዘመን አቆጣጠር 2024 ላይ፣ ‘HospaccX’ በተባለ (በኢትዮጵያ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ በጤና እንክብካቤ ማማከር ሥራ በሚያከናውን) ተቋም የተሠራ ጥናት፣ ኢትዮጵያውያን ለላቀ ሕክምና ወደ ውጭ አገር በመጓዝ በየዓመቱ ወደ 500 ሚሊዮን ዶላር የሚጠጋ ወጪ እንደሚያወጡ አረጋግጧል፡፡ እንግዲህ አዲስ አበባ የጤና ቱሪዝም ማዕከልነት ስኬት ይህ ገንዘብ እንዳይወጣ ከማስቻል የሚጀምር ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ስኬታማ ጅምሮዎቿን የበለጠ እንድታስቀጥል፤ በየዓመቱ በግምት ከ34 ቢሊዮን እስከ 76 ቢሊዮን ዶላር በላይ የገበያ ድርሻ ባለው የዓለም የሕክምና ቱሪዝም ገበያ ውስጥ ጉልህ ተሳትፎ የሚያደርጉ አገራትን (ታይላንድ፣ ተርኪዬ፣ ሕንድ እና ማለዢያ) ተሞክሮ፣ ዓለም አቀፍ የንግድና ተያያዥ እንቅስቃሴዎችን የተመለከቱ መረጃዎችን በማውጣት የሚታወቀውን Global Market Insights፣ Medical Tourism Statistics 2026 በምንጭነት በመጠቀም እንመልከት፡፡

ታይላንድ ዘመናዊ የሕክምና መሠረተ ልማትን ከባህላዊ የቱሪዝም እንክብካቤ ጋር በማዋሃድ፣ ዓለም አቀፍ ዕውቅና የተሰጣቸው ከ60 በላይ ሆስፒታሎቿን በመጠቀም ከተለያዩ አገራት ለሚመጡ ታካሚዎች አገልግሎት ታቀርባለች። በተለይ በልብ ቀዶ ህክምና፣ በአጥንት ሕክምና እና በፕላስቲክ ሰርጀሪ ተመራጭ መሆን ችላለች፡፡ በዚህም ከጤና ቱሪዝም ብቻ በዓመት ከ4 ቢሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ታገኛለች፡፡

በጎርጎሮሳዊያን የዘመን ቀመር 2025 ብቻ በዓመት ከ2 ሚሊዮን በላይ የሕክምና ቱሪስቶችን በማስተናገድ ከ3 ቢሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ያገኘችው ተሪኪዬ፤ በጥርስ ሕክምና፣ በካርዲዮሎጂ፣ በአጥንት ሕክምና እና በፀጉር ንቅለ ተከላ አገልግሎትን በማቅረብ ተመራጭ ናት፡፡ ለሕክምናው እጅግ ዘመናዊ ቴክኖሎጂን መጠቀሟ፣ በቅናሽ ዋጋ ማቅረቧ እንዲሁም የተሪኪዬ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር (USHAS) የተባለ ልዩ ተቋም በማቋቋም የሕክምና ቪዛ አሰጣጥን የሚያቀል አሠራር መዘርጋቱ ለስኬቷ ጉልህ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡

### እንደማጠቃለያ

የጤና ቱሪዝም ማዕከልነትን ማረጋገጥ፤ በአንድ ድንጋይ በርካታ ወፎችን እንደመምታት የሚቆጠር ነው። አዲስ አበባ እየተጓዘችበት ያለው የጤና ዘርፍ ስኬታማ መንገድ ይህንን ታሳቢ ያደረገ ስለመሆኑ፤ የከተማ አስተዳደሩ ጤና ቢሮ ኃላፊ ዮሐንስ ጫላ (ዶ/ር) በተደጋጋሚ ሲያነሱ ይደመጣል፡፡ በቅርቡ ለአገልግሎት የበቃው የኒው ሊፍ ሜዲካል ኮምፕሌክስ ምረቃ ላይ ተገኝተው ባስተላለፉት መልዕክት፤ በከተማዋ በመንግስትና በባለሀብቶች ጥራት ያለው የህክምና መሰረተ ልማትና አገልግሎት እንዲኖር እየተደረገ ያለው ጥረት አዲስ አበባን የጤና ቱሪዝም መዳረሻ የሚያደርጉ መሆናቸውን በመጥቀስ፤ ይህ ዓላማ ስኬታማነቱ እንዲቀጥል ሁሉም የድርሻውን እንዲወጣ ማሳሰባቸው ይታወሳል፡፡

# ግልፅ የጨረታ ማስታወቂያ

በልደታ ክፍለ ከተማ ስር የሚገኝ ዳግም ህዳሴ ጤና ጣቢያ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ዕቃዎች በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡ በመሆኑም፡-

1. ሎት 1 የደንብ ልብስ የጨረታ ማስከበሪያ 4000 ብር
2. ሎት 2 የፅዳት እቃዎች የጨረታ ማስከበሪያ 4000 ብር
3. ሎት 3 እስቴሽነሪ እቃዎች የጨረታ ማስከበርያ 4000ብር
4. ሎት 4 የቋሚ የፈርኒቸር እና ኤሌክትሮኒክስ እቃዎች የጨረታ ማስከበርያ 7000 ብር
5. ሎት 5 የህትመት ስራ የጨረታ ማስከበርያ 5000 ብር
6. ሎት 6 መድሃኒት እና የህክምና እቃዎች ጨረታ ማስከበርያ 7000 ብር
7. ሎት 7 የህንጻ እድሳት እና የፓርትሽን ስራ: Isolation ግንባታ፣ የጥበቃ ክፍል ግንባታ ስራ ሌሎችም የማስፋፋት ግንባታዎች ጨምሮ (የጥገና ግንባታ) ጨረታ ማስከበሪያ 7000 ብር
8. ሎት 8 የጥገና እቃዎች ጨረታ ማስከበሪያ 4000 ብር
9. ሎት 9 የመስተንግዶ ጨረታ ማስከበሪያ 1000 ብር

ስለዚህ ብቃት ያላቸውና በመስኩ የተሰማሩ ተጫራቾችን አወዳድሮ ግዢ መፈፀም ይፈልጋል፡፡ በዚሁ መሰረት፡-

1. በጨረታው ለመወዳደር ፍላጎት ያላቸው ተጫራቾች የታደሰ የንግድ ፈቃድ ያላቸው፣ የዘመኑን ግብር የከፈሉ፣ በመንግስት የግ/ን/አስ/ኤጀንሲ ላይ በአቅራቢዎች ምዝገባ ዝርዝር የተመዘገቡ የቲንና የቫት ተመዝጋቢ የሆኑና የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ፡፡
2. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ በባንክ የተረጋገጠ ሲፒኦ ብቻ ከጨረታ ሰነድ ጋር አያይዘው ማቅረብ የሚችሉ፡፡
3. ተጫራቾች ጨረታውን በአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ አዲስ ልሳን ጋዜጣ ከወጣበት ዕለት አንስቶ ለ10 ተከታታይ የስራ ቀናት የማይመለስ ብር 300 (ሶስት መቶ ብር) በመክፈል ዳግም ህዳሴ ጤና ጣቢያ 4ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 409 በመምጣት የጨረታ ሰነድ መግዛት ይኖርባቸዋል፡፡
4. ተጫራቾች የመጫረቻ ሰነዶቻቸውን በታሸገ ኤንቨሎፕ ኦርጅናል እና ኮፒ ጋር ማስታወቂያው ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ10 ተከታታይ የስራ ቀናት ዳግም ህዳሴ ጤና ጣቢያ 4ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 409 በመምጣት ለጨረታ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡ እዲሁም የጨረታ ማስከበርያ ሲፒኦ ከቴክኒክ ሰነድ ጋር አያይዘው ማቅረብ ይኖረባቸዋል፡፡
5. ጨረታው ተጫራቶች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በ10ኛው ቀን ከቀኑ በ11፡00 ሰዓት ታሽጎ በ11ኛ ቀን በ4፡00 ሰዓት ዳግም ህዳሴ ጤና ጣቢያ 4ኛ ፎቅ ይከፈታል። የመክፈቻ ቀን ቅዳሜና እሁድ ወይም በበዓል ቀን ከሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን በተመሳሳይ ሰዓት ታሽጎ ይከፈታል፡፡
6. ተጫራቾች የጨረታ ሳጥኑ ከመከፈቱ በፊት ለተወዳደሩባቸው ሎት 1፣ ሎት 2፣ ሎት 3 የዕቃዎች ናሙና ማቅረብ የሚኖርባቸው ሲሆን ሎት 4 ድርጅቱ የሚያቀርበውን እቃ በፎቶ እና ማኑዋል ዝርዝሩን በእስፔኩ መሰረት በፖስታ አሽጎ በሳምፕል መልክ ለግዢ ክፍል ማቅረብ አለበት እዲሁም እንደአስፈላጊነቱ የመስሪያ ቤቱ ጥራት ኮሚቴ ድርጅታችሁ ባለበት ቦታ ሄዶ ዕቃውን የሚያይ ሆናል፡፡: በሎት 5 ደግሞ መስሪያ ቤቱ ሳምፕል በሚሰጠው መሰረት ዋጋ የሚሞላ ይሆናል በሎት 6 ተጫራች ባስገባው ዋጋ የሚወዳደር ሲሆን በሎት 7 ደግሞ ተጫራች መስሪያ ቤቱ ባስቀመጠው ዲዛይን እና ቦታውን በአካል አይቶ ዋጋ የሚሞላ ይሆናል፡፡ በሎት 8 የዕቃዎች ናሙና ማቅረብ የሚኖርባቸው ሲሆን የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች በድርጅቱ በሚያቀርበው ስፔስፊክሽን ሲሆን የተበላሹ ዕቃዎች ቦታው ድረስ በማየት ዋጋ የሚሞላ ይሆናል፡፡
7. ተጫራቾች ለሚወዳደሩባቸው ዕቃዎች ለእያንዳንዱ ከቫት ጋር ያለውን ዋጋ ማስቀመጥ ይጠበቅባችዋል፡፡ አሸናፊ ተጫራቾች ያሸነፉባቸውን እቃዎች በራሳቸው ትራንስፖርት ግዢ ፈፃሚው መስሪያ ቤት ድረስ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
8. መስሪያ ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
9. መስሪያ ቤቱ ለጨረታ ካቀረባቸው ዕቃዎች ውስጥ እስከ 20% ድረስ ጨምሮ ወይም ቀንሶ የመግዛት መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ማሳሰቢያ፡- ተጫራቾች ለሚያቀርቡት ለእያንዳንዱ ዕቃ ዋጋ ከቫት ጋር ተሰርቶ መቅርብ አለበት**

**አድራሻ፡- በልደታ ክፍለ ከተማ ዳግም ህዳሴ ጤና ጣቢያ ከአባጅፋር መስጊድ ከፍ ብሎ መሰረተ ዕድገት ት/ቤት ፊት ለፊት**

**ስልክ ቁጥር፡- 011-2-79-13-59/ 011-2-79-14-80/**

**በልደታ ክ/ከተማ ጤና ጽ/ቤት የዳግም ህዳሴ ጤና ጣቢያ**

**<u>የደረሰኝ መጥፋት ማሳወቅ</u>**

በአዲስ አበባ ክልል የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 የቤት ቁጥር ጂ24 ግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) 0043284829 የሚታወቀው አልጋነሽ ገብረመድህን በየነ በግብር/ታክስ ከፋይነት ከተመዘገብኩበት አዲስ አበባ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የህትመት ፍቃድ በማግኘት የተሰራበት እና ያልተሰራበት የእጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ ከቁጥር የተሰራበት ከ 001 እስከ 004 እና ያልተሰራበት ከ 005 እስከ 050 ስለጠፋብኝ በማንኛውም አካል እጅ ወስጥ ገብቶ ወንጀል እንዳይሰራበት እና የጠፋ መሆኑ የሶስተኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ ይሁንና ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ ለመፈፀም በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው አዲስ አበባ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ወይም በአቅራቢያ የሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲደረግ አስታውቃለሁ፡፡

**የግብር ከፋይ ስም፡- አልጋነሽ ገብረ መድህን በየነ**

---

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ወረዳ 06 ክልል ውስጥ የሚገኝ በምስራች አጎናፍር ተፈራ ስም የተመዘገበ ካርታ ቁጥር 021444/1 ሴሪ ቁጥር 046270 የቦታው ስፋት 140 ካሬ ሜትር የሆነ ይዞታ በእጃቸው ላይ ያለ ኦርጂናል ካርታ የጠፋባቸው በመሆኑ በጋዜጣ እንዲታወጅ እየገለጽን በማንኛውም ምክንያት የጠፋባቸውን ካርታ ይዤዋለሁ የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከታወጀበት ዕለት ጀምሮ እስከ 30 ተከታታይ የሥራ ቀናት ባለው ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ የመሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ካርታ የምንሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት ልማት አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ወ/ሮ/ወ/ት/አቶ አዝመራው ዋለ ፈጠነ ስም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ክ/ከተማ ወረዳ 02 የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000080212700 የሆነው ይዞታ (ካርታ) ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

**<u>የጠፋ ካርታ በጋዜጣ እንዲወጣ ስለመጠየቅ</u>**

ከላይ በርእሱ ለመግለጽ እንደተሞከረው የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት በ አስቴር ንጉሴ ስም የተመዘገበ ኮንዶሚንየም /ይዞታ መለያ ቁጥሩ AA000051305280 የሆነና የተሰጠበት ቀን 18/03/2009 የሆነ የሙብት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት እንደጠፋባቸው በቁጥር GOPBM 1.16/503 በቀን 25/12/2018 ዓ.ም የሚገልጽ ማስረጃ በማቅረብ አመልክተዋል፡፡ ይህም በጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣልኝ ሲሉ ያመለከቱ ስለሆነ ካርታውን አይቻለው ወይም ሙብት አለኝ የሚል በ 30 ቀናት ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅ/ጽ/ቤት ቀርቦ እንዲያሳውቅ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ምትክ ሰርተፊኬት የምንሰጥ መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ በቀለ ማሞ በጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 5 የቤት ቁጥር 471 ካርታ ቁጥር ወ15/ወዝ01/464/12141/00 ተመዝግቦ የተሰጣቸው በእጃቸው መገኘት የነበረበት ካርታ የጠፋ በመሆኑ ይህንኑ አስመልክቶ የሚቀርብ ማንኛውም መቃወሚያ ካለ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ በ30 ቀን ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ ጉለሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ማስረጃውን ይዞ ካልቀረበ ካርታው እንደጠፋ ተቆጥሮ በምትኩ አዲስ ካርታ በማዘጋጀት አገልግሎት የምንሰጥ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የጉለሌ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ በቀድሞ ------ ቀበሌ ----- በአዲሱ ወረዳ 06 የቤት ቁጥር 205 በካርታ ቁጥር ጂ አይ ኤስ 70279 በአቶ/ወ/ሮ/እነ ታደሰ ሐይሉ እና ሰላማዊት ጎበና ስም ተመዝግቦ ተሰጥቶ የነበረ ካርታ የጠፋ ስለሆነ በማንኛውም ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል አካል ማስታወቂያው በጋዜጣ ከወጣበት እስከ 20 ቀን ድረስ ለንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ድረስ በመቅረብ አቤቱታ እንዲያቀርብ፡፡ ይዤዋለሁ የሚል ከሌለ ተለዋጭ ሌላ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የን/ስ/ላ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ/ወ/ሮ/ወ/ሪት ከወንድሙ በዳኔ ገለቱ በኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ በቀድሞ ቀበሌ ----- በአሁኑ ወረዳ 09 ቤት ቁጥር ----- ነዋሪ ሲሆኑ ከይዞታ አስተዳደር የተሰጣቸው ካርታ ቁጥር 42L በሴሪ ቁጥር ------- ኦርጂናሉ ካርታ ተፈልጎ ሊገኝ ስላልቻለ በምትኩ ሌላ ካርታ እንዲሰጣቸው ይህንን ካርታ በዕዳ፣ በዋስትና ወይም በሌላ በማንኛውም ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ካለ በ30 ቀን ውስጥ ኮ/ቀ/ክ/ከተማ ቀርቦ እንዲያሳውቅ ካላሳወቀ ግን በምትኩ ሌለ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ መሬት ልማት አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ክልል ውስጥ የሚገኝ በካርታ ቁጥር ቦሌ10/7/9/15/6654/00 ሴሪ ቁጥር 108013 አዲስ መንደር የቤት ሥራ አ/ማ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ቤት ማህደር ከለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በማህደር ክፍላችን ተፈልጎ ባለመገኘቱ ማህደራቸው ተደራጅቶ በመመሪያ መሠረት ለማስተናገድ በሂደት ላይ ስለሆነን ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ ከ30 ቀናት ውስጥ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ተቃውሞውን እንዲያቀርቡ እያሳሰብን በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ተቃውሞ የማያቀርቡ ከሆነ በምትኩ በመመሪያው በሚፈቅደው መሠረት ተገቢውን ምላሽ የምንሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ መሬት ልማት አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በወረዳ 04 ክልል ውስጥ በአቶ ዘውዴ ጓዴ መንግስቱ ስም በይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000070402168022000004 ሴሪ ቁጥር 0342918 በሆነ የተመዘገበው የጋራ መኖሪያ ቤት፤ የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም መልኩ በእጄ ይገኛል የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን 04/01/2019 ዓ.ም ጀምሮ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው መቅረብ የሚችሉ መሆኑን እያሳወቅን ይህ ካልሆነ በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ ሙብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

ወ/ሮ ይመኙሻል ፍቃዱ ፈይሳ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 8 የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር ሴሪ ቁጥር AA000060806872 ሴሪ ቁጥር L 044668 የሆነው በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ/ይዤዋለሁ የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በሶፊያ ቀፀላ ወልደመድህን አድራሻ በልደታ ክ/ከተማ ወረዳ 10 የቤት ቁጥር 66 የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000031000794 የሴሪ ቁጥር R018918 የጠፋባቸው በመሆኑ በጋዜጣ ታውጆ አገልግሎት እንዲሰጣቸው አመልክተዋል፡፡ በመሆኑም በጠየቁት መሰረት የምትክ ካርታ አገልግሎት ለመስጠት ያሙች ዘንድ ከላይ በተጠቀሱት ካርታ ቁጥሮች እና በባለጉዳዮቹ ስም የተመዘገበውን የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት /ኦርጂናል ካርታም ሆነ ኮፒውን/ ይዤዋለሁ የሚል ማንኛውም አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ልደታ ክ/ከተማ የመሬት ይዞታ ሙብት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ካልቀረበ በመመሪያ ቁጥር 61/2010 አንቀጽ 72 ንኡስ አንቀጽ 3 መሰረት በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ ሙብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ልደታ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ ሲሳይ ይልማ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ወረዳ 03 ክልል ውስጥ የሚገኘው ይዞታ ካርታ ተመዝግቦ የተሰጣቸው ካርታ ቁጥር 09578 የሴሪ ቁጥር 025142 የይዞታ ስፋት 238 ካ/ሜ የሆነ ካርታ የጠፋባቸው መሆኑን ከፖሊስ ማስመዝገባቸውን ወመ/8/3502/19 በቀን 20/12/18 ዓ/ም በተፃፈ ደብዳቤ በተገለፀልን መሰረት ወጪውን ግለሰቡ በመቻል በጋዜጣ እንዲታወጅ እየገለፅን በማንኛውም ምክንያት የጠፋው ካርታ ይዤዋለው የሚል አካል ካለ እስከ 30 ተከታታይ የስራ ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት እንዲያቀርቡ በአክብሮት እንጠይቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

# የመስከረም ስጦታዎች

በሳህሉ ብርሃኑ







ፎቶ፦ ከገፀ ድር
በመስከረም ወር ከተወለዱ ስፖርተኞች መካከል ጥቂቶቹ

የአዲስ ዓመት የመጀመሪያ ወር መስከረም በኢትዮጵያ ስፖርት ታሪክ ያለው ስፍራ ከቀን መቁጠሪያ ተሻግሮ በድል፣ በጽናት እና በከፍታ የተጻፈ ነው። የዘመን መለወጫና የበዓላት ወር የሆነው መስከረም ሲጠባ፣ የኢትዮጵያ የስፖርት ቤተሰብ የደመቁ ታሪኮቹንና የድል አሻራዎቹን በድጋሚ እያስታወሰ ይኖራል። ይህ ወር ለስፖርቱ ዘርፍ በአርዓያነት ከሚጠቀሱት ከታላቁ አርበኛ ከይድነቃቸው ተሰማ ጀምሮ እስከ ዓለም አቀፍ ስመ-ጥር ሯጮች ድረስ የበርካታ ስፖርተኞች የልደት በዓል መታሰቢያ ነው።

በመስከረም ወር የተወለዱ የኢትዮጵያ የስፖርት ባለውለታዎች ለሀገራቸውና ለአህጉራቸው ያበረከቱት አስተዋጽኦ ጉልህ ነው። በወሩ አጋማሽ ከተወለዱት የክቡር ይድነቃቸው ተሰማ የስፖርት ዲፕሎማሲና የእግር ኳስ መሠረት አንስቶ እንደ ገብረእግዚአብሔር ገብርማርያም፣ አበሩ ከበደ እና ብርሃኑ ለገሰ ያሉ የረጅም ርቀትና የማራቶን ሯጮች በዓለም አቀፍ መድረክ ያስመዘገቡት ድል ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም፤ የሕይወት ታሪካቸውና ያስመዘገቡት ስኬት ለአዲሱ ትውልድ፣ ለአፍሪካና ለዓለም አቀፍ ስፖርተኞች ትልቅ የጽናትና የከፍታ አርአያ ነው፡፡

ከመስከረም 1 ቀን ጀምሮ እስከ ወሩ አጋማሽ ድረስ የተወለዱት አትሌት ገብረእግዚአብሔር ገብረማርያም፣ አበሩ ከበደ እና ብርሃኑ ለገሰ ለአፍሪካና ለኢትዮጵያ ስፖርት ግንባታ ያበረከቱት አስተዋጽኦ የላቀ ነው፡፡ በመሆኑም የትውልድ ወራቸው የሆነውን ወርሃ መስከረምን መነሻ በማድረግ በወፍ በረር ልንቃኛቸው ወደድን፡፡

የኢትዮጵያ እግር ኳስ በዓለም አቀፍ መድረክ እንዲከበርና ጠንካራ መሠረት እንዲኖረው ከሰሩ ቀዳሚ ሰዎች መካከል አንዱ የሆኑት ክቡር ይድነቃቸው ተሰማ የተወለዱት በወርሃ መስከረም በመጀመሪያው ቀን ነው፡፡ በአትሌቲክስ አስተዳደር፣ በብሔራዊ ቡድን ስልጠና እና በስፖርት ዲፕሎማሲ ረገድ ላበረከቱት አስተዋጽኦ በኢትዮጵያ ስፖርት ታሪክ ውስጥ ትልቅ ስፍራ አላቸው። የዓለም አቀፉ ኦሎምፒክ ኮሚቴ አባልነት እና የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን ፕሬዝዳንት ሆነው አገልግለዋል።

በዓለም አቀፍ የስፖርት ደረጃ አቶ ይድነቃቸው ተሰማ በተጫዋችነት፣ በቡድን መሪነት፣ በአሰልጣኝነት የኢትዮጵያን ብሔራዊ ቡድን ይዘው ከ1940 ዓ.ም ጀምሮ በተለያዩ የአፍሪካ እና አውሮፓ ሀገሮች ተዘዋውረዋል።

"የአፍሪካ እግር ኳስ አባት" የሚል ስያሜ የተሰጣቸው የስፖርቱ ሰው አቶ ይድነቃቸው ስፖርትን ከሀገር ፍቅር ጋር በማያያዝ ወጣቶች ስነ ምግባር እንዲኖራቸውና እንዲታነጹ በማድረግ ረገድ ትልቅ አስተዋጽኦ አድርገዋል። በስፖርት ቤተሰቡ ዘንድ በትህትናቸው፣ በታማኝነታቸው እና ለሙያቸው በነበራቸው የማይናወጥ ጽናት ይታወቃሉ።

ከመስከረም ወር ጋር ተያይዞ በታሪክ ከሚነሱ ስፖርተኞች መካከል አንዱ መስከረም 1 ቀን 1977 ዓ.ም የተወለደው ታላቁ የረጅም ርቀት ሯጭ አትሌት ገብረእግዚአብሔር ገብርማርያም ነው። በውድድር ላይ ያለው ብርቱ ትዕግስትና በውድድር መድረክ የሚያሳየው ቆራጥነት የኢትዮጵያን ስም ከፍ ያደረገው ይህ አትሌት፣ የሀገራችንን አትሌቲክስ ታሪክ ከንጹህ ድል ጋር አስተሳስሮ ሰርቷል።

አትሌት ገብረእግዚአብሔር የዓለም አቋራጭ ሻምፒዮናዎችን በመቆጣጠር፣ በተለይም እጅግ ፈታኝ በሆኑት የርቀት ውድድሮች ላይ ላበረከተው አስተዋጽኦ በስፖርቱ ቤተሰብ ዘንድ ሁሌም በታላቅ አክብሮት ይታወሳል። በዓለም አቀፍ መድረኮች ላይ ኢትዮጵያን በኩራት ወክሎ በመሮጥ፣ በዓለም አቋራጭ ሻምፒዮና የወርቅና የሜዳሊያ ባለቤት በመሆን የፈጠረው ድንቅ አሻራ ከትውልድ ትውልድ የሚሸጋገር ነው። አትሌት ገብረእግዚአብሔር በረጅም ርቀት ሩጫ ታሪኩ በርካታ ድንቅ ዓለም አቀፍ ድሎችን አስመዝግቧል።

> "በመስከረም ወር የተወለዱ የኢትዮጵያ የስፖርት ባለውለታዎችና አትሌቶች ለሀገራቸውና ለአህጉራቸው ያበረከቱት አስተዋጽኦ ጉልህ ነው፤ እነዚህ የስፖርቱ ዓለም ከዋክብት የሕይወት ታሪካቸውና ያስመዘገቡት ስኬት ለአዲሱ ትውልድ፣ ለአፍሪካና ለዓለም አቀፍ ስፖርተኞች ትልቅ የጽናትና የከፍታ አርአያነት ነው"

የዓለም አቋራጭ ሻምፒዮና በፈረንሳይ፣ በዮርዳኖስ እና በሌሎች ዓለም አቀፍ ውድድሮች ላይ ሀገሩን በድምቀት ወክሏል። በየዓመቱ በሚካሄደው የዓለም አቋራጭ ሻምፒዮና ላይ በወጣቶች ዘርፍ የወርቅ ሜዳሊያ፣ በጎልማሶች ምድብ ደግሞ እጅግ ፈታኝ የሆኑ ርቀቶችን በማሸነፍ የወርቅ እና የብር ሜዳሊያዎችን ወስዷል። እ.ኤ.አ 2010 የኒው ዮርክ ማራቶን ድል የመጀመሪያ ማራቶን ውድድሩን በድምቀት የጀመረው ገብረእግዚአብሔር እጅግ ስመ ጥር በሆነው የኒው ዮርክ ማራቶን ላይ የመጀመሪያ ተሳትፎውን አድርጎ በማሸነፍ ታሪክ ሠርቷል። የኦሎምፒክ እና በኦሎምፒክ ጨዋታዎች በ5 ሺህ እና 10 ሺህ ሜትር ለኢትዮጵያ በመሮጥ ውጤታማነቱን አሳይቷል፡፡

መስከረም 2 ቀን 1989 ዓ.ም የተወለደችው ሌላኛዋ አትሌት አበሩ ከበደ እንደዚሁ በዓለም አቀፍ የማራቶን ውድድሮች ላይ ስመጥር አትሌት ናት። የበርሊን ማራቶንን በበላይነት በማሸነፍ እና አሸናፊነቷን በበርካታ የዓለም ዋና ዋና ማራቶኖች ላይ በማረጋገጥ የኢትዮጵያ ሴቶች ማራቶን አቅም ከፍ እንዲል ከፍተኛ አሻራ ካሳረፉ አትሌቶች አንዷ ነች።

በ1994 ዓ.ም መስከረም 1 ቀን የተወለደው ብርሃኑ ለገሰም የዘመናችን እጅግ ፈጣን ከሆኑ የማራቶን ሯጮች ውስጥ ቀዳሚ ተጠቃሽ ነው። በተለይም ዓለምን ባነጋገረበት የቶኪዮ ማራቶን ድል እና በዓለም አቀፍ ውድድሮች ባስመዘገባቸው ግሩም ሰዓቶች የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ከፍ አድርጎ ያስጠራ ስመ-ጥር አትሌት ነው።

በ1962 ዓ.ም መስከረም 5 የተወለደው አትሌት አዲስ አበበ በ1980ዎቹ የኢትዮጵያ የረጅም ርቀት ሩጫ ከቀየሱ አቅኚዎች አንዱ ነው። በዓለም ጁኒየር እና በጎልማሶች ሻምፒዮናዎች ላይ በ5 ሺህ እና 10 ሺህ ሜትር ውድድሮች ላይ ሀገሩን በድምቀት ወክሎ በመሮጥ ለኢትዮጵያ አትሌቲክስ መሠረት መጣል ከቻሉ ታላላቅ አትሌቶች መካከል ይጠቀሳል።

ከክቡር ይድነቃቸው ተሰማ ጀምሮ እስከ ዘመናችን ስመ-ጥር የማራቶን ሯጮች ድረስ በመስከረም ወር የተወለዱ ስፖርተኞች ያበረከቱት አስተዋጽኦ ለትውልድ የሚተርፍ ትልቅ አርአያ ነው። እነዚህ የሜዳ ጀግኖች ያሳዩን ቁርጠኝነት ስፖርት ለአንድ ሀገር ሁለንተናዊ ዕድገትና ክብር ያለው ሚና የላቀ መሆኑን ያስታውሰናል። የዘመን መለወጫ በሆነው በዚህ ወር የተዘከሩት እነዚህ ጀግኖች ሁልጊዜም የኢትዮጵያን ስም በዓለም አቀፍ መድረኮች ከፍ አድርገው ማሳየታቸውን ይቀጥላሉ።

በእርግጥ አዲስ ዓመትን አስታክከን ዳሰሳችንን ኢትዮጵያውን እውቅ ስፖርተኞች ላይ አደረግን እንጂ በመስከረም ወር የተወለዱ አፍሪካውያን እና ዓለም አቀፍ ስፖርተኞች ታሪክ ሲታይ፣ ስኬት በሜዳ ላይ ከሚገኝ ድል የዘለለ ትርጉም እንዳለው በግልጽ ይታያል። እንደ አትሌት ሞ ፋራህ እና ቦክሰኛው ፍራንሲስ ንጋኑ ያሉ የአፍሪካ ኩራቶች እንዲሁም ዓለም አቀፍ ስመ-ጥር አትሌቶች በጽናትና በድካም ያገኙት ውጤት ለአፍሪካ ወጣቶች ትልቅ መነሻ ነው።